

"ደርግን የጣለው ኢህአዴግ አይደለም"

ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ

## የሁለቱ ሲኖዶሶች መጨረሻ ምን ይሆን?



የተፈራው የ'ቀለም አብዮት' በ'ቢራቢሮ አብዮት' ሲተካ

ታዬ ንጉሤ (ዶ/ር)


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ **1** ቁጥር 12 ሰኔ **2010** ዓ.ም

ዋጋ 14.99




## በባህር ዳር የተገለጠው ቀስተ ደመና!!!

# የዚህች ባንዲራ ነገር



"የባህር ዳሩ ሰልፍ ሕገ መንግሥቱን ሙሉ ለሙሉ ይፃረራል"

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

"የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ካልተመሠረተ ኢህአዴግ ብቻውን ችግሩን አይፈታውም"

ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

"ህወሓት መራሹን በኦህዴድ መራሹ ኢህአዴግ መተካት መፍትሔ አይሆንም"

ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ሐምሌ 07
ይጠብቁን!






ቁጥር 11 ዕትም


# 5 የዚህች ባንዲራ ነገር

2 የአፋር ወጣቶች፣ “ጠ/ሚኒስትሩ ጋር አትገቡም” በሚል ተደበደቡ

8 በባህር ዳር የተገለጠው ቀስተ ደመና!!!
በፍቃዱ አባይ

10 የተፈራው የ‘ቀለም አብዮት’ በ‘ቢራቢሮ አብዮት’ ሲተካ

12 “የተቀጣጠለው ለውጥ ወደኋላ መመለስ ቀርቶ ማዝገምን አይታገሥም”
ም/ጠ/ሚ/ር አቶ ደመቀ መኮንን

14 “ህወሓት መሪሹን በኦህዴድ መሪሹ ኢህአዴግ መተካት መፍትሔ አይሆንም”
ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ

15 “የባህር ዳሩ ሰልፍ ሕገ መንግሥቱን ሙሉ ለሙሉ ይፃረራል”
ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

16 አባይ፡-ኢትዮጵያና ግብፅ
ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

17 “የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ካልተመሠረተ ኢህአዴግ ብቻውን ችግሩን አይፈታውም”
ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

18 “ደርግን የጣለው ኢህአዴግ አይደለም”
ጠ/ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



19 ያልተበረዘውና ያልተከለሰው የኢትዮጵያውያን ማንነት ለልኬት መሠረት ሆኗል።
ድምጻዊ ሊዛ ብዙ

20 ሰኔ ወር በታሪክ ውስጥ

21 ለ2026ቱ የዓለም ዋንጫ ሦስት ሀገራት ተመረጡ
ፍቅሩ ኪዳኔ

22 ታሪካዊ ቅርስን ማጥፋት...
ሰሎሞን ለማ ገመቹ

23 የዐቢይ ተቀባይነት እና የማኪያቬሊያኖቹ ጤናማ ያልሆነ አካሄድ
አሸናፊ ትርፌ

24 የድምፃችን ይሰማ ንቅናቄ ከትናንት እስከ ዛሬ
አቡበከር ዓለሙ

26 “ታላቋ ኢትዮጵያ” በጠ/ሚ ዐቢይ አንደበት

28 የሁለቱ ሲኖዶሶች መጨረሻ ምን ይሆን?

**ዜናዎች**

## ጠ/ሚኒስትሩ የእስልምና ጉዳዮች ም/ቤትንና መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴውን አስታረቁ!



ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤትንና የሙስሊሙ ማህበረሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን በነበሩባቸው ልዩነቶች ዙሪያ በሰፊው አወያይተዋል፡፡

"ለመንግሥት ክፍተት በመፍጠር፣ ሙስሊሙን በመከፋፈል ምቹ ሁኔታ የፈጠራችሁት ራሳችሁ ናችሁ" ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ፤ የመጅሊሱ ፕሬዝዳንት የሆኑት ሸይኽ መሐመድ አሚን የሙስሊሙ መሪ ነኝ ብለው ካመኑና በቦታው ላይ ከተቀመጡ፤ "ኮሚቴዎች ሲታሰሩ፣ ለምን እስር ቤት አልጠየቋቸውም? ቤተሰባቸውንስ ለምን አልዘየሩም? ለዚህም የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላቱንና ህዝበ ሙስሊሙን ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል" ማለታቸው ታውቋል፡፡

ሁለቱን ወገኖች በተናጠል ያነጋገሩት ጠ/ሚኒስትሩ፣ የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላቱ የታሰሩት ለዲናቸው መሆናቸውን ገልፀው፤ ሲወነጀሉበት የነበረው የሽብርተኛነት ካባ፤ ሐሰት መሆኑን እንዳረጋገጡላቸው ከጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት ሐላፊ አቶ ፍጹም አረጋ ትዊተር ገፅ ላይ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

ሁለቱም ወገኖች፣ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ያደረጉትን ውይይት ተከትሎ፤ የእስልምና አስተምህሮዎቻቸውን መሠረት አድርገው ችግሮቻቸውን ለመፍታት የተስማሙ ሲሆን፤ በመጨረሻም ከሁለቱም ሦስት፣ ሦስት ተወካዮች፤ ከምሁራንና ከሽማግሌዎች ሦስት ግለሰቦች፤ በአጠቃላይ ዘጠኝ አባላት ያሉበት ኮሚቴ በጠ/ሚኒስትሩ ፊት ተቋቁሟል፡፡

## የሱዳን ወታደሮች ድንበር በመጣስ ጥቃት ፈፀሙ!

ኢትዮጵያን ከሱዳን በሚያዋስነው በምዕራብ ጎንደር ዞን መተማ አካባቢ ባለው ድንበር የሱዳን መለዮ የለበሱ ወታደሮች ከኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ጋር በፈፀሙት ግጭት በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

ወታደሮቹ በመተማና በቋራ ነፍስ ገበያ አካባቢ የኢትዮጵያ መሬት ይገባኛል ጥያቄ በማንሣት በእርሻ ሥራ በተሰማሩ ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ላይ ለዓመታት ተደጋጋሚ ጥቃትና ትንኮሳ ሲፈፅሙ ኖረዋል፡፡ "መሬቱ የኢትዮጵያ ነው፤ ሱዳኖች የሚያነሡት ጥያቄ ስህተት ከመሆኑም በላይ የኛን ትዕግስት የሚፈታተን ሆኖብናል" ያሉት የምዕራብ ጎንደር ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዘላለም ልጃለም ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በወሰዱት የአጸፋ እርምጃም፣ አንድ የሱዳን ሻለቃን ጨምሮ ሰባት ወታደሮች ሲገደሉ በመተማ ደለሎ በኩል ያለው ጥቃት ፈፃሚ ጦር ተደምስሷል፡፡ በኢትዮጵያ በኩልም ሦስት አርሶ አደሮችና ሁለት የመከላከያ ሠራዊት አባላት ተሠውተዋል፡፡ ጉዳት የደረሰባቸው ስድስት የሚጠጉ ሰዎች ደግሞ መተማ ሆስፒታል ገብተዋል፡፡

ለጣምራ የፀጥታ ቁጥጥር በሚል የተቋቋመው የሱዳን ኃይል በተደጋጋሚ ስፍራውን ለቆ እንዲሄድ ሰላማዊ ጥረት ቢካሄድም እንዳልተሳካ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ተናግረዋል፡፡ ይህ ጣምራ ጦር የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን የለውጥ እርምጃ በፅኑ በሚቃወሙ ኃይሎች የሚደገፍና ሱዳንን ሽፋን በማድረግ የሚፈፅሙት ጥቃት እንደሆነ የሚናገሩ አልጠፉም፡፡

## ሕግ የጣሱ የማረሚያ ቤት አመራሮች ለፍትሕ ይቀርባሉ!

ታራሚዎችንና ተጠርጣሪ እስረኞችን አስከፊ የሰብዐዊ መብት ጥሰት በመፈፀም ለዘመናት ሲወቀሱ የነበሩት የኢትዮጵያ እስር ቤቶች እየተመረመሩ ይገኛሉ፡፡ የእስር ቤቶቹ አመራሮችና ሓላፊዎች መሰናበታቸውን የገለጸው ዓቃቤ ሕግ፣ የማረሚያ ቤት አስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን እንዳልተወጣና አመራሮቹም ከሓላፊነት የተነሡት የማረም እና የማነፅ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ችግሮች በመፍጠራቸው እንደሆነ ጨምሮ ጠቅሷል፡፡ ከዚህ በፊት ህግ የጣሱ አካላትም ጉዳያቸዉ ተጣርቶ ወደፍትሕ ይቀርባሉ ተብሏል፡፡ አስተዳደሩ ላይ የአሠራር ውስንነቶችና ክፍተቶች በመኖራቸው፣ መንግሥት ማሻሻያ ለማድረግ መገደዱንም የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ለኢቢሲ አስታውቀዋል፡፡

ከሓላፊነት በተነሡት ምትክ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ለፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተርን ጨምሮ ለአዳዲስ አምስት አመራሮች ሹመት ሰጥተዋል፡፡

ቃሊቲ፣ ቂሊንጦ፣ ዝዋይና ሸዋ ሮቢትን ጨምሮ የኢትዮጵያ እስር ቤቶች ባለፉት 27 ዓመታት በንፁሐን፤ በተለይም በፖለቲካ



አመለካከታቸው በታሰሩ ዜጎች ላይ አሰቃቂ በደል ፈፅመዋል፡፡ ከላይ አመራር እስከተራ ጥበቃ ያሉት የማረሚያ ቤቶቹ አባላት፤ ከሕገ መንግሥቱ ይልቅ የህወሓትን ፍላጎት በግልፅ ሲያስፈፅሙ ነበር፡፡ በተለይም በኦሮሞና በአማራ ተወላጆች ላይ ላደረሱት ዘር ማምከን፣ አካል ማጉደል፣ ድብደባ፣ አሰቃቂ ግርፋትና መሰል ኢ-ሰብአዊ ተግባራት በሕግ ሊጠየቁ እንደሚገባና ለዚህም በቅርብ ከእስር የተፈቱ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ከበቂ በላይ ምስክር ሆነው መቅረብ እንደሚችሉ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡

### አምባሳደር ትርፉ ኪዳነ ማርያም "ፀረ-አንድነቶች ተለይተው መውጣት አለባቸው" አሉ

አምባሳደር ትርፉ ኪዳነ ማርያም አሁን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የፍቅር፣ የይቅርታ የአንድነትና የመደመር መንገድ እጅግ እንዳስደሰታቸው በአውስትራልያ ለሚገኘው ኤስ ቢ ኤስ ሬዲዮ ገልፀዋል፡፡ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም በጠ/ሚኒስትሩ ላይ የተቃጣውን የግድያ ሙከራ አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ "በሰልፉ ላይ የሰላምና የዕርቅ ድጋፍ ለማሳየት፣ ህዝብ በነቂስ የመሰለውን አመለካከትና ሐሳብ ይዞ መውጣቱ፤ ኢትዮጵያን በአንድነት ከፍ አድርጎ ማሳየቱ፤ ዘረኝነትን እያወገዘ በፍቅርና በይቅርታ ለመኖር መወሰኑን የሚቃወሙና በዚህ የሚበሳጩ ኃይሎች የፈፀሙት ጥቃት ነው፡፡ የጠ/ሚኒስትሩ የደህንነት ጉዳይ በደንብ ሊታሰብበት የሚገባ ሲሆን፤ በፀጥታ መዋቅሩ ውስጥ ተሰግስገው ያሉ የፀረ አንድነት ኃይሎችን ለይቶ የማውጣት ሥራ ሊሠራ ይገባል" ብለዋል፡፡

# የአፋር ወጣቶች ጠ/ሚኒስትሩ ጋር አትገቡም በሚል ተደበደቡ

## “ወንድሜ ከሠልፈኞች ውሃ ሰጥተሀል በሚል ታስሯል”

**አቶ መሐመድ ቦልአ (የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል)**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰኔ 21 ቀን 2010 ዓ.ም. ወደ አፋር ክልል ተጉዘው ከክልሉ ተወላጆች ጋር ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል:: የክልሉ መንግሥት ለዘመናት ሲታማበት የቆየውን የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የህወሓትን ጣልቃ ገብነት፣ የሰብዓዊ መብቶችን ጥሰትና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ያንፀባርቃሉ ተብለው የታሰቡና ከነበረው ሥርዓት ደጋፊነት የራቁ የክልሉ ነዋሪዎች እንዳይገቡ የተደረገበት የአፋሩ ስብሰባ፤ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደሥልጣን ከወጡ በኋላ በተለያዩ ክልሎች በመገኘት ካደረጓቸው ስብሰባዎች ሁሉ በሀሳብ ማንሸራሸር ዙሪያ ደከም ብሎ የታየና የለውጥ መንገዱ ያልተዋጠላቸው ግለሰቦች ስሜትና ፍላጎት በግልፅ የተንፀባረቀበት ነው ማለት ይቻላል::



*የአፋር ወጣቶች በ ጠ/ሚኒስትሩ የድጋፍ ሰልፍ ላይ*

በአፋር ስላሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው፣ እንዲሁም ስለ ቀጣይ የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር እንዳይወያይ አስቀድሞ በተካሄደው የተደራጀ ሥራ ወጣቶች በስብሰባው ላይ እንዳይታደሙ ሲደረግ፤ በአንፃሩ በአፋር ክልል ያሉ ባለሥልጣናትንና አሠራራቸውን በመደገፍ የክልሉን ዕድገት በማቀጨጩ በኩል ለዓመታት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሲያበረክቱ የነበሩ ካድሬዎችና ደጋፊዎቻቸው ከሠላሣ ሁለቱም ዞን ተውጣጥተው በጉባዔው እንዲታደሙ ማድረጉን የግዮን የዜና ምንጮች ጠቁመዋል::

ሰኔ 21 ቀን፣ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ አፋር ክልል እንደሚሄዱና ሕብረተሰቡን እንደሚያወያዩ መገለፁን ተከትሎ በህወሐት/ኢህአዴግ አመራር ለዘመናት ጭቆና ሲፈፀምበትና በስሙ ጥቂቶች ራሳቸውን ከመጥቀም ባሻገር የዜጎችን ሰብዓዊ መብት በመርገጥ የኢህአዴግ ታማኝ አገልጋይ መሆናቸውን ያረጋገጡበትን ሂደት ለማጋለጥ የአፋር ሕዝብ ቀኑን በጉጉት ሲጠባበቅ ነበር:: በተለይም ወጣቶች በተለያየ መንገድ በመደራጀት የክልሉ መስተዳድር በልማት፣ በፖለቲካና ተዛማጅ ጉዳዮች ለአፋር ህዝብ ያበረከተው አንዳችም የጎላ ነገር አለመኖሩን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ሲያሰባስቡ ቆይተዋል::

በሌብነት (ሙስና) እና በዘመድ አዝማድነት የተንጠለጠለ አሠራርን ለማጋለጥ ፅኑ ፍላጎት የነበረው የአፋር ህብረተሰብ እስከ ዛሬ ድረስ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሁሉም ዞኖች ትልቅ መነሣሣት አሳይቶ፤ በኢትዮጵያ የጨለማ ጉዞ ውስጥ የለውጥ ብርሃን ሆነው የመጡት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ለመቀበል በዝግጅት ላይ ባለበት ወቅት ህወሓት አምላኪ ናቸው በመባል በክልሉ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ የሚቀርብባቸው የክልሉ ባለሥልጣናት በዕለቱ ሕዝብ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ስብሰባ በሚያመራበት ወቅት በያለበት በፀጥታ ኃይሎች እርምጃ እንዲወሰድበትና በጉባኤው ላይ እንዳይገኝ አምባገነንነት የታየበት እርምጃ በአደባባይ ወስደዋል::

“አሁን ሀገሪቱ በለውጥ መንገድ ላይ ነች፤ ሀሳባችንንና እስከ ዛሬ ድረስ የተፈፀመብንን በደል እናጋልጣለን” በማለት ለውይይቱ ራሳቸውን አዘጋጅተው የነበሩ የአፋር ወጣቶች፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ምሁራን ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ለመገናኘትና የውይይቱ ተሳታፊ ለመሆን፤ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል አስቀድመው ለጠየቁት ይፋዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ከመስጠት ይልቅ በዝምታ አልፈው ውይይቱ በሚካሄድበት ቦታ ጠ/ሚኒስትሩን ለማግኘት በወጡ ነዋሪዎች ላይ የኃይል ዕርምጃ እንዲወሰድ አድርጓል::

የክልሉ መስተዳድር ከሚቀርቡበት ውንጀላዎችና ክሶች የፀዳ፣ በሥልጣን ዘመኑ ለአፋርና ህዝቧ በጎ ነገር ያከናወነ ቢሆን ኖሮ ማንኛውም የአፋር ተወላጅ በውይይቱ ላይ በነፃነት እንዲሳተፍ በሩን ክፍት ያደርግ እንደነበር ያስታወሱትና ለዜና ምንጮቻችን አስተያየታቸውን የሰጡ የክልሉ ነዋሪዎች “ከክልሉ ፖሊስና ከልዩ የፀጥታ ኃይሎች የተውጣጡ ታጣቂዎች፣ ከጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ጋር መነጋገር የምትፈልጉ ወገኖች ዐሥር ሰው መርጣችሁ ስጡን” ብለው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ህዝብ በኃላፊነት መርጦ የሰጣቸውን ዐሥር ሰው ወስደው ከፍተኛ ድብደባና ጉዳት አድርሰዋል::

በድፍረት ነገሮችን የተጋፈጡ በርካታ ወጣቶች በአሁኑ ሰዓት አፋር ማረሚያ ቤት በእስር ላይ እንደሚገኙ ታውቋል::

የአፋር ክልል ባለሥልጣናት በ“መደመር” መንገድ ማልያ ቀይረው ለመቅረብ ያደረጉት ጥረት በተለያዩ ሚዲያዎች እየተጋለጠ በሚገኝበት በዚህ ወቅት እንኳን፤ እነዚህ ወገኖች ራሳቸውን ለለውጥ ከማዘጋጀት ይልቅ ዜጎችን በልዩ ኃይል አማካኝነት ማስፈራራትና ማሰሩን ሥራዬ ብሎ እንደተያያዘው የደረሰን መረጃ ያመለክታል:: የሕብረተሰቡን ፍላጎት ማድመጥ የተሳናቸው የኢህአዴግ ሰዎች ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ አፋር እንደሚመጡ ማሳወቃቸውን ተከትሎ ከሠላሣ ሁለቱም ዞኖች 16፣ 16 አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በማሰባሰብ ሰላማዊና ብዙኃኑን ህዝብ ያማከለ ውይይት ለማድረግ ያደረጉት ጥረት በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል ወዲያውኑ ሊደረስበት እንደቻለም ምንጮች ጠቁመዋል::

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ ትክክለኛውን የሕብረተሰብ ተወካይ ባለ ማግኘታቸው በውይይቱ ደስተኛ ሳይሆኑ እንደቀሩና በዕለቱ በክልሉ ባለሥልጣናት የተዘጋጀላቸውን የምሳ ግብዣ ሳይቀበሉ በፍጥነት አፋርን ለቀው እንደወጡ ያመለከተው መረጃ፤ ከቀን ወደቀን በአፋር ወጣቶች ዘንድ እየተስተጋባ የመጣው የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የሚስተካከልበትን መንገድ በአጭር ጊዜ ለመፍታት በቅርቡ አንዳንድ የሹመት ለውጦችን እንደሚያደርጉ ፍንጭ ሰጥቷል::

የአፋር ክልል ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተካሄደውን ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ በመደገፍ ከሎጊያ ሰመራ ድረስ 15 ኪሎ ሜትር በእግር በመጓዝ አደባባይ በመውጣት ለጠ/ሚኒስትሩ ያላቸውን ድጋፍ አረጋግጠዋል:: ወጣቶች በራሳቸው ተነሣሽነት ያደረጉት ይህን መሰሉ ድጋፍ ለውጡን በማይደግፉት የክልሉ ባለሥልጣናት ክፉ ዕይታ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል ነው የተባለው::

እየተንሰራፋ የመጣው ችግር መባባሱን ተከትሎ የአፋር ወጣቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ አደባባይ ሊወጡ እንደሚችሉ ሥጋት ያላቸው መሆኑን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆኑት አቶ መሐመድ ቦልአ መሐመድ ለሚመለከተው አካል ቀደም ሲል አሳውቀው ነበር:: በጠ/ሚኒስትሩ የአፋር ክልል ጉብኝት ሕገ መንግሥት ተጥሶ ከ50 በላይ ወጣቶች መታሠሰራቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የገለፁት አቶ መሐመድ፣ ወጣቶች የአፋር ሕዝብ ተጠቃሚ የሚሆንበትን እና ሌብነትና የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚቆምበትን መንገድ ከመሪያችን ጋር ለመወያየት በመፈለጋቸው ብቻ አምባገነን በሆኑ ኃይሎች እንደተደበደቡ ጠቁመዋል::

በአሁኑ ሰዓት በአፋር ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ ወጣቶች በልዩ የፀጥታ ኃይልና በክልሉ ፖሊስ አባላት እየተለቀሙ ሲሆን፤ አቶ መሐመድም በክልሉ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በማጋለጣቸው ሁለት ወንድሞቻቸው ለእስር ተዳርገዋል:: አንደኛው ወንድማቸው የታሰረውም ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ለመደገፍ ከሎጊያ ወደ ሰመራ ለመጡት ወጣቶች “ውሃ ሰጥተሃል” በሚል አሳፋሪ ምክንያት እንደሆነም ገልፀውልናል::

ካለፈው ሳምንት አጋማሽ ጀምሮ፣ በአፋር ክልል በተነሣው ውዝግብ የክልል ም/ቤት ተመራጭ የሆኑት አቶ ደርሳ ዓሊን እንዲሁም የከተማው ፖሊስ አባል የሆነችውና የወጣቶችን እንቅስቃሴ በመደገፍ የምትታወቀው ሳዲያ መሐመድን ጨምሮ ብዛት ያላቸው ወጣቶች በእስር ላይ እንደሚገኙ ያገኘነውን መረጃ ተከትሎ፤ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡን የክልሉ ዋና ኮሚሽነር አቶ ኦሎ አስቢ እና የክልሉ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዑመር ኮቢናን በእጅ ስልካቸው ላይ በተደጋጋሚ ደውለን ብንጠይቅም ስልኩን መልሰው በመዘጋትና ባለማንሣት ፈቃደኛ ሊሆኑልን አለመቻላቸውን ለአንባብያን እንገልፃለን::

# ጀግኖች አባቶቻችን የተሠውለት፤
# ሰንደቅ ዓላማ
## ወደ ክብሩ ተመለሰ !

ላለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት ሀገራዊና ኢትዮጵያዊ መንፈስ ርቆ፣ ድርጅታዊ ስሜትና ጎጠኝነት በከፍተኛ ሁኔታ ተንሰራፍቶ ቆይቷል:: ኢህአዴግ የአንድነት ገፅታን ከመናድ ባሻገር የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማችንን በርዞ ተምሳሌታዊነቱን አጥፍቶት ነበር ማለት ይቻላል::

ወያኔ/ኢህአዴግ በማንአለብኝነት ከወሰዳቸው አስከፊ እርምጃዎች ሁሉ ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ኩራት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማችንን ዜጎች በነፃነት እንዳያውለበልቡ ማገዱ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል:: ከዐሥራ ሠባት ዓመት ጦርነት በኋላ በደርግ ውስጣዊ መፍረክረክ በለስ ቀንቶት ወደ ሥልጣን የመጣው ህወሓት መራሹ መንግሥት በጫካ ዘመኑ "ትግላችን መረብ ምላሽ ነው" በማለት ለታጋዮቹ ሲያቀነቅን የቆየውን የ"ትግራዋይነት መንፈስ" መሀል አዲስ አበባ ከገባም በኋላ ደግሞታል::

ኢትዮጵያዊነትን ያልተላበሱት የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ሥልጣን በያዙ ማግስት፣ ህዝቦች ተፈቃቅረውና ተግባብተው በአንድነት ላይ የተመረኮዘ ኑሮአቸውን እንዳይገፉ ከሠሯቸው የመከፋፈል ዘርፈ ብዙ ተግባራት ሌላ፣ ኩራታችን ከሆነው ሰንደቅ ዓላማ ውጪ ያለፍላጎታችን በግዴታ እንድናውለበልብ አድርጎን ቆይቷል::

ኢህአዴግ፣ "ኮከብ የሌለውን ሰንደቅ ዓላማ ይዞ መውጣት ሕገ መንግሥቱን በኃይል እንደ መናድ ይቆጠራል" በማለት በሕግ ሲደነግግና ሲያውጅ፣ በሌላ አገላለፅ ሁላችሁም ኢህአዴግን ብቻ ደግፉ ማለቱ ነው:: ኢህአዴግ አንድ ፓርቲ እንጂ ሀገር አይደለም፣ ዜጎች ኢህአዴግን ቢቃወሙም፣ ቢደግፉም ሀገራቸውን መውደድ ግን መብታቸው መሆኑ መዘንጋት አልነበረበትም::

ጨቋኝ ነው የሚሉት የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ደርግ እንኳን፣ በሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ እንደ ኢህአዴግ አምባገነንነቱን አላሳየም:: ከሰንደቅ ዓላማ በላይ ምንም እንደሌለና፣ "አባቶቻችንና አያቶቻችን በደምና በአጥንት መሥዋዕትነት ያቆዩትን ክብር አንበርዝም" እያለ ሁሌም ዜጎች ለሰንደቅ ዓላማቸውና ለሀገራቸው ክብርን እንዲሰጡ ሲመክር ኖሯል:: ደርግ ምንም እንኳ የራሱ ድርጅታዊ ዓርማ ቢኖረውም፣ እንደ ኢህአዴግ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ላይ ለጥፋችሁ ውጡ አላለም:: ህዝብ በየትኛውም ቦታ ንጹሑን ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልብ፣ ደርግም በጽ/ቤቱ ብቻ ዓርማው ያለበትን ሰንደቅ ዓላማ ይጠቀም እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

ለኢትዮጵያዊነት ደንታ የሌለው ሕወሓት/ኢህአዴግ ኮከቡን በራሱ ጽ/ቤት ቢጠቀም አንዳች ችግር የለውም:: ሆኖም ግን ሕዝብ ንጹሑን ሰንደቅ ዓላማ በነፃነት እንዳያውለበልብ የሚያደርግ አፋኝና የተሳሳተ ህግ ማውጣቱ ስህተት በመሆኑ መንግሥት በፍጥነት ህጉን ማሻሻል ይኖርበታል:: በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለ ህዝብ ፈቃድ ኮከቡ ሲለጠፍ፣ ዓርማው የብሔር ብሔረሰብ እኩልነትን ያሳያል ተብሎ ነበር:: ባለፉት 27 ዓመታት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ቀን የብሔሮች መብት ተከብሮ አያውቅም፣ ሕወሐት/ኢህአዴግ የአንድን ብሔር የበላይነት ጠብቆ ለመዝለቅ ሌላውን ብሔር ሲያስር፣ ሲገድልና ሲያጠፉ ነው የከረመው::

ለዚህም ነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ኮከቡን" በመተው፣ የሚያውቀውንና ትርጉም ያለውን፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ በክብርና በኩራት የሚሸጋገረውን፣ ንፁህ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሰሞኑን ከዳር ዳር ይዞ የታየው:: የሰሞኑ የኢትዮጵያውያን ህዝባዊ ንቅናቄ፣ ለሀገር ወዳዱ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ይዞት የመጣው መልዕክት በግልፅ ይታያል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የጭቆና፣ የጎጠኝነትና የሀገር አልባነት ቅሪት የሆነው ኮከብ ከሰንደቅ ዓላማው ላይ እንዲነሣለት ይፈልጋል::፡ ህዝብ አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ጉዳዩን በሕግ አስደግፈው ወደ ተግባር እንዲያመጡለት እግረ መንገዱን ጥያቄውን አቀረበ እንጂ፣ ሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ፣ በጎንደር፣ በደሴና በወልድያ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተደረጉ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ላይ ኮከቡን አስቀድሞ በማንሣት በአደባባይ ዘምሯል::

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ከነክብሩ ብዙ ዓመታትን ተጉዟል:: ጊዜውን ጠብቆም በሕዝብ ልብ ውስጥ ሲውለበለብ የቆየው የማንነታችን መገለጫ በጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ጊዜ፣ ዳግም በክብር አደባባይ ወጥቷል:: ከሀገር በላይ ምንም የለምና፣ ጀግኖች አባቶቻችን መሥዋዕትነት የከፈሉለት ሰንደቅ ዓላማችን ዳግም ወደ ክብሩ ተመልሷል:: ኢትዮጵያ ክብርና ሞገሷ ኃያል ነው፣ይህንን እውነታ የሚያረጋግጠውና ውስጣችንን ሀሴት የሚሞላው ሰንደቅ ዓላማችን ግን ሁሌም እንዲህ በክብር ሲውለበለብ ማየት የሁላችንም ፍላጎት ነው::


ግዮን መጽሔት
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየ 15 ቀኑ ለኅትመት**
**የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል

**ዋና አዘጋጅ**
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

**አዘጋጆች**
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

**አምደኞች**
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
enqu2013@ gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤
አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10
የቤ.ቁ. 066/ሀ

# የዚህች ባንዲራ ነገር



ፎቶ መለኩ ብርሃኑ

ሰኔ 24 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. የአማራ ክልላዊ መንግሥት መዲና በሆነችው ባህር ዳር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለተጀመሩ በጎ ተግባራት ድጋፍ ለመስጠት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የታደመበት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህ የአዲስ አበባውን የሰኔ 16 ትዕይንተ ህዝብ ተከትሎ የተካሄደ ሰላማዊ ሰልፍ አንድም ባለኮከብ ባንዲራና የአማራ ክልል መለያ ሰንደቅ ያልታየበት ነበር፡፡ "አማራ የሚያነሣው ሰንደቅ፣ የኢትዮጵያዊነት መለያ የሆነውን እንጂ በብሔርተኝነት ለተሰፋ ባንዲራ ድጋፍ የለውም፤ ኢትዮጵያን የሚወክላት ሰንደቅ ዓላማ ውስጡ ምንም የፖለቲካ ምልክት የሌለበት አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩ ብቻ ነው" በማለት ህዝቡ ሐሳቡንና ውሳኔውን በተግባር ገልጾ ነበር፡፡ ይህንን ተከትሎ ህወሓት በትግራይ ቲቪ ባስተላለፈው ዘገባ ላይ "በአማራ ክልል የተካሄደው ሰልፍ ደርግ ያደራጀው ሰልፍ ነው፡፡ ኮከብ የሌለው ሰንደቅ ዓላማ ይዞ መገኘት ሕገ መንግሥቱን ስለሚጻረር ሰልፉ በአጠቃላይ ሕገ መንግሥት የተጣሰበት ነው" በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ በሰልፉ አመራሮችና ህዝቡ የተጠቀሟቸውን ቃላትም "ይመለከቱኛል" ዓይነት ሥጋቱን አቅርቧል፡፡

**ህወሐት ከበላይ ሆኖ የመራው ኢህአዴግ ለዘመናት የሰውን ሰብዓዊ መብት ሲገፍፍ እና መንግሥታዊ አሸባሪነት ተግባር ውስጥ ገብቶ ራሱ ሕገ መንግሥቱን ሲንድ ኖሮ፤ ከጥቅሙ ጋር የሚጋጭና ከፖለቲካ ሥልጣኑ የሚያገልለው ሂደት ሲመጣ የባንዲራውን ነገር በማስታከክ ደርሶ የሕገ መንግሥቱ ጠበቃ ሆኖ ብቅ ማለቱ ብዙዎችን አስገርሟል**

የህወሓት ወኪል የማህበራዊ ሚዲያ አንቀሳቃሾች በተለይ በባህር ዳር በተውለበለበው ባንዲራ ጉዳይ ላይ ሰፊ ተቃውሞ በማቅረብ ጉዳዩን ከአማራ ገዢ መደብ ፍላጎትና ከጠቅላይነት አስተሳሰብ ጋር አዛምደው ለመንቀፍ ሞክረዋል፡፡

በዚህ ባንዲራ የተነሳው ክርክር አሁን ድረስ ያልበረደ ከመሆኑ፤ በተለይም ህዝቡ ባንዲራው እንዲቀየር አጥብቆ ከመፈለጉ ጋር በተያያዘ ከባንዲራው እና ከሀገር ፍቅር ስሜት ጋር የተያያዙ ትርክቶችን በዛሬ ጽሑፋችን እንዳስሳለን፡፡ "ለመሆኑ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ባንዲራ የቱ ነው?" ብለንም እንጠይቃለን፡፡

## ታሪክና ጀግንነት

የኢትዮጵያ ህዝብ የላቀ ቦታ ከሚሰጣቸውና እንደማንነቱ መገለጫዎች ቆጥሮ ከማይደራደርባቸው ነገሮች ውስጥ ሀገር፣ ሰንደቅ ዓላማና ነጻነት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ታሪክ እንደሚመሰክረው ኢትዮጵያዊ ▶

በሀገሩ ጉዳይ ለመጣበት ግንባሩን የማያጥፍ፣ ኩሩና በነጻነት መኖርን የለመደ ህዝብ በመሆኑ መገዛት እና በሌሎች ተጽዕኖ ውስጥ መውደቅን አጥብቆ ይጠላል። በዚህ ሳቢያም በዘመነ ቅኝ ግዛት የአፍሪካ ሀገራት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ እንደቅርጫ በተቀራመቷቸው ቅኝ ገዢዎች መዳፍ ሥር በወደቁበት ዘመን አየሯ የነጻነት ንፋስ እየነፈሰባትና አፈሯ በቅኝ ገዢዎች ሳይረገጥ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ዘመኑን የተሻገረች ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት።

የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ ያላትን ጥንታዊቷን ሀገር ኢትዮጵያን ዓለም የሚያውቃት በዳበረ ታሪኳ ብቻ ሳይሆን፤ ለውጭ ወራሪ ኃይል ሳትንበረከክ ነጻነቷንና ሰንደቅ ዓላማዋን አስከብራ የኖረች ባለታሪክ ሀገር በመሆኗም ጭምር ነው። በተለይም የአፍሪካ አህጉር ህዝቦች ክብርና ማንነታቸው ተዋርዶ፣ ለባርነት ተዳርገውና በነጮች ተረግጠው ባህልና ቋንቋቸው እስኪጠፋ ድረስ በገዛ ሀገራቸው የተሰቃዩበት የቅኝ ግዛት ታሪክ ያልደፈራት በመሆኗ፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲል ተብላ እንድትጠራ ምክንያት ሆኗል። የጥቁሮችን ታሪክ የሚጽፉ ምሁራን ደጋግመው እንደሚያነሡትም፣ ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ዘመን ጭዳ ያልሆነችው ሳትወረር ቀርታ ሳይሆን፤ ከዚህ ቀደም በታሪክ ሊመዘገብ ቀርቶ ሊኖር ይችላል ተብሎ በማይታሰብ ቆራጥነት ነጭ ቅኝ ገዢና ወራሪ ኃይልን ጦርነት ገጥማ ድል በመንሣቷም ጭምር ነው።

በዚያ የአፍሪካ ኋላ ቀር የጨለማ ዘመን የኢትዮጵያ ህዝቦች ዘርና ጎሳ፣ ሃይማኖትና ብሔር ሳይለዩ፤ ለአንድ ሀገራቸው በጋራ በመዝመት እስከአፍንጫው የታጠቀውንና ማንም የሚቋቋመው የማይመስለውን ወራሪ የጣልያን ጦር፤ በሀገር ፍቅር ወኔና በጀግንነት ብቻ እጅግ ኋላ ቀር በሆነ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ መክተው፤ ድል በመንሣት የሽንፈት ካባ ማከናነባቸው እስከዛሬም ለዓለም ትንግርት እንደሆነ ኖሯል።

ኢትዮጵያውያን ወራሪውን የጣልያን ፋሽስት የመስፋፋት ህልም በማጨንገፍ በጦር ሜዳ ገጥመው ድል የነሡበት የአድዋ ጦርነት፤ መላውን የአፍሪካና የዓለም ጥቁር ህዝቦች አንገት ቀና ያደረገ አኩሪ ታሪክ ነው። ኢትዮጵያ፣ ተፈራርቀው በገዟት ኃያል መንግሥታቷ ታሪክ ውስጥ በዘመኗ አንድም ጊዜ ሌላ ሀገር ወርራ አታውቅም። ነገር ግን ከቱርክ ፓሻዎች እስከ ግብፅ ፈርዖኖች፣ ከመሃዲስቶች እስከ ደርቡሾች እንዲሁም ከእንግሊዞች እስከ ጣልያኖች ተስፋፊውን የሶማሊያ ጦር ጨምሮ ድንበሯን ጥሶ ለመግባት ተደጋጋሚ ወረራ ተፈጽሞባት በጀግኖች ልጆቿ ደምና አጥንት አጥሯን ሳታስደፍር ዘመናትን ተሻግራለች።

የዚህ ሁሉ በደምና በአጥንት የተዋጀ ነጻነት ማሰሪያ ጥብጣብ፤ የኢትዮጵያ መለያ የሆነው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ነው። ይህ ሰንደቅ ዓላማ በአምሥት ዓመቱ የጣልያን ወረራ ዘመን ወድቆ፤ በጀግኖች አርበኞች መሥዋዕትነት ዳግም ወደማማው ከመመለሱ በቀር በዘመናት የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንዴም የነጻነት ምልክትነቱ ሳይጠፋ ሁሌም ሲውለበለብ ኖሯል። ብዙዎች እንደሚሉትም ከቅኝ ግዛት ዘመን ማክተም በኋላ የአብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ሰንደቅ ዓላማ ቀለሞች የተዋቀሩት በነዚሁ ሦስት ቀለማት የመሆኑ ዋና ምክንያትም ይህንኑ የነጻነት ተምሳሌት የሆነውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለማሰብ ነው።

## የሀገር እና የባንዲራ ፍቅር

(እድሜ ለኢህአዴግ ይሁንና) እንደዛሬ የባንዲራ ክብር በፖለቲካ አተያይ እና በተዛቡ ታሪኮች የተንሻፈፈ ትርጉም ይዞ የክርክርና የጸብ መንስዔ ከመሆኑ በፊት በዚያ የሀገር ፍቅር ስሜት በደሙ ገብቶ ያነደደው በነበረ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ውስጥ ሀገር ማለት ነጻነት፣ ነጻነት ማለት ደግሞ በኩራት የምትውለበለብ ሰንደቅ ዓላማ ማለት ነበር። እስከዘመነ ኢህአዴግ ዋዜማ ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሩ ጉዳይ በአንድ አሳብ እና በአንድ መንፈስ ተሳስሮ እንዲኖር ምክንያት የሆነው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ ዓላማ የኔ ብሎ ተቀብሎ መኖሩና ለባንዲራው ክብርም ሕይወቱን መሥዋዕት እስከማድረግ የደረሰ ፍቅር ስለነበረው ነው።

ድሮ ወራሪዎች በጦር ሞክረው አልሳካላቸው ሲል በሽንፈት የተሰናበቱበትን ኢትዮጵያን በዘር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖትና በብሔር ከፋፍሎ የማዳከም እቅድ ዛሬ በራሱ ፍላጎት በተግባር ለማሳካት እየዳከረ ያለ (በመጠኑም የተሳካለት) የፖለቲካ አመራር የሚፈነጭባትን መሬት በደምና አጥንታቸው ዋጋ ከፍለው ያስረከቡን አባቶቻችን የተዋደቁት ለሰንደቃቸው ክብር ነበር።

ለኢትዮጵያዊ፣ ባንዲራ ማለት ማንነት ነው። ባንዲራ ማለት በደም የሰረጸ ነጻነት፣ የባለታሪክነት ምስክር፣ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ፣ የነጻነት ዓርማ፣ የሀገር ፍቅር ስሜት ማከማቻ ነው። በዚህ ሳቢያም ነው ኢትዮጵያውያን በቀደመ የነጻነት ታሪካቸው መለያቸው ሆኖ የኖረ ሰንደቃቸውን በየትኛውም የዓለም አደባባይ ከፍ አድርገው ማውለብለብ ህልማቸው ሆኖ የሚኖሩት።

በጦርነት ጊዜ "ተከተል ንጉሥህን፤ ተመልከት ባንዲራህን" ብሎ በወኔ የሚተም ተዋጊ ሠራዊት ከዚያ የጦር አውድማ የሚበተነው፤ ሰንደቁ ከዓይኑ የጠፋ እና የወደቀ እንደሆነ ብቻ ነው። ኢትዮጵያዊ፣ በውጊያ ላይ እያለም ቢሆን፤ አንዱ ሲወድቅ ሌላው ሰንደቁን እያነሣ እስከመጨረሻው ባንዲራውን መሬት ላለማስነካት እየታገለ ነው መሥዋዕትነት ከፍሎ ለድል የሚበቃው። በዚህ ሳቢያ የትኛውም ቦታ ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ያየ ኢትዮጵያዊ በፍጹም የሀገር ፍቅር ስሜት በዓይኖቹ ዕንባ ይሞላል። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዓለም አደባባይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ ማውለብለብ የሌት ተቀን ሕልማቸው ነው። ለዚያም ነው ባንዲራው ሲሰቀል ዕንባቸውን መቆጣጠር የማይችሉት። በሰው ሀገር ስደት ላይ ያለ ኢትዮጵያዊም ሰንደቅ ዓላማውን ሲያይ ሀገሩን እንዳየ የሚደነግጠውና የሚደሰተው፣ "የሰው ሀገር ሰው፤ ባንዲራ ዘመዱ" ብሎ የሚተርተው ለዚሁ ነው።

ኢትዮጵያዊ ማለት ለሕግ እና ለባንዲራ ታማኝ የሆነ ህዝብ ነው። በቀደመው ዘመን "በሕግ አምላክ!" ተብሎ ተጠይቆ እምቢ የሚል፣ "በባንዲራው!" ተብሎ የተጠየቀውን የሚጥስ ማንም ሰው እንደነውረኛ ብቻ ሳይሆን እንደ ከሃዲ ይቆጠር ነበር። የሕግንና የባንዲራን ክብር ማናናቅና ለቃሉም አለመገዛት ብቻውን ለክስ እና ለቅጣት የሚያበቃ ወንጀልም ነበር። በተለይም ኢትዮጵያን ከጣልያን የግፍ ወረራ ነጻ ለማውጣት በጥንት አባቶቻችን በተካሄደው የአምሥት ዓመቱ የአርበኝነት ዘመን በኋላ በነበረው የነጻነት ጊዜ "ወድቆ በተነሣው ባንዲራ!" ብሎ መለመን ወይም መገዘት፤ ብቻውን ማንኛውም ሁከት እንዲወገድ ወይም ሰዎች ከጀመሩት መልካም ያልሆነ ተግባር እንዲታቀቡ ለማድረግ በቂ ነበር። በኢትዮጵያ የባንዲራ ክብር እዚህ ድረስ ነበር።

## ክብርና ባንዲራ

በኢትዮጵያ ከተነሱ መንግሥታት ሁሉ እንደኢህአዴግ ራሱ በሚመራት ሀገር ላይ የተሳለቀና ታሪክና ክብሯን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት መንግሥት ተነሥቶ አያውቅም። በታሪክ ተመራማሪዎች ጥያቄ የማይቀርብበት፣ በብዙ ማስረጃዎች የተደገፈውና የተረጋገጠው እውነት፤ ኢትዮጵያ የ3 ሺህ ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆነች ሀገር መሆኗ ነው። ይህንን እውነት ዓለም አክብሮት ህወሓት/ኢህአዴግ ግን የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ100 ዓመት አውርዶታል።

ህወሓት ከጅምሩም ሆነ እስካሁን ድረስ አብሮት በኖረ እምነቱ "ከትግራይ ውጪ ያለው ቀሪ የኢትዮጵያ ክፍል ታሪክ አልባ ነው" ብሎ ያምናል። በህወሓት ስሌት መሠረት የኢትዮጵያ የታሪክ አስኳል ትግራይ እንደመሆኗ፤ ትግራይን መገንጠል ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ታሪክ ከምኒልክ ዘመን ጋር ብቻ አቆራኝቶ ያስቀራታል ብሎ ያምናል፤ ሲሠራም የኖረው ይህንኑ ለማስፈጸም ነበር። ከጅምሩም ትግራይን ነጻ የማውጣት ዓላማ ብቻ ይዞ ብረት ያነሣው ይህ ፓርቲ፤ በታሪክ አጋጣሚ ግንባር ፈጥሮ ኢትዮጵያን የመምራት ዕድል ሲያገኝ ለአገዛዙ እድሜ ለመቀጠል ሲል የኖረ እምነቱን ጠረጴዛ ሥር ከትቶ አስቀምጦት ኖሯል። ያም ሆኖ አልፎ አልፎ እውነተኛ ማንነቱ ብልጭ ማለቱ አልቀረም። ህወሓት ከዚህ የ100 ዓመት የታሪክ ትርክቱ ባሻገር ግን አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ጥርስ ውስጥ የከተተው በወቅቱ የድርጅቱ ሊቀ መንበር እና የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የሆኑት መለስ ዜናዊ "ባንዲራ ጨርቅ ነው" በማለት ስለባንዲራ በአንደበታቸው የተናገሩት ንግግር ነው። ይህ ንግግር ለባንዲራው ክብር ሲል ነፍሱን አሳልፎ በሰጠው ትውልድ ዘንድ እስካሁን ድረስ በህወሓት ላይ ያልተፈታ ቂም እንዲቋጥርበት አድርጓል።

የኢትዮጵያ ባንዲራ በየዘመኑ ሀገሪቱን እንዳስተዳደሯት መንግሥታት ቀለሙ አንድ ሆኖ መሐሉ ላይ ግን ምልክት ሲቀያየርበት ኖሯል። በምኒልክ ዘመን "ም" የሚል ምልክት እንደነበረው ሲነገር፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ደግሞ የይሁዳ አንበሳ ዓርማ ነበረበት። የደርግ ዘመን በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ጊዜው ማጭድና መዶሻ ኋላም ኢህዲሪ ሲመሠረት ያንኑ ዓርማ በባንዲራው ላይ አትሟል። ደርግ ከወደቀ በኋላ፣ የኢህአዴግ መንግሥት በባንዲራው ላይ ኮከብ በማተም ሥራ ላይ አውሎታል። ያም ሆኖ ከኢህአዴግ ውጪ በነበሩት ያለፉት መንግሥታት ህዝብ በብሔራዊ፣ ሃይማኖታዊና ህዝባዊ በዓላት ወቅት ይዞ የሚወጣው ባንዲራ፤ ምንም ዓርማ የሌለውን ሲሆን፣ ባለአርማዎቹ ባንዲራዎች ለጽህፈት ቤትና ለኦፊሴል አገልግሎት ብቻ ሲውሉ ኖረዋል። ነገር ግን ኢህአዴግ ባንዲራውን ከቀየረ በኋላ ሕግ በማውጣት፣ ኮከብ የሌለው ባንዲራ የያዘ ሰው በሕግ እንደሚቀጣ በመደንገጉ ለወትሮ ባንዲራን እንደክት ልብሱ በቤቱ በጥንቃቄ ያስቀምጥ የነበረው ኢትዮጵያዊ ባልተለመደ ሁኔታ ከአዲሱ ባንዲራ ጋር ተለያየ። ቤተ ክህነት ሳትቀር የፖለቲካ ዓርማ ያለበትን ባንዲራ ለማውለብለብ ተገደደች። ይህም ብዙዎችን አስቆጥቶ ቀን እንዲጠብቁ አደረጋቸው።

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የፓርላማ አባል የነበሩትና የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል የሆኑት

**ለኢትዮጵያዊ፣ ባንዲራ ማለት ማንነት ነው። ባንዲራ ማለት በደም የሰረጸ ነጻነት፣ የባለታሪክነት ምስክር፣ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ፣ የነጻነት ዓርማ፣ የሀገር ፍቅር ስሜት ማከማቻ ነው። በዚህ ሳቢያም ነው ኢትዮጵያውያን በቀደመ የነጻነት ታሪካቸው መለያቸው ሆኖ የኖረ ሰንደቃቸውን በየትኛውም የዓለም አደባባይ ከፍ አድርገው ማውለብለብ ህልማቸው ሆኖ የሚኖሩት**

◀ሻለቃ አድማሴ በ1987 ዓ.ም. የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ጉባዔ ላይ፤ የህወሓት/ ኢህአዴግ ሊቀ መንበር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ አገሪቱን በተቆጣጠረበት 1983 ዓ.ም. አካባቢ በቴሌቪዥን ቀርበው፣ “ባንዲራ ጨርቅ ነው” ብለው መናገራቸውን በመጥቀስና ታጋዮቹም ባንዲራውን የጨውና የዱቄት መጠቅለያ ማድረጋቸው ትክክል አለመሆኑን አንሥተው ባንዲራ ክብር መሆኑን ለማስረዳት ጥረው ነበር፡፡ ሻለቃ አድማሴ፣ በወቅቱ አቶ መለስን ሲያስጠነቅቁ “በዚህች ባንዲራ ላይ አንዲት ነገር ብትጨምሩባት ህዝቡ አይቀበላችሁም፤ ይቃወማችኋል” ብለዋቸው ነበር፡፡ እንደትንቢት ሆኖም እነሆ ህዝብ በዚህች ባንዲራ የተነሣ ኢህአዴግን ሁለት ዐሥርት ዓመታት በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ ሲቃወም ኖረ፡፡

በወቅቱ ለሻለቃ አድማሴ ጥያቄ ከረር ባለ ድምጸት የተሰጠው የአቶ መለስ ምላሽ ግን ህወሓት እንደፓርቲ ሲታይ ከኢትዮጵያ ባንዲራ ጋር ባለው የተለየ አመለካከት ጸብ እንዳለው በግልጽ ያሳየ ነበር፡፡ “ኢህአዴግ የራሱ መለያ አለው፡፡ ከባንዲራው ጋር ችግር የለበትም፡፡ ችግሩ ከባንዲራው ኋላ ካለው ‘የኔ ጥሩ፤ ያንተ ጥሩ ያልሆነ’ ከሚለው አስተሳሰብ ጋር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ባንዲራውን ከፈለገው የራሱ ጉዳይ ነው፡፡ ባለበት እንዲቀጥል ያደርጋል ወይም ይለወጥ ካለም ይለወጣል” በማለት “ባንዲራ ከጨርቅ የዘለለ ትርጉም የለውም” የሚለውን የቀድሞ ቃላቸውን አድሰውታል፡፡

ባንዲራው ለጨው እና ለዱቄት መያዣ መዋሉን በተመለከተ ለተጠየቁት ሲመልሱም “አንዳንድ የድርጅታችን አባላት ነገሩን በውል ባለመገንዘብ አድርገውት ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆነ ይህ ግን ኢህአዴግ ከባንዲራው ችግር የለበትም” በማለት ፓርቲያቸው የባንዲራው ጉዳይ ያን ያህል የማያስጨንቀው መሆኑን በድጋሚ ገልጸዋል፡፡

አቶ መለስ “ኢህአዴግ የባንዲራው ጉዳይ ያን ያህል አያስጨንቀውም” ባሉበት እና “የኢትዮጵያ ህዝብ ባንዲራውን ከፈለገው የራሱ ጉዳይ ነው፣ ይለወጥ ካለም ይለወጣል” ብለው በተናገሩበት አፍ ዛሬ ከ27 ዓመታት በኋላ በባንዲራው ጨው ሲቋጥሩበት የኖሩት የፓርቲያቸው ሰዎች ባንዲራውን ተንተርሰው ሕገ መንግሥት ተጣሰ እያሉ ነው፡፡ የቀድሞ መሪያቸው “ህዝቡ ባንዲራውን ካልፈለገው ሊለውጠው ይችላል” ያሉትን ረስተው፤ ህዝብ ወደቀድሞ መልኩ የተቀየረውን ባንዲራ ብቻ እንደሚፈልግ የተናገረበትን መድረክ “ደርግ የነገሠበት መድረክ” በማለት አጣጥለውታል፡፡

## “የህዝብ ባንዲራ”

ጠ/ሚ ዐቢይ ወደሥልጣን ከመጡበት ጊዜ አንሥቶ በይቅርታ፣ በፍቅርና በመደመር መርህ የሀገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ 360 ዲግሪ በመቀየር ማንም ያልጠበቀውን ሪፎርም ጀምረዋል፡፡ በዚህ ሳቢያም ከህዝብ ፍላጎት ውጪ በሆነ መንገድ መንግሥት ሀገር መምራት እንደማይችል በማመን፣ ኢትዮጵያ ከገባችበት የእርስ በርስ መጠላላትና ጠቅላላ ውድቀት ይታደጋታል ላሉት ለዚህ ሪፎርም እንቅፋት የሆኑትን አካላት በጊዜ ጥግ አስይዘዋቸዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለህዝቡ ልብ ቀርበው የዘመናት ጥያቄዎቹን በመመለስ የወሰዷቸው በጎ እርምጃዎች ባረጀና ያፈጀ የተንኮል፣ የጭቆና እና የአውቅልሃለሁ ፖለቲካ የሚመራውን የአዛውንቶቹን ፓርቲ ህወሓትን ያስከፋው ሲሆን ከፌዴራል የሥልጣን መዋቅሩ በጡረታ የተሰናበቱ አዛውንት አመራሮቹን ይዞ መቀሌ ላይ እስከመመሸግና እንደተቃዋሚ ፓርቲ ይፋዊ የተቃውሞ መግለጫ እስከማውጣት አድርሶታል፡፡ ህወሓት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የሪፎርም መንገድ በተቃራኒ የቆመ መሆኑን በተዘዋዋሪ በሚያደርጋቸው አሉታዊ ተግባራት በይፋ አውጇል፡፡ በሃገሪቱ ውስጥ እዚህም እዚያም የሚቆሰቆሱ ብጥብጦች እና አለመረጋጋቶች ይህንን የለውጥ ጉዞ ለማስቀረት የተወጠኑ እርምጃዎች መሆናቸውን የተረዳው የኢትዮጵያ ህዝብም፣ እነዚህን ቁማርተኞች በመቃወም ከጠ/ሚ ዐቢይ ጎን ለመሰለፍ እና ድጋፉን ለመግለጽ ታላቅ ህዝባዊ ትዕይንት ማካሄድ የጀመረው በዋና መዲናዋ አዲስ አበባ ነበር፡፡

እዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ህዝቡ ቀድሞ ሲቃወመው የኖረውን፣ ነገር ግን የህወሓት/ ኢህአዴግ መንግሥት ከህዝብ ፍላጎት ውጪ የሀገሪቱ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ያደረገውን ባለኮከብ ባንዲራ በመተው ምንም ምልክት የሌለውን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ነበር በብዛት ይዞት የወጣው፡፡

ያ ታላቅ ትዕይንተ ህዝብ ጠ/ሚ ዐቢይ “የቀን ጅቦች” ባሏቸው የለውጥ አደናቃፊና አኩራፊ ኃይሎች በታቀደ ተንኮል በቦምብ ፍንዳታ ቢቋረጥም፤ የህዝቡ የለውጥ መንፈስ ግን ሊዳከም አልቻለም፡፡ ይህንን በኢትዮጵያ ታሪክ ያልተመዘገበ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተሞች የተካሄዱት ሰልፎችም ተመሳሳይ ዓላማ ያነገቡና በተለይ በኮከብ አልባው ባንዲራ የደመቁ ነበሩ፡፡

ከዚህ ድጋፍ ጎራ አለመሆኗን በግልጽ ያወጀችው መቀሌ፣ ሰልፍ ማድረግ ቀርቶ በተቃራኒው የጠ/ሚ ዐቢይን ጉዞ የሚቃወም እና እርምጃው ከህወሓት ፍላጎት ተቃራኒ መሆኑን የሚያውጅ መግለጫ በማውጣት ተጠምዳ ከርማለች፡፡ የክልሉ ቴሌቪዥንም የአዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች የአገሪቱ ከተሞች የሚካሄዱ የድጋፍ ሰልፎችን ላለመዘገብ እንደምክንያት ያስቀመጠው ከሰንደቅ ዓላማው ጋር የተያያዘ ትርክቱን ነው፡፡ ህወሓት ከበላይ ሆኖ የመራው ኢህአዴግ ለዘመናት የሰውን ሰብዓዊ መብት ሲገፍፍ እና መንግሥታዊ አሸባሪነት ተግባር ውስጥ ገብቶ ራሱ ሕገ መንግሥቱን ሲንድ ኖሮ፤ ከጥቅሙ ጋር የሚጋጭና ከፖለቲካ ሥልጣኑ የሚያገልለው ሂደት ሲመጣ የባንዲራውን ነገር በማስታከክ ደርሶ የሕገ መንግሥቱ ጠበቃ ሆኖ ብቅ ማለቱ ብዙዎችን አስገርሟል፡፡

በዚህ ሂደት ላይ ሳለ ነው እጅግ ብዙ ህዝብ የተካፈለበት የባህር ዳሩ ትዕይንተ ህዝብ የተካሄደው፡፡ ይህ ሰላማዊ ሰልፍ ከአዲስ አበባውም ሆነ ከክልል ከተሞች የሚለየው ነገር ሙሉ በሙሉ በአረንጓዴ ቢጫና ቀይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ብቻ መድመቁ ነው፡፡ በዚህ ሰልፍ ላይ የክልልም ይሁን የፓርቲ ሰንደቅ ዓላማዎች አልተውለበለቡም፡፡ በሰላማዊ ሰልፉ የገነነው እና የጎላው ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው፡፡ በሰልፉ ላይ ህዝቡ ብቻ ሳይሆን የክልሉ ጸጥታ ኃይሎችም የያዙት ባንዲራ ይህንኑ ኮከብ አልባውን ባንዲራ ነው፡፡ ትዕይንተ ህዝቡ በተካሄደበት ስታዲየም ዙሪያ ስታንዣብብ የዋለችው ሄሊኮፕተርም በይፋ ታውለበልብ የነበረው ሰንደቅ ዓላማ ይህንኑ ነው፡፡

## ከህዝብ ተቃርኖ ወዴት ይጓዟል?

ህዝብ የሚፈልገውን መከተል የመንግሥትና መሪ ፓርቲዎች ድርሻ ነው፡፡ ኢህአዴግ በህዝብ የተመረጠ ፓርቲ ባይሆንም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ቢያንስ የህዝቡን ጥያቄ መመለስና ህዝብ በሚፈልገው መንገድ መጓዝ ግድ ይለዋል፡፡ እንዲያ ካልሆነ ከህዝብ ጋር ወደቅራኔ መግባትና በመጨረሻም ራሱ ወደሥልጣን በመጣበት መንገድ በአመጽ መውረድ ዕጣ ፈንታው ይሆናል፡፡ ጠ/ሚ ዐቢይ ይህንን ቀድመው መገንዘብ የቻሉ የፓርቲው ሰው ናቸው፡፡ እንደአጠቃላይ መዋቅር ፓርቲያቸው የሚከተለው አግላይና ጠቅላይ አመራር የዴሞክራሲያዊ መንግሥት መገለጫ አለመሆኑ በመሪና በተመሪ መካከል እያደር ያመጣውን ክፍተት ፍጹም ሰላማዊ በሆነ እርቅ እና ይቅርታ በመድፈን የፓርቲውን መንገድ ለማስተካከል በመጣር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ግን “እኛ ካልሆንን ማንም በዚህ ስፍራ መቀመጥ የለበትም” ለሚሉት ህወሓቶች አልተዋጠላቸውምና በሰበብ በአስባቡ የጠ/ሚ ዐቢይን አመራር ለመተቸት ብሎም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተከሰተ ለሚሉት ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ በግልጽ በስም ማጥፋት ዘመቻ ላይም ተጠምደዋል፡፡

ከነዚህ መክሰሻ ምክንያቶቻቸው ውስጥ በ17 ዓመታት ትግላቸው ወቅት የናቁትንና የሚፈሩትን፣ አንድነትን የሚሰብክ እና ኢትዮጵያዊነትን የሚያስተሳስር በመሆኑ ሊያጠፉት ተነሥተውለት የነበረውን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ የመነታረኪያ ርዕስ አድርገው ተነስተዋል፡፡ ህወሓቶች፣ ይህ የህዝብ ምርጫ የሆነ ኮከብ አልባ ባንዲራ በሁሉም ስፍራ ሲውለበለብ ዝም ብለው፤ ነገር ግን በባህር ዳር ሲውለበለብ የተቃወሙበት ምክንያት ለዘመናት ለአማራ ህዝብ ያላቸውን ጥላቻ ስላጋለጠባቸውና የብአዴን አመራርም ሴራቸውን ደርሶበት፣ ከነርሱ መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑን ስላወጀባቸው ብቻ ነው፡፡ በዚህ ሳቢያ የባህር ዳሩ ሰልፍ ጸረ-ትግራይ ብቻ ሳይሆን ደርግ ያዘጋጀው ሰልፍ ነው እስከማለት የደረሰ ድፍረት ፈጽመዋል፡፡ ይህ ሴራና የለውጥ አደናቃፊነት ተግባራቸው ይቆይ ይሆናል እንጂ ራሳቸውን ከተሸሸጉበት የትግራይ ህዝብ ጉያ ውስጥ አውጥቶ ሜዳ ላይ በመጣል በገዛ እጃቸው ባመጡት ጦስ ከባድ ዋጋ እንዲከፍሉበት ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡

# በባህር ዳር የተገለጠው ቀስተ ደመና!!!




በፍቃዱ አባይ

## እንደ መሻገሪያ

በኢትዮጵያ የወጣውን ፀሐይ አብዛኛዎቻችን በጋራ፣ በፍቅርና በኢትዮጵያዊነት እየሞቅነው እንገኛለን:: ከሦስት ወራት ብዙም ባልዘለቀ ቆይታ ያገኘነው ትርፍ በምንም ልኬት የማይመዘንና ከጊዜ መደበኛ ዑደትም ያፈነገጠ ይመስላል:: ዐይናችንን ከድነን የመክፈት ያህል በአገራችን እየታዩ ያሉ ለውጦችና ደስታዎች እኛን ብቻም ሳይሆን ራሱን ጊዜንም ጭምር ሳያምታቱት አልቀረም:: ለ27 ዓመታት በጨለማ ውስጥ ለኖረ ህዝብ ይሄ ደስታና ለውጥ የተአምር ያህል ቢሆንበት ብዙም አያስገርምም:: እንዲያውም አንዳንዶች በሰው ልጆች አቅም የተሠራ አድርገው መቀበል እያቃታቸው ፈጣሪ እየከወነው ያለ ያህል እንዲሰማቸው እያደረጋቸው ነው::

ያም ሆኖ የነጻነትና የለውጥ ሒደቱ የማያስደስታቸውና ሒደቱን በመቀልበስ ወደ ተለመደው የጭቆናና የአራዊትነት ዘመን ለመመለስ የሚሹ ጥቂት ኃይሎች እንደሚኖሩ ሰሞነኛው መንፈራገጣቸው እያሳየን ነው:: ያም ቢሆን ህዝባዊ ተቀባይነት ያላቸውን ለውጦች ያለፉ ታሪኮችንና የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮዎችን ስናይ ይህ መሰሉ ሒደት ቀሰ በቀስ እየከሰመና ጥቅመኞችም ተስፋ ወደ መቁረጡ አልያም ለውጡን ወደ መምሰሉ መግባታቸው እንደማይቀር ያሳያሉ:: ይሄንን ማለት ግን መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆናል ማለት አይሆንም:: የጨለማው ዘመን ተጠቃሚዎችና ፍርፋሪ ለቃሚዎች እስትንፋሳቸው ተዛብቶ አማራጮቻቸው ሁሉ መዘጋታቸውን እስኪያረጋግጡና እጅ የመስጠት የመጨረሻ ግዴታ ውስጥ እስኪገቡ ድረስ መውተርተራቸው እንደማይቆም መረሳት የለበትም::

ለዚህም ነው የለውጡ ጀማሪም፣ የለውጡም አስቀጣይ ህዝብ መሆን የሚኖርበት:: ይህ ሥጋት የገባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ በንግግሮቻቸው መካከል በየጊዜው ይህንን እንዳንዘነጋው የሚያስታውሱን ምክንያት ስላላቸው ነው:: አንዳንድ ጊዜ እነዚህን መሰል ህዝባዊ መነሣሣቶችንና ለውጦችን ህዝብ ነቅቶ ካልጠበቃቸውና ካልተንከባከባቸው ሌሎች አምባገነን ኃይሎች እጃውን አስገብተው ሊቆጣጠሩትና ሊጠልፉት ስለሚችሉ ነው:: ዕድሉን በአግባቡ ያልያዘና ያልመራ ህዝብ ደግሞ በጨቋኞች መዳፍ ዳግም ከገባ ቀሪውን ዘመናቱን በሰቆቃ የማሳለፍና ከሰው በታች ሆኖ ዳግም ለመኖር ይገደዳል:: በዚህ አገራዊ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ነው በባህር ዳር የወጣውን ቀስተ ደመና የምቃኘው::



ባህር ዳር ስታዲየም

## ሰኔ 24 ቀን፣ 2010 ዓ.ም.

“ዴሞክራሲን እናበርታ፤ ለውጥን እንደግፍ!!” በሚል መርህ ሥር በአዲስ አበባ ከተካሔደው የምስጋናና የድጋፍ ሰልፍ አንድ ሳምንት በኋላ የሁላችንም ቀልብ የአማራ ህዝቦች ብሔራዊ ክልል መዲና ወደ ሆነችው ባህር ዳር ዞሮአል:: የመስቀል አደባባዩ የቦምብ ጥቃት ሙከራ ተረት አድርጎን አስቀርቶን ቢሆን ኖሮ በኢትዮጵያችን ምን ሊከተል ይችል እንደነበር መሳ ምታዊ አስተያየቶችን

እያስቀመጥን የሳምንቱ ባለተራ የሆነችውን ባህር ዳር ትዕይንተ ህዝብ አሻግረን ከማየት አልፈን በውቢቷ ከተማ የተገኘንበት ዕለት ነበር:: የክልሉ መንግሥትና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደሮች ከሰልፉ ቀደም ብሎ በደረሳቸው ጥቆማ መሠረት ለሰላማዊ ሰልፉ ሥጋት የሆኑ ቁሳቁሶች እንዳይገቡ፣ የሰልፉን ዓላማ የሚያበላሹ መልእክቶችን ያዘሉ ህትመቶች ወደ ከተማው እንዳይገቡ ማሳሰቢያዎችን በተለያዩ የመገናኛ አማራጮች ከመስጠትም አልፈው በጋራ ጥብቅ የጸጥታ ቁጥጥር በአዋሳኝ ከተሞች ጭምር የሚያደርጉበት ዕለት ነበር፤ ቅዳሜ ሰኔ 24 ቀን 2010 ዓ.ም::

ከአዲስ አበባ እስከ ባህር ዳር ተጉዘን ወደ ከተማዋ እስክንደርስ ድረስ ባለፍንባቸው ሌሎች የክልሉ ከተሞች ሁሉ የነበሩት ድባቦች በጣም የተለዩና የማንንም ቀልብ ለመሳብ ጉልበት የነበራቸው ነበሩ:: አብዛኛዎቹ የክልሉ ከተሞችም ኮከብ አልባ በሆነው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ባንዲራዎች ተውበው ይታያሉ:: ባጃጆች፣ ሞተር ብስክሌቶች፣ ታክሲዎች፣ ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የህዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች ሳይቀሩ በባንዲራው ተሸልመው ወዲህና ወዲያ ሲሉ ላያቸው በሐበሻ ምድር አንድ ታላቅ ጉዳይ እንዳለ ያሳብቃሉ:: ወደ ባህር ዳር ከተማ ሲዘልቁ ደግሞ ሁኔታው በጣም የተለየ ነበር::

እኛ ባህር ዳር ከተማ በገባንበት ምሽት በከተማዋ ያሉ ሁሉም የግል፣ የድርጅት፣ የመንግሥት መኪናዎች የከተማዋን አውራ ጎዳናዎች በሰልፍና በሆታ አስጨንቀውታል:: በባንዲራ የተሸለሙ፣ የተለያዩ ባነሮችን የለጠፉ፣ በወጣቶች ጭፈራ የደመቁና ከአናታቸው ላይ ሳይቀር በርካታ ወጣቶችን የተሸከሙ መኪናዎች በመኪና ጥሩንባ ድምጽ ከተማዋን አሳብደዋታል:: የተቀረው ነዋሪ ደግሞ የመንገዶቹን ግራና ቀኝ ይዞ በጭፈራ ድጋፉን ይገልጣል፤ ደስታውን ያበራል:: ሁኔታውን ልብ ብሎ ላየው የነዋሪው ደስታ ነገን የናፈቀ ብቻ አይመስልም፤ ይልቁንም ድል ያደረገ የስፖርት ቡድን አልያም ተወዳጅ ፖለቲከኛ ወደ ከተማዋ ሲገባ አቀባበል እያደረጉ ያሉ ይመስላሉ:: ምክንያቱንም ነገ ይርቃቸዋልና?

ነገሩ ወዲህ ነው:: በርካቶች የሞቱበት፣ በርካቶች የቆሰሉበት፣ በርካቶች የተሰደዱበት፣ ነዋሪውም በከፍተኛ ቁዘማ ለዓመታት አንገቱን ደፍቶ የኖረበት ዘመን ማለፉን ለማመን ከመቸገር የመጣ ደስታ ነው በዋዜማው በባህር ዳር የሆነው:: ነገር ግን ይህንን ሆታና ደስታ ለመቆጣጠር በሚመስል መልኩ በከተማዋ አስተዳደር መብራት እንዲጠፋ መደረጉ እንዲሁም ወቅቱን የሚዋጀው ዝናብ በእኩል ሰዓት መገጣጠም ነዋሪውን በጎዳናዎቹ ላይ ብዙም እንዳይቆምና በቶሎ እንዲበተን አስገደደው::

## ባህር ዳር ነጋለት!!!

በሰንበት ማለዳ የባህር ዳር ነዋሪዎች በቡድን፣ በቡድን እየሆኑ በጎዳናዎቿ ላይ ፈሰሱ:: በሁሉም አቅጣጫዎች በደስታና ሆታ የተመላው የከተማዋና የአካባቢው ነዋሪዎች ሰልፍ ማዕበል ይመስል ነበር:: ቀዝቃዛ የነበረውን የማለዳ አየርም የተለያዩ መፈክሮች፣ ባህላዊ ጭፈራዎች፣ የጥሩንባ ድምጾች ዋጡት:: ልሙጥ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ባንዲራ በነጻ የታደለ ይመስል በሁሉም እጆች እጅ ተውለበለበ:: ባንዲራው በቀሚስ መልክ ተሰፍቶ እንስቶች ለበሱት፣ ወጣቶች እንደ ሽሚዝ አሰፍተው አማሩበት:: የጎረቤት አገር ኤርትራን ባንዲራም ጭምር ደመቁበት:: ነገሩ እንዲህ በቃላት የሚገለጽ አይደለም:: ስሜቱን ለመረዳት በአካል መገኘት ያስፈልጋል:: ሁሉም እግሮች ወደ ባህርዳር ስታዲየም ተመሙ:: ስታዲየሙም መሸከም የሚችለውን የሰው ቁጥር አስተናገደ:: ሆኖም ከስታዲየሙ ውጭ የነበረው ህዝብ በስታዲየሙ ከታደመው ህዝብ ጋር ይስተካከል ነበር:: በዚያም የተለየው ነገር ሁሉ መፈጸም ያዘ::

## ተነቅሎ የተወረወረ ቦምብ

በደስታና በሆታ በታጀበው የድጋፍ ሰልፍ ላይ ለታደሙትና በመገናኛ ብዙኃን ሰልፉን ለተከታተሉ በሙሉ፤ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በአቶ ገዱ አንዳርጋቸው የተደረገው ንግግር ያልተጠበቀ ነበር ማለት ይቻላል:: የክልሉ ነዋሪ ካሳለፈው መከራ አንጻርና ለሹመኞቹ ከነበረው ግምትና እምነት አንጻር አቶ ገዱ ያደረጉት ንግግር ተአምር ሆኖባቸዋል:: ይህንን ንግግራቸውን ማመን ያልቻሉ የከተማዋ ነዋሪዎች የተቀረጸውን ንፋስ ድምጽ ዛሬም ድረስ ደጋግመው እየሰሙት ነው:: ለምን ቢባል ይህ በባህር ዳር እንደሚሆን ማን ይጠብቅ ነበር? ማንም::

በራስ መተማመን ከተሞላበት መንፈስ ጋር በተደረገው የአቶ ገዱ ንግግር የተላለፈው መልዕክት ባልተጠበቀ ሰዓት ተነቅሎ የተወረወረ ቦንብ ያህል አስደንጋጭ ነበር:: ይህ የሁሉም ስሜት ቢሆንም፣ የአቶ ገዱ ንግግር በርካቶችንም አስለቅሷል:: በስታዲየሙ የነበሩ ታዳምያን በየንግግሮቻቸው ጣልቃ ሲቃ ሲተናነቃቸው፣ ዕንባቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው አሳይቶናል::

የአቶ ገዱ ንግግር ቦምብ የሆነባቸው ለደጋፊዎቻቸው ብቻም አልነበረም፤ ትዕይንተ ህዝቡን በጥርጣሬ ለሚመለከቱትና አሁንም ድረስ ለውጡን ለመቀበል ለቸገራቸው ወገኖችም ጭምር ነበር:: ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ የድፍረት ልክ፣ በዚህ የራስ መተማመን ከፍታ ላይ ሆነው ያደረጉት ንግግር በዚያኛው ወገን ይበልጥ ጥርስ እንዳስነከሰባቸውም በማግሥቱ በተካሔዱ የውስጥ ስብሰባዎች በተነሡ ሐሳቦች መነሻነት ለመረዳት ችያለሁ:: ልዩነቱ የአቶ ገዱ ንግግር ለአንደኛው ወገን የደስታን ሲቃና ያለማመንን ገጽ ሲያበረክት፤ በሌላኛው ወገን ደግሞ ቦምቡ አስለቃሽ ጭስን ያካተተ እና ዓይንን የሚቆረቁር ጭስን ያስከተለ መሆኑ ነው:: ባህር ዳር ግን በታሪኳ ዐይታው በማታውቀው የደስታ ባህር ውስጥ መስፈፏ እርግጥ ነው::

## የሄሊኮፍተሯ ጉዳይ?

በዕለቱ በስታድየሙ የታደመው ህዝብ ያልጠበቀው እንግዳ ከአየር ላይ መጣበት:: ባለቡኒ ቀለሟና ወገቧ ላይ ቀይ መቀነት የታጠቀችው ሄሊኮፍተር ልክ በስታድየሙ እንደታደመው ህዝብ ሁሉ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራዋን እያውለበለበች ስተከሰት ሌላ ደስታ፣ ሌላ መደነቅ ተደመረ:: እየዞረች ቄጤማ ጎዝጉዛ፣ ስታድየሙን ለሞላው ታዳሚ ተደጋጋሚ ሰላምታ ሰጥታ ለመውረድ ብታኮበኩብም ሜዳውን ያጥለቀለቀው ሰልፈኛ ማረፊያ አሳጥቷት እንድትመለስ አስገደዳት:: ያም ሆኖ ግን የባህር ዳሩን ሰልፈኛ አስደምማና ቀልቡን ገዝታ እብስ አለች:: ያ ትዕይንት አሁን ድረስ ለብዙዎች መነጋገሪያ እንድትሆን አስችሏታል:: ከመከራከሪያ ነጥቦቹ አንዱ ሄሊኮፍተሯ የማነች? የሚለው ነው:: በዚህ ረገድ ባደረግሁት ማጣራት ንብረትነቷ በግል ድርጅት ሥር የሆነች ናት:: ብዙዎች እንደገመቱት የመከላከያ ሠራዊት አልያም የአየር ኃይላችን ንብረት አይደለችም::

## ባለሪከርዱ ቀስተ ደመና

የክልሉ መስተዳደር፣ የከተማዋ ወጣቶች፣ የሰልፉ ደጋፊ ባለሀብቶች፣ የጸጥታ ክፍሉ …ወዘተ የሠሯቸው ሥራዎች በተገቢው የታቀዱና ተገቢው ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን ካሳዩን ሥነ ሥርዓቶች ዋነኛው ባለ 500 ሜትሩ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ ነው:: ባንዲራው ሙሉውን የስታዲየሙን የመሮጫ መም የሸፈነ ሲሆን በዓለም ትልቁ ባንዲራ የመሆን ክብርንም አግኝቷል:: ብዙዎችም የዚህን ባንዲራ ምስል በመላው ዓለም ተቀባብለውታል:: ባህር ዳር በባንዲራ ታሪክ መሥራቷ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስተዳደሩና በአቶ ገዱ ላይ ሌሎች ኃይሎች ጥርስ እንዲነክሱባቸው ካስገደዷቸው ተጨማሪ መግፍኤዎች ውስጥ ባለ ኮከብ ባንዲራ ቀርቶ ሕገ መንግሥቱ ተጥሶ በሀገሪቱ የማይታወቅና በሕግ ያልጸደቀ ባንዲራ በዚህ መልክ መታየቱ ጉዳዩን በጥብቅ እንዲያዩት አስገድዷቸዋል:: ይህንን ቅሬታቸውንም በውስጥ ስብሰባዎች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል:: ቀስተ ደመናው በባህር ዳር ነግሦ ዓለምን ጉድ ሲያስብል ሁኔታው የመርዶ ያህል የሆነባቸውም ጥቂት አይደሉም:: የሆነው ግን ይህ ነው:: ባህር ዳር በዓለም ትልቅ በተባለው ቀስተ ደመናዊ ባንዲራ ምድሯን አለበሰች:: ህዝቡም በደስታ ሰከረ፤ ልክ እንደ ቀስተ ደመናውም አብሮ ደመቀ:: አንዳንዴ ትክክል እንዳልሆኑ እየታወቁ እንኳን ዝም የሚባሉ ሁነቶች አሉ:: ከእነዚህ አስገራሚ ክስተቶች አንዱ የባህርዳሩ ቀስተ ደመና ነው:: ሀገሪቱ በሕገ መንግሥቷ ዘርዝራ ያስቀመጠችውና በዓለም አቀፍ ደረጃ መለያዬ ብላ ያውለበለበችው ባንዲራ፤ መካከሉ ላይ ሰማያዊ መደብና የቢጫ ኮከብ ጨረር መለያ ያለበትን ቢሆንም፣ ከሰኔ 16 ዓ.ም. ጀምሮ ህዝቡ በራሱ ፈቃድ የሕገ መንግሥቱን ባንዲራ የሚመለከተውን አንቀጽ በራሱ ፈቃድ ሽሮታል:: ይህ የሆነው በባህር ዳር ብቻም አይደለም፤ ከአዲስ አበባ እስከ ድሬዳዋ፣ ከወልድያ እስከ ባህር ዳር ነው:: ነቀምት ደግሞ በሌላ ቀለም ሌላ ተጨማሪ ታሪክ አስመዘገባለች:: ለዚህም ነው ለባለ ኮከቡ ባንዲራ ዘብ ቆመናል የሚሉት ኃይሎች ቁጥር እየተመናመነ እንዲመጣ ግድ የሆነው::

## የባህር ዳር ነዋሪ ጨዋ ነው፤

ነዋሪዎቹና ከሌሎች አካባቢዎች የታደሙት ሰልፈኞች የጋራ ሥጋት ነበራቸው:: ይህ ሥጋትም የደህንነት ሥጋት ነው:: አዲስ አበባ የቀመሰችው ጉዳት ዳግም በባህር ዳር እንዳይከሰት ሁሉም በጋራ ሠግቷል:: ከሥጋት ባለፈ ግን ሁሉም ለሰላም መከበርና ለሰልፉ በሰላም መጠናቀቅ እኩል በህብረት ቆሟል:: ከአስተዳሩና ከጸጥታ ክፍሉ ባሻገርም እያንዳንዱ ተሰላፊ ሰላሙን ለመጠበቅ ታትሯል:: ወደ ስታዲየሙ እንዳይገቡ የተከለከሉ አልባሳትና ቁሳቁሶች ማንም ሳይጠብቃቸው ሰልፈኛው ወደ ስታዲየም ሲገባ ያስቀመጣቸውን ንብረቶቹን በቦታቸው ያለ ችግር አግኝቷቸዋል:: ወደየቤቱ ሲመለስም በታላቅ ሥነ ሥርዓትና መተሳሰብ ነበር:: ለዚህም ነው ሰልፉ ያለምንም እንከን የተካሄደው:: በዚህም ሰልፈኛው ጨዋነቱን በሚገባ አስመስክሯል::



ታዬ ንጉሴ (ዶ/ር)

# የተፈራው የ'ቀለም አብዮት' በ'ቢራቢሮ አብዮት' ሲተካ




የቀድሞው የ'ኢትዮጵያ' ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ (ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል በነጠላ ትምዕርተ ጥቅስ ያስገባሁት ኢትዮጵያን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ከልባቸው ሳይወዱና ሳያምኑበት በድንገት እንደሚመሯት የተገደዱባት ሀገር ስለሆነች ነው::) በምስራቅ አውሮፓ የአምባገነን መንግሥታትን የጠራረገውን ሰላማዊ የህዝብ ዓመፅ ኢትዮጵያ ውስጥ በምንም ዓይነት እንደማይካሄድና ቢካሄድም በፍፁም እንደማይሳካ የቀለም አብዮት እያሉ ሲያናንቁትና ሲያጣጥሉት ነበር:: ያ ሲያጣጥሉት የነበረው ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ ትንሽ መልኩን ቀይሮ ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄዱ አይቀሬ ሆኗል:: በሌሎቹ ሀገሮች ህዝባዊ አመፆቹ በዋናነት የተካሄዱት በየሀገሮቹ ርዕሰ ከተማዎች ነዋሪዎች ሲሆን፤ የወቅቱ የኢትዮጵያውያን አመፅ ግን ከዋናው ከተማ ከአዲስ አበባ ወጣ ባሉ መካከለኛና ትንንሽ ከተሞች የተካሄደ እንቅስቃሴ ነው::

ሌላው የኢትዮጵያውያን ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ፤ ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው ሀገሮች (የቀለም አብዮት ከተካሄደባቸው) ለየት የሚያደርገው ባህርይ አለው:: ምንም እንኳን እምቢተኝነቱ በሰፊው ህዝብ የተቀሰቀሰ ቢሆንም፣ የንቅናቄው ግለት በህወሓት ፊታውራሪነት የሚመራውን የኢህአዴግን ዘውጋዊ የፖለቲካ ቡድኖች ሰነጣጥቆ የተወሰኑ መሪዎችን ከህዝብ ጎን እንዲሰለፉ ያስገደደ ክስተት መሆኑ ለየት ያለ ባህርይ እንዲጎናፀፍ አድርጎታል::

በመጨረሻም እንደታዘብነው አመፁን ተከትሎ በተካሄደው የገዥው ፓርቲ ሹም ሽር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን ወደ ጠ/ሚኒስትርነት አምጥቶ ባልተጠበቀና ባልታሰበ መልኩ የለውጡ መሪ ሆነው የህዝቡን ብሶትና ጥያቄ ለመመለስ ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛሉ::

ጠ/ሚ ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እየወሰዷቸው ያሉት እርምጃዎች መሠረታዊና ሥር ነቀል በመሆናቸው "የውስጥ አብዮት" ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ▶

ይህንንም የውስጥ አብዮት የቢራቢሮ አብዮት ብዬ ለመጥራት እደፍራለሁ::

የቢራቢሮን የተፈጥሮ ውልደት ልብ ብለን ካየን አስቀያሚና ምድር ለምድር እየተጎተተ የሚሄደው አባ ጨጓሬ፤ አርጅቶ መንቀሳቀስ ሲያቅተው ከውስጡ ውብ የሆነችው ቢራቢሮ በክንፏ ያረጀውን የአባ ጨጓሬ ቅርፊት ሰባብራ በመውጣት በሰማይ ላይ መብረር ትጀምራለች::

ጠ/ሚ ዐቢይን በዚች ቢራቢሮ ስመስላቸው፤ በህወሓት ፊታውራሪነት የሚመራውን፣ ያረጀውንና ያረጠውን ኢህአዴግ በአባ ጨጓሬ እመስለዋለሁ:: እናም "የቢራቢሮ አብዮት" ብዬ የምጠራው በጠ/ሚኒስትሩ አመራር እየተካሄደ ያለውን መሠረታዊ የለውጥ እርምጃና እንቅስቃሴ ነው:: አቶ መለስ የፈራው የ'ቀለም አብዮት' በ'ቢራቢሮው አብዮት' ተተካ ይሏል ነው::

## የ"ቢራቢሮው አብዮት" አዲስ ርዕዮተ ዓለም

ህወሓት/ኢህአዴግ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ርዕዮተ ዓለሜን ይወክልልኛል ብሎ እንደ ቀኖና ሲያነበንበው የሰነበተውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ፤ በግልፅ እንዲህ ማለት ነው ብሎ በቀላሉና በሚገባ ቋንቋ ያስቀመጠበት ጊዜ ያለ አልመሰለኝም:: ይህም የሆነበት በውስጡ ክፋት፣ ተንኮልና ማጭበርበር ስላለበት ለህዝብ በሚገባ መልኩ ማስቀመጥ ስለሚያዳግተው ይመስለኛል::

ላለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት ድርጅቱ ኢትዮጵያን በገዥነት ሲያስተዳድር እንደተረዳነው፤ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዋና መገለጫዎች፤ ጎሰኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ጥላቻ፣ ቂም በቀል፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ውሸት፣ መከፋፈል ወይም ፀረ አንድነት መሆናቸውን በተግባር ስንኖረው ከርመናል::

ይህንን ፋሽስታዊ ርዕዮተ ዓለም ሲያካሄዱ የተለያየ መሸፋፈኛና ማስመሰያ ምክንያቶች ተደርድረዋል:: ከነዚህም ውስጥ የብሔር ጭቆናና የማንነት ጭቆና የሚባሉት በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው:: ከዚህ በተፃራሪ በጠ/ሚ ዐቢይ የሚመራው አዲሱ የለውጥ ጉዞ (የቢራቢሮው አብዮት) የሚያቀነቅነው ፍቅርን፣ መቻቻልን፣ ወንድማማችነትን፣ ህብረትን፣ አንድነትን፣ ይቅር ባይነትን፣ ፀረ-ዘረኝነትንና ፀረ-ሌብነትን ነው::

የዚህ ርዕዮተ ዓለም መሰረታዊ እሳቤ ሰብዓዊነት ሲሆን፤ ሰዎች ያለምንም ውጫዊ ማንነታቸው (ሃይማኖት፣ ጎሳ፣ ዘር፣ … ወዘተ) በሰውነታቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ልንቀበላቸውና ልናከብራቸው ይገባል የሚል ነው:: የግለሰቡ ፈጣሪ የለገሰውን ነፃነትና ሉዐላዊነት እውቅና ይሰጣል ማለት ነው:: በዚህም መሰረት የመንጋውን ወይም የቡድኑን ህልውና ብቻ ከሚቀበለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም በተፃራሪ ያስቀምጠዋል:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግለሰቡን የማያስብ ዝም ብሎ ተነጂ እንስሳ አድርጎ እንደሚመለከተው ልብ ልንል ይገባል::

አዲሱን ርዕዮተ ዓለም በህብረተሰብ ውስጥ ለማስረፅ ጠ/ሚ ዐቢይ ሁለት የተለያዩ ስልቶችን ጥቅም ላይ ሲያውል ይስተዋላል:: የመጀመሪያው ስልት ወደ ህብረተሰቡ ወረድ ብሎ በመወያየት፣ በመመካከር፣ በመደማመጥ ህብረተሰቡን ማነቃቃትና ለለውጥ መቀስቀስ ነው:: በተግባር እንዳየነው ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ማግሥት ጀምሮ ይህን ሥራ ያለመታከት በቁርጠኝነት በመወጣት ላይ ይገኛሉ::

በተለያዩ ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የሚያደርጉትን ንግግር ይዘት ጠለቅ ብለን ስንመረምረው፤ የይቅር ባይነት፣ የአንድነት፣ የአብሮነት፣ የፍቅርና የነፃነት መልዕክቶች ጎላ ብለው ይታያሉ::

ሁለተኛው የለውጥ ስልት ደግሞ ተቋማዊ ለውጥ ነው:: ይህን ተቋማዊ ለውጥ በሁለት ክፍሎች ማየት ይገባል::

አንደኛው፣ ህወሓት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማስረዘም በተለያዩ ጊዜያት (በተለይም ከ1997ቱ ታሪካዊ ምርጫ በኋላ) ህዝቡን ለማፈን ያወጣቸውን ቀፍዳጅና ፋሽስታዊ ሕጎች፣ ደንቦችና አዋጆች የማንሣት ጉዳይ ይሆናል::

በእስካሁኑ የጠ/ሚ ዐቢይ የለውጥ እንቅስቃሴ እንዲነሣ የተደረገው፣ በቅርብ ጊዜ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብቻ ነው:: ሌሎቹ፣ ለምሳሌ፡- የፀረ ሽብር፣ የፕሬስ፣ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎች አፋኝ ሕጎች ገና እንዳሉ ናቸው:: አሁን እነሱን ለመለወጥ እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: በቅርብ በሚዲያ የሕግና የፍትሕ ጉዳይን የሚመረምር ግብረ ኃይል እንደተቋቋመ ይፋ ተደርጓል::

በሁለተኛው የተቋማዊ ለውጥ ውስጥ የማካትታቸው፤ ቁልፍ በሆኑ የመንግሥት ተቋማት ማለትም እንደ ባንክ፣ ደህንነት፣ መከላከያና ሚዲያና የመሳሰሉትን የሚመሩትን የህወሓትና የግብረ አበሮቹን ባለስልጣናት የመተካት ሂደት የሚመለከት ሲሆን፤ በዚህም የጠ/ሚኒስትሩ የለውጥ እንቅስቃሴ አነቃቂና አበረታች ይመስላል:: ሆኖም፣ ምንም እንኳን የእነዚህን ተቋማት ሓላፊዎችን ቢለውጡም፤ የህወሓትን የበላይነት በማራመድ የሚጠቀሙበትን የአሠራር ስልት ግን ሙሉ ለሙሉ ቀይረዋል ማለት አይደለም::

ለምሳሌ ያህልም፡- በኢትዮጵያ ቴሌቭዥርን የዜና እወጃ ሰዓት የሚሰማው "የብዝኃነትና የህዳሴ ድምፅ" የሚል የሕወሐት መፈክር ለዚህ ማሳያ ነው:: መሆን ያለበት "የአንድነትና የመደመር ድምፅ" ነው::

ከዚህ በመነሣት፣ "የህወሓት ፖለቲካ፣ የቅኔ ፖለቲካ ነው" የሚል እምነት አለኝ:: ያም ማለት ሁልጊዜ ህወሓት የሚቀምራቸው የፖለቲካ ሐረጎች ሰምና ወርቅ አላቸው::

ሰሙ፡- ከላይ ያለው ፍቺ ሲሆን ይህ ጣፋጭ የሆነና የሁሉንም ልብ የሚያማልል ነው::

ዋናው መልዕክቱ ያለው ወርቁ ላይ ነው:: "ብዝኃነት" የሚለው የተለመደውን "የክፍፍል፣ የልዩነት እና የጥላቻ አስተሳሰብ ሲያመለክት፤ "ህዳሴ" የሚለው ቃል ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገዢው ፓርቲ በከፍተኛ ደረጃ በህዝብ ያጣዉን የቅቡልነት ኪሳራ ለመሸፋፈን የፈበረከው (legitimacy crisis) ነው::

ይህ "ሎጎ" በምንም መልኩ ከጠ/ሚ ዐቢይ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የይቅር ባይነትና የህብረት ርዕዮተ ዓለም ጋር አይሄድም::

## የቢራቢሮው አብዮት ታላቅ ተግዳሮት

በሰኔ 25፣ 2014 (እ.ኤ.አ) "አዲስ ስታንዳርድ" በተባለ መጽሔት ላይ "A Tale of Two Federations" በሚል የጻፍሁት መጣጥፍ፤ ኢትዮ ምህዳር በሚባል ጋዜጣ ላይ "የሁለት ፌዴሬሽኖች ወግ" በሚል ተተርጉሞ ለህዝብ ቀርቧል::

የመጣጥፉ ዋና ጭብጥ ያሁኑን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ሕገ መንግሥት ጋር በማወዳደር የሚገርምና የሚደንቅ መመሳሰል እንዳላቸው የሚያሳይ ነው::

በመደምደሚያውም ላይ፤ ሁለቱም ከሞላ ጎደል አንድ አይነት የሆኑና የአፓርታይድ ወይም የከፋፍለህ ግዛ አገዛዝ የሚከተሉ ሲሆኑ፤ ልዩነቱ የደቡብ አፍሪካው የዘር አፓርታይድ፤ የኢትዮጵያው (የህወሓቱ) የጎሳ ወይም የዘውጌ አፓርታይድ መሆኑ ብቻ ነው::

ይህ ንድፈ ሐሳብ አሁን አሁን በአንዳንድ ሚዲያዎች እየተንፀባረቀ መሆኑን ተረድቻለሁ:: በህገ መንግሥቱ ጎልተው ከሚታዩ ህፀፆች መካከል የመክፈቻውን ሐረግ እንመልከት:: "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች…" በማለት የሚጀምረው ሐረግ በራሱ ብዙ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለ:: አንደኛው የኢትዮጵያ ህዝቦችን በደም የተሳሰረ ታሪካዊ አንድነትን አጣጥሎ ተራ ወደሆነ የሕዝቦች አርቲፊሻል ድምር ያወርደዋል:: ሁለተኛ እነዚህ "ብሔር፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች" የሚላቸው ሐረጎች በግልጽ ያልተረጎማቸው ከመሆኑ በተጨማሪ "ማን ብሔር?"፤ "ማን ብሔረሰብ?"፤ "ማን ሕዝብ?" እንደሆነ በፍፁም አላመለከተም:: በራሱ "ብሔር"፣ "ብሔረሰብ" እና "ሕዝብ" ብሎ በሦስት ተዋረድ መከፋፈሉ የሕዝቦች ዕኩልነት እያለ ከሚጮህበት ዜማ ጋር በቀጥታ ይላተማል:: እዚህ ላይ የሕገ መንግሥቱ አንድምታ የሚያሳየው የሀገሪቷ ባለቤቶች ዜጎች ሳይሆኑ እነዚህ በግልፅ ያልተመላከቱ ምናባዊ ስብስቦች መሆናቸውን ነው::

በአጠቃላይ አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ህወሓት የራሱን የፖለቲካ ፕሮግራም ሕገ መንግሥት የሚል ቅርጽ ሠጥቶ በህዝብ ላይ የጫነው ሠነድ መሆኑን ብዙዎች ጠንከር ባለ የመከራከሪያ ሀሳብ በተደጋጋሚ የጻፉበት መሆኑን ላስታውስ እወዳለሁ::

ዋናው ነጥብ፤ ጠ/ሚ ዐቢይ እያራመዱት ያለው የፍቅር፣ የአንድነትና የህብረት ርዕዮተ ዓለም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ታስቦ ከተዘጋጀው ከዚህ ከፋፋይ ሕገ መንግሥት ጋር መሠረታዊ ቅራኔ ስላለው ሕገ መንግሥቱ የግድ መሻሻል አለበት:: ይህ ካልሆነ አሁን ተጀመረው ኢትዮጵያን የማዳን የለውጥ እንቅስቃሴ በፍፁም ከግቡ ሊደርስ አይችልም::

ስለሆነም የጠ/ሚ ዐቢይ መንግሥት ቅድሚያ ሰጥቶ ሊተገብረው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር፣ የሕገ መንግሥት አሻሻይ (ከላሽ) ኮሚሽን ከተለያዩ የፖለቲካ ሰዎች፣ ከባለሙያዎች፣ ከሲቪክ ተቋማት፣ ከሀገር ሽማግሌዎች …ወዘተ አውጣጥቶ በማቋቋም አሁን ያለውን ሕገ መንግሥት ከአዲሱ የአንድነት፣ የፍቅር፣ የህብረትና ኢትዮጵያን የማዳን ርዕዮተ ዓለም ጋር በሚጣጣም መልኩ አርቅቆ ህዝቡ በሰፊው እንዲወያይበት መደረግ ይኖርበታል::

ይህ አዲስ ሕገ መንግሥት በሕዝብ ውይይት ዳብሮና ተደግፎ ለአዲሱ መንግሥት መቋቋም መሠረት መጣል አለበት::

ይህ ሳይሆን ቀርቶ በዚያው በድሮው የአፓርታይድ ሕገ መንግሥት፤ ከሁለት ዓመት በኋላ ምርጫ አካሂደን አዲስ መንግሥት እንመስርት የሚለው ዝንባሌ ብዙ የሚያራምድ አይመስለኝም::

እውነተኛዋን፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያ መልሰን ለማቅናት ከሕገ መንግሥት መጀመር የግድ ይሆናል:: ይህ ካልሆነ አዲስ ወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ እንደመጨመር እንዳይሆንብን ያሠጋል::

---

*ታዬ ንጉሤ (ዶ/ር)*
*በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሺዮሎጂ መምህር ናቸው::*

*ባለፈው እሑድ፣ በባህር ዳር በተደረገው የድጋፍ ሰልፍ፤ የብአዴን ሊቀመንበርና ምክትል ጠቅላይ ሚ/ር አቶ ደመቀ መኮንን፣ የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፤ እንዲሁም ብ/ጄኔራል አሳምነው ጽጌ እና ወ/ሮ እማዋይሽ ዘውዱ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ንግግሮች አድርገዋል፡፡ ከንግግሮቻቸው መካከልም ወቅታዊና አንኳር፣ አንኳር የሆኑትን መርጠን እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል፡፡*

# "የተቀጣጠለው ለውጥ ወደኋላ መመለስ ቀርቶ ማዝገምን አይታገሥም"

*ም/ጠ/ሚ/ር አቶ ደመቀ መኮንን*



-ይህ ታሪካዊ ቀን ቀጣዩን ጊዜ የተሻለ እና ክልላችንን እና ሀገራችንን ተመራጭ የሰላምና የልማት ምድር ለማድረግ ብሩህ ዕለት የወገገበት ነው:: ለዚህ ዕለት ዕውን መሆን በየፈርጁ የታገሉ፣ የደሙና የቆሰሉ፣ ከዚያም አልፎ ክቡር ሕይወታቸውን የሠው በዚህ አደባባይ ክብርና ሞገስ ለእነሱ ይሁን::

-የዛሬው የምስጋናና የድጋፍ ትዕይንት የአደራና የብርታት ስንቅ ነው:: አደራው የሁሉም፤ አቅሙም የጋራ ነው:: ይህን ለውጥ ከዳር ለማድረስ ስንበረታ፣ ተመካክረንና ተግሳፃችሁን ሰምተን ልንታረምና ልናገለግላችሁ ቃል የምንገባበት መድረክም ነው::

-ለውጡን በሚጠበቀው ከፍታ ለማስቀጠል በየደረጃው ያለን መሪዎች ካለፈው ጉድለታችን ተምረን ቃላችንን ለማደስና ህዝባችንን ለመካስ ከፊታችሁ ቆመናል:: ንቅናቄው ጥቂቶች የሚዘውሩት ሳይሆን፤ ሁሉም በባለቤትነት ሊተውንበት የሚገባ ነው::

-ብዕራችሁ የተባ፣ አዕምሯችሁ የሰላ እንዲሁም ተሳትፏችሁ ደግሞ የነቃ እንዲሆን ዘመኑ ራሱ ይጠይቃል:: መንግሥት ይሄ ድባብ እንዲፈጠር አቅሙ የፈቀደውን ጠጠር መወርወር እንጂ የዜጎች ባላጋራና የዲሞክራሲ ሥርዓት ደንቃራ መሆን አይገባውም::

-ከዚህ በኋላ ፀረ-ዴሞክራሲ በቃ ብለናል፤ እያንዳንዱን ድርጊታችንና ሥራችንን በንቃት ተከታተሉ:: አካሄዳችንና ሁኔታችን ከዴሞክራሲ ያፈነገጠና የዜጎችን መብት የሚጋፋ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ልትታገሉን እና አደብ ልታስገዙን ይገባል::

በዚህ አያያዝ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው፤ በነፃነት የሚያስቡባት፣ በነፃነት የሚፅፉባት፣ ያለ ገደብ የሚመረጡባትና የሚመርጡባት፣ የዴሞክራሲና የፍትሕ ሥርዓትን የሚመሩና የሚያስተባብሩ የጋራ ተቋማት የተገነቡባት፤ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ባለቤት ይሆናሉ::

-ይህ የህዝብ ጎርፍ፣ ኢትዮጵያን የዳበረና የተረጋጋ ዴሞክራሲ ባለቤት የሆነች አገር የማድረግ ጉዞ ነው:: ነገር ግን፣ ዴሞክራሲ እንደፈለግን እንድንሮጥ እንደሚያስችለን ሁሉ ልጓምንም ያበጃል:: ልጓሙ የየግል ሩጫችንን በሕግ ጥበቃ የተበጀላቸውን የሌሎች ዜጎችን መብቶች እንዳይጋፋ ሲባል የተበጀ ነው::

-አሁን የተጀመረው የለውጥ ማዕበል ካለፈው ጉድለት ተምሮ በፅናት መጓዝን ይጠይቃል:: ይህን የለውጥ ማዕበል በሙሉ ልብ ተቀብሎ ድርሻን መወጣት የግድ ይላል:: ከዚህ ውጭ በእኔ አውቅልሃለሁ ፈሊጥ መንታ መንገድ መወጠን አይቻልም:: መፍትሔው የህዝብን የለውጥ ፍላጎት አድምጦ ከእሱ ጋር በመሰለፍ ለውጡን በትክክለኛ አቅጣጫ መምራት ብቻ ነው::

-ኢትዮጵያ፣ አንዳንዶቻችን የቅንጦት ሕይወት የምንገፋባት እና እንዳሻችን የምንፈነጭባት፤ ሌሎቻችን ደግሞ ባይተዋር የምንሆንባት ሀገር መሆን የለባትም:: እናም በእናት አገርና በጋራ ጎጇችን በእኩልነትና በፍቅር እንኖራለን::

ሀገራችን በተያያዘችው የለውጥ መንፈስ አስቀድመው ለተፈፀሙ እኩይ ታሪኮች ዳግም እንዳይፈፀሙ ትምህርት ወስደንባቸው፤ አዲስ ታሪክ ለመሥራት ደግሞ የተለኮሰውን መነሣሣት ሂደቱን በአግባቡ ልንመራውና ልንገራው ይገባል:: በዚህ አጋጣሚ እኔና ባልደረቦቼ፤ ክልላችንና ኢትዮጵያን የተረጋጋና የዳበረ ዴሞክራሲ ባለቤት የማድረግ የቤት ሥራን ዳር ለማድረስ ከህዝባችን ጋር በመሆን በፅናት እንደምንዘልቅ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ::

በታሪካችን አንዳችን በሌላችን ላይ ተነሥተናል:: ሲከፋም ቃታ ስበን አንዳችን የሌላችንን አካል አቁስለናል፤ አጉድለናል:: ምንም እንኳን ትናንት የተከሰቱ መጥፎ ታሪኮችን መዘንጋት ሰዋዊው የማስታወስ ችሎታችን የማይፈቅድልን ቢሆንም፤ ለወደፊት የጋራ ጥቅምና ጉዞ ሲባል ሆን ተብሎ እኩይ ትዝታዎችን መቀየር በእጅጉ ያስፈልጋል::

-በሚሊዮኖች ተደግፎ የተቀጣጠለው ለውጥ ወደ ኋላ መመለስ ቀርቶ ማዝገምን አይታገሥም:: መፍትሔው በህዝብ ባለቤትነት እና በወጣቱ መሪነት በፍጥነት መጓዝ ነው:: ካሁን በኋላ ሀገራችን ለሁሉም በእኩል የተመቸች፤ ዜጎቿ እኩል የሚደመጡባት፤ እኩል የሚሳተፉባት የጋራ ማዕዳችን ሆና ትቀጥላለች:: ለዚህ እውን መሆን በፅናት መታገል ይኖርብናል:: ከዚህ አኳያ የሥራ ባልደረቦቼ እና እኔ፤ ቴዎድሮስና ገብርዬ ሆነን ተጋግዘን፤ አለቃ እና ምንዝር ሳንሆን፤ የአንድ ዓላማ ተሰላፊዎች በመሆን የህዝባችንን የሰላም፤ የዴሞክራሲ እና የልማት ፍላጎት ዳር እናደርሳለን::

-እርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ ከእንግዲህ እንደማንሣሣት ሳይሆን እንደምናደምጣችሁ፤ እንደከዚህ ቀደሙ ዘግይተን ሳይሆን ፈጥነን እንደምንመልስላችሁ እና በዚያው ፍጥነት እንደምንስተካከል ነው:: ምስጋናችሁን ብቻ ሳይሆን ተግሳፃችሁን ከልብ ሰምተን ፈጥነን ለመታረም ዝግጁ መሆናችንን በልበ ሙሉነት አረጋግጥላችኋለሁ::

-በዚህ አጋጣሚ ብአዴን፤ በአማራው ስም በውጭ አገር የተደራጁና ለሱ የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ማህበራዊ የሚዲያ ተቋማት በሰላም ለመንቀሳቀስ እስከወሰኑ ድረስ ወደ ክልላችን መጥተው እንዲቀሳቀሱ ጥሪ እያስተላለፈ እኛም ግማሽ መንገድ ድረስ ተጉዘን፤ ለህዝባችን ጥቅም መከበር አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆናችንን አረጋግጣለሁ:: ▶

# ስንደመር ብረትን ማቅለጥ እንደምንችል አይተናል

## ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው



-ከሁሉ በማስቀደም በሚያለያዩን ጉዳዮች ላይ ጊዜያችንን ማባከኑን ትተን፤ አንድ በሚያደርጉን ጉዳዮች ለመተሳሰር በመፈለግ ቃል ወደምንገባበት የ"መደመር" ቀን፤ ሁላችንንም እንኳን አደረሰን! እንኳን አንድ ሆነን ተገናኘን!

-ሀገራችን ከዓመታት የሰላም እጦት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወጥታ አንፃራዊ ሰላም የሰፈነባትና ህዝቦቿ አንድ መሆን የጀመሩበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። የጥይት ድምፅና ለቅሶ ያደነቁራቸው የነበሩ ከተሞቻችን ሰላምንና ፍቅርን ከፍ አድርገው መዘመር ጀምረዋል። ልጄ እንደወጣ ይቀራል ብለው ሰቀቀን ውስጥ ወድቀው የነበሩ የእናት አንጀቶች በሰላም ማረፍ ጀምረዋል። ይህ ለኛ ለኢትዮጵያውያን የትናንቱን ገናና ታሪካችንንና የነገውን ታላቅ ተስፋችንን ማስተሳሰሪያና ማረጋገጫ ማህተም ነው። የአማራ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር አንድ በመሆን በሀገራችን ጠንካራ መንግሥት እንዲመሰረት፣ ታሪክ እንዳይበላሽና ነፃነት እንዳይገፈፍ፤ ጥንትም ጀምሮ የሠራና የታገለ ጀግና እና ባለ ታሪክ ህዝብ ነው።

-ሀገራችን ከወደቀችበት እንደገና መነሣት ጀመረች እንጂ ገና በቅጡ መራመድ አልተቻላትም። አሁን ያሳየነውን አንድነትና ፍቅር በማይናወጥ መሠረት ላይ አንፀን፤ የኔን፣ የእናንተን፣ የልጆቻችንንና የልጅ ልጆቻችንን እድል ተስፋ እንዲበቅልበት ማድረግ ካልቻልን፤ በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በአጋጣሚ መገኘታችን ትርጉም የለውም። በሥራችን ውጤት ዛሬ እንዲህ አምሮብንና ተውበን ብንታይም ልንሻገራቸው የሚገቡ በርካታ ወንዞችና ሰበርባራ መንገዶች ከፊት ለፊታችን ይጠብቁናል። እንደጀመርነው ሁሉንም እናልፋቸዋለን። ግን ስንቅ ያስፈልገናል። ስንቁም ፍቅር፣ አንድነትና ተስፋ ነው። አንድ ስንሆን የማይደፈሩ መስለው ይታዩ የነበሩ ተራሮችን መናድ እንደምንችል ተምረናል። ስንደመር ብረትን ማቅለጥ እንደምንችል አይተናል። ስንፋቀር በሀገራችን የይቅርታና የምህረት ዝናብ እንደሚዘንብ ተገንዝበናል።

-ዛሬ ሀገራችን ደስታና ፍቅር ብቻ የሚታይበት ሀገር አይደለችም። ሰላም የዋለው ሀገር ሰላም እንዳያድር የሚደክሙ፣ ሽንፈትን ያልተቀበሉ ደካሞች ከዙሪያችን አልጠፉም። ድል መንሻው ዘዴ የታወቀና የተለየ ነው። አንድ መሆን፤ መደመር። ተለያይተን ሞክረነዋል፤ አልተሳካልንም። ተነቃቅፈንና ተጠላልፈን አይተነዋል፤ የጅብ እራት ነው የሆንነው። እናም አንድነትን በጥብቅ እንሻለን። አንድነት የሚጀምረው ከቤት ነው።

-በሀገራችን ወንድማማችነትና እህትማማችነት መሠረቱ ሰፍቶ፤ ታላቅ ታናሹን በተለመደው ኢትዮጵያዊ ባህል እንዲያከብርና ሰላም በሀገራችን እንዲበዛ ተግታችሁ ታስተምሩን ዘንድ እንደልጅነቴ በክብር እጠይቃችኋለሁ።

-ትናንት ለሰላምና ለሰው ልጅ ክብር ያልተመለሰው ብዕራችሁ፤ ዛሬም በምድራችን ፍቅርና መተሳሰብ እንዲሰፍን፣ ዴሞክራሲ እንዲስፋፋ፣ የአማራ ህዝብ ታሪክ እንዳይዛባና እንዳይጠፋ አቅማችሁና የሞያ ደረጃችሁ በሚፈቅደው መጠን ሁሉ ከጐናችን ቆማችሁ እንድንተጋገዝና እንድንደመር ጥሪ አቀርብላችኋለሁ።

-በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የአማራን ህዝብ በልማትና በዴሞክራሲ ተጠቃሚ እናደርጋለን የሚል ሀሳብ ይዛችሁ የምትሠሩ ተፎካካሪ ፖርቲዎች እንዳላችሁ እናውቃለን። ዓላማችሁና ፍላጐታችሁ የአማራን ህዝብ መጥቀም እስከሆነ ድረስ በፍቅር ዓይን እንመለከታችኋለን። ከፊታችን ያሉ ትልልቅ ችግሮችን ተራርቀን በመቆም ልናሸንፋቸው እንደማንችል ተገንዝባችሁ ከሀገር ውጪ ያላችሁ ተመልሳችሁ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያላችሁም ተቀራርበን አንድ በሚያደርጉን ነገሮች ላይ ተመሥርተን አብረን እንሥራ።

- ለክልላችንና ለመላ ኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት እየከፈላችሁት ያላችሁትን ዋጋ አሳምሬ እገነዘባለሁ። ሀገራችን ሰላሟ የተጠበቀና እኩልነት የተረጋገጠባት ሆና እስክትዘልቅ ክንዳችሁ ሳይዝል፣ ነፃና ገለልተኛ ሆናችሁ የሰላም ምልክትነታችሁን መሠረት እንድታስይዙት አሳስባችኋለሁ። ኢትዮጵያ ንፁህ ደም ሳይሆን ፍቅር የሚፈስባት፣ በሥጋት ሳይሆን በራስ መተማመን የተሞሉ ልጆች ያሏት ሀገር ትሆን ዘንድ የጀመራችሁትን ጀግንነት አበርትታችሁ እንድትቀጥሉ ጥሪ ቀርቦላችኋል።

## "ኢትዮጵያ ስትጠፋ ሁላችንም እንጠፋለን፤ ኢትዮጵያ ስትኖር ሁላችንም እንኖራን"

### ብ/ጄኔራል አሳምነው ፅጌ



እንደኔ ለነፃነት ታግላችሁ ይህችን ቀን ለማየት የበቃችሁ የነፃነት አርበኞች፤ በዛሬው ዕለት እናንተ ፊት እንድንቆም፣ ይህችን ቀን በጋራ እንድንጋራት፣ በአማራነታችን እንድንኮራ፣ በኢትዮጵያዊነታችን እንድንፀና፤ በፅናት ለታገላችሁልን ወጣቶች፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ምስጋናችን ይድረሳችሁ:: እዚህ ብቻ ሳይሆን፤ በየትኛውም የሀገራችን አካባባዎች፣ ለኛ ነፃ መውጣት የታገላችሁ ውድ ወንድሞቻችን አሁንም ክብርና ምስጋና ይግባችሁ::

በኢትዮጵያ እስር ቤቶች፣ ፈርዖን በራሔል ላይ ካደረሰው ዘግናኝ በደል ባልተናነሰ እየተፈፀመባት በምትገኝ ሀገር ነፃ በመውጣታችን እጅግ ዕድለኞች ነን:: እስራኤልን ነፃ ያወጣው ሙሴ ነው:: ሙሴ እስራኤልን ነፃ ያወጣው በ40 ዓመቱ ነው:: ዐቢይ ኢትዮጵያን ነፃ ያወጣው በ40 ዓመቱ ነው:: የኢትዮጵያን ነፃነት እየመሩ ያሉት ዐቢይና ወንድሞቹ ናቸው:: ይሄ ሰላም፣ ይሄ ታላቅ ኢትዮጵያዊነት፣ ይሄ ፅናት እንዲቀጥልልን ከልብ እንሻለን::


አሁን የተጀመረው የሰላም የዴሞክራሲ እንዲህ በነፃነት ቆሞ የመናገር መብት በእጅጉ ሥር እንዲሰድ እንታገላለን:: ከአሁን በኋላ በአማራነቱ አንገቱን የሚደፋ፤ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያፍር ኢትዮጵያዊ አይኖርም:: በየትኛውም አጋጣሚ ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት እውነተኛ ህዝባዊ ለውጥ ለማደናቀፍ የሚሞክሩ፤ ጥቅማቸው የተነካባቸው አልያም የሚነካባቸው ካሉ፣ አብረን ለመታገል ዝግጁነታችንን ለማረጋገጥ እንወዳለን::

ኢትዮጵያ ለሁላችንም በቂ ናት:: ኢትዮጵያ ስትጠፋ ሁላችንም እንጠፋለን:: ኢትዮጵያ ስትኖር ሁላችንም እንኖራን::

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ፤ አመሰግናለሁ::

## የሽግግር መንግሥት ልናቋቁም ነው ወይስ በተቀደደልን ቦይ ልንፈስ ነው?"

### ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ



የተከበራችሁ ወገኖቼ፣ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያን እግዚአብሔር እንዲባርካት ደጋግመው እንደጠየቁት ሁሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርዓን ላይ ኢትዮጵያ ተደጋግማ ተጠርታለች:: ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይባርክ!

ዛሬ የመደመርን ቀን ምክንያት በማድረግ፤ ኢትዮጵያዊ ስሜት ለማጎልበት የተሰባሰባችሁ፤ እንኳን ለዛሬው ቀን አደረሰን እላለሁ::

የተከበራችሁ ወገኖቼ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን ትልቅ ለማድረግ ስንጥር በጠ/ሚኒስትራችንና በክልላችን አስተዳደር የተፎካካሪ ቡድኖች እየተጠሩ ነው::

ምንም እንኳ ኢትዮጵያዊነት ጥሩ ቢሆንም፣ መደመርና በጋራ መኖር ታላቅነት ቢሆንም፣ አመጣጡ በምን መልኩ ነው? የሽግግር መንግሥት ልናቋቁም ነው ወይንስ በተቀደደልን ቦይ ልንፈስ ነው?

ይህችን የተባረከች ሀገር የፍቅር ሀገር አድርገን አንድ ላይ እንድንኖርባት እግዚአብሔር ይርዳን::

# “ህወሐት መራሹን በኦህዴድ መራሹ ኢህአዴግ መተካት መፍትሔ አይሆንም”

## ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ

*ሰሞኑን በመላው ኢትዮጵያ ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ድጋፍ የሚሰጥና የተጀመረው የለውጥና የዴሞክራሲ መንገድ እንዲበረታ የሚያመለክቱ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፎች በስፋት እየተካሄዱ ነው፡፡ በተለያዩ ከተሞች በተከናወኑትና በኢህአዴግ የሥልጣን ዘመን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለሀገር ዕድገትና ብልፅግና እንዲሁም ለፍትሕ የበላይነትና ጭቆናን ለማስወገድ በሚደረገው ሰላማዊ ትግል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደረጉ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ተወድሰዋል፤ ተመስግነዋል፡፡ አወዛጋቢ ሆኖ የቆየው ኮከቡ ያለበት ባንዲራ በንፁህ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ተተክቶ ከትንንሽ የገጠር ከተሞች እስከአዲስ አበባ በአደባባይ በክብር ተውለብልቧል፡፡ ዜጎች በዚሁ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በባህር ማዶ የሚገኙ የተፎካካሪ አባላት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡና በቀጣይ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡*

*የተለያዩ ወገኖች “ኢህአዴግ በውጭ ያሉትን ተፎካካሪ ፓርቲዎች በማምጣት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አለበት” እያሉ ነው፡፡ እኛም በዚህ እና በሌሎችም ጉዳዮች አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ፕ/ር መድኃኔ ታደሰን፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን እና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስን አነጋግረናቸዋል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡*

**ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ የሀገሪቱና የኢህአዴግ መሪ ሆነው መመረጣቸውን ከሰሙበት ጊዜ አንስቶ ያለዎትን ስሜት በመግለፅ ውይይታችንን ብንጀምር…**

**ፕ/ር መድኃኔ፡-** መልካም፡፡ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መመረጣቸው ጥሩ ነው፡፡ አዲስ ፊት፣ አዲስ ሀሳብ፣ አዳዲስ ንግግሮች፣ አዲስ ተስፋ ነው የፈነጠቀው፡፡ ገና ከጅምሩ ሀገሪቱን የመምራት ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹበት ሁኔታ ስለነበር፤ ከዚህ ምኞታቸው ተነሥተው ብዙ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡

ሀገሪቱ ለውጥ ያስፈልጋት ስለነበረ የእሳቸው መመረጥ ከለውጥ ጋር አብሮ የመጣ ጅምር ሂደት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የጠ/ሚኒስትር ዐቢይን መመረጥ በጥሩ ጎኑ ነው የተመለከትሁት፡፡

**ግዮን፡- ሰኔ 16 በአዲስ አበባና በተለያዩ የክልል ከተሞች የተካሄደውን የድጋፍ ሰልፍ እንዴት አዩት? “አስፈላጊ ነበር” የሚሉ ወገኖች እንዳሉ ሁሉ “ተቸኩሏል” የሚሉም አልጠፉም፡፡**


**ፕ/ር መድኃኔ፡-** እኔ የሰልፉ ዕለት ሀገር ውስጥ አልነበርሁም፡፡ በአጠቃላይ ግን የለውጥ ተቋማትን ማጠናከር መቅደም የነበረበት ይመስለኛል፡፡

**ግዮን፡- ምን ዓይነት የለውጥ ተቋማት ናቸው መጠናከርና መፈጠር ያለባቸው?**

**ፕ/ር መድኃኔ፡-** አብዛኞቹ የመንግሥስት ተቋማት ነፃ ተቋማት አይደሉም፡፡ ብዙ ጊዜ የለውጥ የሽሽግር በዚህ ሀገር የሚጨናገፈው ነፃና ጠንካራ ተቋማት ማቋቋም ስለሚያቅተን ነው፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና የፖለቲካ ልሂቃን የተስማሙባቸውንና ያመኑባቸውን፤ በአጠቃላይ የሽግግር ሂደቱን ሊያሳኩ የሚችሉ ተቋማትን የማደራጀትና የመፈተሽ፤ አብሮ የመሥራት ነገሮች ቢቀድሙ ይመረጣል፡፡

እኛ ሀገር ብዙ ጊዜ የሰልፍ ችግር የለብንም፡፡ ሰልፉ ደግሞ በአብዛኛው ከአድርባይነት ባህርያችን ጋር የተሳሰረም ጭምር ነው፡፡ የሚወልደው የፖለቲካ ባህል ጥሩ አይደለም፡፡ በሰልፍ የዚህች ሀገር ችግር አይፈታም፡፡ ሕዝቡ የፖለቲካ ስሜቱን፣ የለውጥ ስሜቱን መግለፁ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚያ በላይ መሥራት ያለባቸውም ኢትዮጵያን የሚወክሉ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎችንና ብዝኃነትን የሚወክሉ ተቋማትን ማጠናከር ያስፈልጋል፤ በፖለቲካ ሂደቱ፣ ድርድሩ ንግግሮች ላይ ቢተኮር የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል፡፡ ዘላቂ መፍትሔም ይኖረዋል፡፡

**ግዮን፡- እርስዎ ካነሡት በተቃራኒ፣ ሰልፉ ላይ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ዓርማዎች፤ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በራሳቸው የሚያንፀባርቁት ነገር አይኖርም?**



*ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ*

**ፕ/ር መድኃኔ፡-** ህዝቦች በመከባባር የተለያዩ ሀሳቦችን ማራመዳቸው ጥሩ እመርታ ነው፤ ግን እኔ በአጠቃላይ እያልኩ ያለሁት እንደዚህ ዓይነት ነገሮች በሰልፍ የሚፈቱ አይደሉም፡፡ በንግግር ነው መፈታት ያለባቸው፡፡ ባንዲራዎች እኮ ዝም ብለው የሚውለበለቡ ነገሮች ሳይሆኑ የተለያዩ ትርክቶችን ነው የሚያንፀባርቁት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥትነትን ትረካዎች በተለያዩ መንገድ፤ በደጋፊነትም፣ በተፃራሪነትም የሚወክሉ ናቸው፡፡ እነሱን ማስታረቅ፣ ወደ አንድ ማምጣት ይጠይቃል፡፡

ይሄ ሳይሆን በየጎራው በተለያየ አቅጣጫ የተለያየ ታሪክ፤ የተለያየ ባንዲራ እንደ ጥቁር ገበያ የሚቸበቸብበት ሀገር መሆን የለበትም፡፡ ወደሚያስማማን አንድ ነጥብ መምጣት አለብን፡፡ ባንዲራዎቹ የሚወክሉት የፖለቲካ አቋም ሳይሆን ታሪክም ጭምር ነው፡፡ ይሄን ማቀራረብ ሳንችል የፖለቲካ ሂደቱን በትክክለኛው መንገድ ማስኬድ አንችልም፡፡

ለውጡ በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሻገር የሚችለው ሰልፎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ከሰልፎች ጀርባ ያሉት የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የማንነት፣ የመጠላላት፣ የመተላላቅ ሂደቶችን ማስተካከል ስንችል ነው፡፡ ከዚያ ደግሞ ረጋ ብለን፤ ሰከን ብለን መነጋገር ይጠበቅብናል፡፡ አንዳንዴ ሰልፎች ያልተረጋገጡ የፖለቲካ ጠላቶችንና የፖለቲካ ወዳጆችን ይፈጥራሉ፡፡ ከዚያ መውጣት፤ ቆም ብለን ማሰብ አለብን፡፡

**ግዮን፡- ኢህአዴግ የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስፋት ባሻገር የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት እየተባለ ነው፡፡**

**ፕ/ር መድኃኔ፡-** የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት ይገባል፡፡ የሽግግር መንግሥት ለሚለው መንግሥትነት ባይሆን እንኳን የሽግግር ተቋሞችንና በተለይ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ጉዞ ሊያግዙ የሚችሉ የፖለቲካ ሂደቶችና ድርድሮች መጀመር አለባቸው፡፡ የግድ ይሄን መንግሥት አፍርሶ ሌላ መንግሥት መመስረት ሳይሆን፤ ሌሎቹን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያገባናል የሚሉ ኃይሎች ሁሉ ያካተተ ድርድር መካሄድ አለበት፡፡

መንግሥትንም ሳታፈርስ ተቋሞቹ ይሄን ቢያደርጉ የታሰበው ተፈፀመ ማለት ነው፡፡ መንግሥት ታክስ ይሰበስባል፤ ሰላምና ፀጥታ ያስከብራል፤ የሀገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይመራል፤ እነዚህን እያደረገ አጠቃላይ የፖለቲካ ሽግግሩ ግን ሁሉም አካላት የሚሳተፉበት እንዲሆን ማድረግ ነው የሚጠበቅበት፡፡ እዚያ ሂደት ውስጥ ገና አልገባንም፡፡ ይሄን ሂደት ተከትለህ ጠንካራ ተቋማት ሳትገነባ እንዴት ነው ወደ ምርጫ የምትሄደው?

ህወሐት መራሹ ኢህአዴግ፣ በኦህዴድ መራሹ ኢህአዴግ መተካቱ ለውጥ አያመጣም፡፡ መፍትሔ አይሆንም፡፡ የፖለቲካና የዲሞክራሲ ተቋማትን በምናስብበት ወቅት ማለት ነው፡፡ የሁሉም ተዋፅዖ ያለበት፣ ኢትዮጵያን ሊወክል የሚችል፣ ባንዲራችንን በትክክል የሚወክል፣ ብዝኃነትን የሚገልፅ የፖለቲካ ሂደት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ትንሽ እየዘገየ ስለሆነ ለውጡ አስተማማኝ የመሆኑን ጉዳይ አሁንም በርግጠኛነት መናገር አይቻልም፡፡

**ግዮን፡- በዚህ መንገድ፤ ብሔር ተኮር ከሆኑ ፓርቲዎችና ሀገራዊ ስሜት ካላቸው ፓርቲዎች ጋር ሙሉ ለሙሉ መግባባት ይቻላል ብለው ያምናሉ? ችግር አይኖረውም?**


**ፕ/ር መድኃኔ፡-** ችግር ለምን ይፈጥራል? ምክንያቱም የፖለቲካ ፍልሚያና ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ፍጭት ነው እዚህ ሀገር የሚያስፈልገው፡፡ አንዳንዴ ብሔር ወደ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ ሊጠቃለል ይችላል፤ አንዳንዴ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ ከብሔር ፓርቲዎች ጋር የሚሠራበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ ገና እየተፈተሸ፣ ገና እየተሞከረ ነው የሚሄደው፡፡

ዋናው ግን ሁሉንም ሊያሠራ በሚችል ተቋማዊና ፖለቲካዊ ሂደት ላይ ማተኮሩ ነው የሚጠቅመው፡፡ የብሔር ተኮር ድርጅቶችም ቢሆኑ የሚወክሉት አካልና ታሪክ ስላለ፤ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲዎችም ሁሉንም ፓርቲዎች አቅፈው፣ የሕዝብን ስሜት ተረድተው፣ ተጠናክረው የወጡበት ሁኔታ አይደለም ያለው፡፡ ስለዚህ የፖለቲካ ሂደቱን አሳታፊ በማድረግ፤ ተቋሞችም ነፃ ሆነው የአንድ የፖለቲካ ኃይል የበላይነት የማይታይባቸው ተቋሞች በመመሥረት ያለፈውን ስህተት እየደጋገምን እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዋና መሠረቱ እዚያ ላይ ነው፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# “የባህር ዳሩ ሰልፍ ሕገ መንግሥቱን ሙሉ ለሙሉ ይፃረራል”

## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ



*ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ*

**ግዮን፡- የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ለጠ/ሚኒስትርነት መመረጥ እንዴት አዩት?**

**ዶ/ር ነጋሶ፡-** በምርጫው ወቅት ሚዲያዎች በስፋት ስከታተል ነበር:: ኢህአዴግ የም/ቤት ስብሰባ አድርጎ በራሱ መዋቅር መሰረት ‘ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ዶ/ር ዐቢይን የድርጅቱ ሊቀ መንበር አድርጎ መርጧል’ የሚል ዜና ስሰማ በሙሉ ልብ ነው የተቀበልኩት:: አምኛለሁም:: በጣም ነው ደስ ያለኝ:: ወጣት ቢሆኑም በድርጅታቸው ውስጥ ተቀባይነት እንዳላቸው እከታተል ነበር፤ በሰዓቱ በአብላጫ ድምፅ መመረጣቸውን በደስታ ነው የተቀበልኩት:: ከአዲሱ ትውልድ የተገኙ ውጤታማ ሰው ናቸው ብዬ ነው የማምነው::

**ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትሩ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የሠሩት ሥራ እንዴት ይገለፃል?**

**ዶ/ር ነጋሶ፡-** የነበሩት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደቀሩና በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ለበርካታ ዓመታት ታስረው የነበሩ የፖለቲካ ሰዎች መፈታታቸው በጣም ደስ የሚል ነው:: በሀገር ውስጥ በዚህ ዙሪያ ጠ/ሚኒስትሩ በርካታ አመርቂ ሥራዎችን አከናውነዋል:: ከሀገር ውጪ በተለያዩ ሀገራት በእስር የሚገኙ ዜጎቻችን ከዚህ በፊት ባልታየ መልኩ ከየሀገሪቱ መንግሥታት ጋር በመደራደር ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ አድርገዋል:: ሽብርተኛ ተብለው የታሰሩ ግለሰቦች ከእስር ተፈተዋል፤ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ድርጅቶች ክሳቸው ተቋርጧል:: ይሄ ሁሉ በመጀመሪው ሩብ የሥልጣን ዘመናቸው የሠሩት መልካም ነገር ነው ማለት ይቻላል::

**ግዮን፡- ሰሞኑን ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ በተዘጋጀ የድጋፍ ሰልፍ ላይ፣ ህዝብ በነፃነት ሀሳቡን ሲገልፅ ነበር:: የነፃነት ታጋዮች ተወድሰዋል፤ ኮከብ አልባው ሰንደቅ ዓላማ በከፍተኛ ሁኔታ ተውለብልቧል:: ኮከብ ያለበት ባንዲራ አለመፈለጉን ይህ አያሳይም?**

**ዶ/ር ነጋሶ፡-** በእኔ በኩል ግለሰቦችና ፓርቲዎች የሚወክሏቸው አመለካከቶች አሉ:: ሀሳብና ፍላጎቶች አሉ:: የፓርቲዎችንና የግለሰቦችን መብት ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው:: በሌላ መልኩ ደግሞ የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥት ማክበር አለብን:: ሕገ መንግሥቱን ተመርኩዘው የወጡ ሕጎችን ማክበር አለብን:: በእኔ እይታ አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ የተለያዩ ዓይነት ባንዲራዎች ይታዩ ነበር:: ከላይ እንደገለፅኩት ይሄ የተለያዩ አካላት ስሜት ነው:: በተለያየ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ አካሎች በአንድነት የጠ/ሚኒስትሩን እንቅስቃሴ መደገፋቸው ጥሩ ነው:: ሁሉም የየራሳቸውን አመለካከት ይዘው ማለት ነው::

የባህር ዳር የድጋፍ ሰልፍ ግን ሙሉ በሙሉ ከአዲስ አበባው የድጋፍ ሰልፍ ይለያል:: በእኔ እይታ ሕገ መንግሥቱን መፃረር ነው ማለት ይቻላል:: ለሕግ ተገዥ ያለመሆን ነገር የተንፀባረቀበት ነው ብዬ ነው የማምነው::

**ግዮን፡- በምን መልኩ ነው ሕገ መንግሥቱን የተፃረረው?**

**ዶ/ር ነጋሶ፡-** ሁላችንም እንዳየነው አንድ ወይም ሁለት ካልሆነ በስተቀር፤ የአማራ ክልልን ባንዲራም ሆነ የፌደራል መንግሥቱን ሰንደቅ ዓላማ በድጋፍ ሰልፉ ላይ አላየሁም:: ሕግ የሚከለክለው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ ነበር በብዛት የታየው:: ስታድዮሙን ሙሉ ለሙሉ የሸፈነው የድሮ የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው:: ይሄ በሕግ ተከልክሏል::

እነዚያ ባንዲራዎች አንድ ሊያደርጉን እንደማይችሉ ዐይተን፤ በ1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚደምር፣ ሃይማኖታችንን በሙሉ የሚደምር፣ የተለያዩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን የሚያግባባና ሁላችንንም አንድ የሚያደርግ ባንዲራ የቱ ነው? ብለን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ሦስት ላይ አስቀምጠልናል:: በባህር ዳር ላይ የታየው ግን ይሄንን የሚቃረን ነው:: በእርግጥ የመቃወም መብት የሁሉም ነው፤ ይሄንን መከልከል አያስፈልግም:: ነገር ግን ሕገ መንግሥት ሳይሻሻል ‘እኛ የምንፈልገው የድሮውን፣ የነገሥታቱን ባንዲራ፣ የእነ አፄ ኃይለ ሥላሴን ባንዲራ፣ የእነ ሚኒሊክን ባንዲራ ነው የምንፈልገው’ የሚሉ ሰዎች ሀሳባቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ አቅርበው ሕገ መንግሥቱ የሚሻሻልበት መንገድ አለ::

ሰዎች በባንዲራው ላይ ተቃውሞ ሊኖራቸው ይችላል:: ግን ይሄንን ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል መጠየቅ ነው እንጂ የድሮ ባንዲራ ይዘው በመውጣት ሀሳባቸውን በሌሎች ላይ መጫን አይችሉም:: እኔ እንደሚመስለኝ ባህር ዳር ላይ የታየው ሰንደቅ ዓላማ ኢትዮጵያን አንድ የሚያደርግ አይደለም:: ሰዎች ትክክል ነን ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፤ ግን ያ ባንዲራ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን አንድ ያደርጋል ተብሎ አይታመንም::

**ግዮን፡- ሕዝቡ ግን “አንድነታችንን ይገልፃል ሁሉንም ህዝብ ያግባባል” ብሎ ነው ኮከቡን ለኢህአዴግ ትቶ ንፁሑን ሰንደቅ ዓላማ ራሱ ያውለበለበው፤**

**ዶ/ር ነጋሶ፡-** ሰዎች ትክክል ነው ብለው ካመኑ የድሮውን ሰንደቅ ዓላማ መሸከም ይችላሉ:: የሚሸከሙት መብታቸው ቢሆንም፤ በይፋ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ባንዲራ ይህ ነው ►

ብለው የሚከራከሩ ሰዎች ካሉ ስህተት ነው ብዬ ነው የማምነው::

ኮከቡ እንዲነሣ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ፣ መጠየቅ መብታቸው ነው፤ ሕገ መንግሥቱ ላይ አንቀጽ ሦስት እንዲሻሻል ሕጋዊ አካሄድን መከተል ነው ያለባቸው እንጂ በእንዲህ ዓይነት ሰልፍ ላይ አይደለም ሌላ ነገር የሚያስተጋባው::

**ግዮን፡- ሰልፉ ላይ የታየው የሰንደቅ ዓላማ ለውጥ በራሱ እኮ ግልፅ ነው ማለት ይቻላል:: መንግሥት ከዚህ ተነሥቶ የባንዲራውን ጉዳይ መልስ ሊሰጥበት አይገባም?**

**ዶ/ር ነጋሶ**፡- አንደኛ፣ በባህር ዳር ስታዲየም ላይ የተገኘው ህዝብ መቶ ሚሊዮን የሚሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀርቶ ጠቅላላ የአማራ ክልልን ሕዝብ አይወክልም:: የተወሰኑ ግለሰቦች ናቸው በስታዲየም የተገኙት፤ እነዚያ ሰዎች በዚያ መንገድ ሀሳባቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ::

ግን ቀደም ሲል እንደገለፅኩት፤ ሕገ መንግሥቱ በግልፅ የሀገሪቱን ህዝቦች እኩልነት የሚያረጋግጥ ነው ያለውን ባንዲራ ይፋ አድርጓል:: በሕግ ፀድቋል:: በ1993 ዓ.ም ሕገ መንግሥት ሲረቅ እኔ ኦህዴድን፣ ዳዊት ዮሐንስ ኢህዴንን (ብአዴንን) ወክለን ተገኝተናል:: ያኔ ኢህአዴግን አይደለም የወከልነው፤ በሕገ መንግሥቱ ላይ ስንወያይ ከሁለታችን ውጪ ሃያ ሠባት የሌላ ፓርቲ ተወካዮች ነበሩ:: አጠቃላይ 29 ሰዎች ነን የተወያየንበት፤ እኛ ተነጋግረን ነው ሕገ መንግሥቱን ወደ ሽግግር መንግሥት ተወካዮች ም/ቤት ያቀረብነው::


ስለዚህ ያኔ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረን፣ ተከራክረን ሕግ አውጥተናል:: የሰንደቅ ዓላማው ጉዳይም በዚያ መንገድ የራሱ ሕግ በሕገ መንግሥቱ ተቀምጦለታል:: በርግጥ እንደሚባለው ሕዝብ የድሮውን ሰንደቅ ዓላማ የሚናፍቅና የሚፈልግ ከሆነ፣ በቀጥታ ሕጋዊውን መንገድ ነው መከተል ያለበት:: ግን እኔ እንደሚገባኝ በባህር ዳር ላይ የታየው ነገር የሁሉንም ኢትዮጵያ ሕዝብ አይወክልም::

**ግዮን፡- በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን የሽግግር መንግሥት ምሥረታ ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ?**

**ዶ/ር ነጋሶ**፡- የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ያስፈልጋል የሚባለው ነገር ትክክል አይመስለኝም:: ሕገ መንግሥቱ "የመንግሥትን ሥልጣን የሚይዝ አካል በምርጫ ያሸነፈው ወገን መሆን አለበት" ይላል:: ስለዚህ ምርጫ ተካሂዶ በምርጫ ነው እንጂ፤ ዝም ብሎ ፓርቲዎችን ሰብስቦ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አይቻልም::

አሁን እየታየ ያለው ሁኔታ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ትክክለኛ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን እየተደረገ ነው:: ስለዚህ ምርጫው እንደከዚህ ቀደሙ አይደለም፤ ፍትሐዊ ይሆናል:: ውጭ ያሉት ኃይሎች ራሳቸው "ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እየመጣ ነውና ጦርነቱን ትተን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመሥራት ዝግጁ ነን" ብለው እነ ግንቦት ሠባት፣ አርበኞች ግንባር እየመጡ እኮ ነው:: ስለዚህ በዚያ መንገድ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ ነው እንጂ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት እያሉ ጊዜ ማጥፋቱ አስፈላጊ አይመስለኝም፤ ለእኛ የሚያስፈልገን አንድነትና መደመር እንጂ መጨንገፍ አይደለም::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



**ግዮን፡- ኢህአዴግ ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድን ጠ/ሚኒስትር አድርጎ መርጦ፤ እሳቸውም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ከጀመሩ ሦስት ወራት ተቆጥረዋል:: ይህንን የሥልጣን ጊዜ እንዴት ይገመግሙታል?**

**ፕ/ር በየነ**፡- የእኔ ግምገማ ወይም ትንታኔ ተቋማዊ ነው የሚሆነው:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ የተሰጣቸውን ሓላፊነት በግል የመወጣት ብቃት አላቸው:: ያንኑ በዚህ ሦስት ወር ውስጥ ሲያደርጉ የቆዩ መሰለኝ:: ባለፉት 27 ዓመታት ተለይቶን የቆየውን ሀገራዊ ስሜት መመለሳቸው ሕዝቡና የፖለቲካ ድርጅቶች የምናነሳቸውን ጉዳዮች ነው ሲያስተጋቡ የነበረው:: እንደ መፈክርም ተጠቅመውበታል:: እሰየው ነው፤ በዚህ በኩል እኛ ችግር የለብንም::

የእስረኞችም መፈታት በራሱ ትልቅና ገንቢ ነገር ነው ብዬ አምናለሁ:: በሦስት ወር ውስጥ በሕዝቡ ወስጥ ያለውን መከፋፈልና ልዩነት የሚፈጥሩ ጉዳዮችን አንስተው፤ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ጥልቅ ውይይት አድርገዋል:: ከዚህ በላይ አልፈው ምን ያህል ይሄዳሉ የሚለው አሳሳቢ ነው:: ምክንያቱም ብዙ ቃል እየተገባ ነው:: ከዚህ በላይ አልፎ ለመሄድ ድርጅታዊ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል:: እውነት ይህን ሁሉ ነገር እያለ ያለው ኢህአዴግ ነው ወይስ በጎ አሳቢ የሆኑ ሰው አጋጣሚውን አግኝተው ነው እንዳያስብል፤ በድርጅታቸው ሙሉ ለሙሉ አሁን በጀመሩት እንቅስቃሴ ላይ መደገፋቸውን እርግጠኛ አይደለሁም::

አንዳንድ ቅሬታ አለን የሚሉ ወገኖችንና በአንድ ጉዳይ ላይ የተሳከረ አስተያየት የሚሰጡ ሰዎችን እንሰማለን:: መልካም ሥራቸው በአፍራሽ ኃይሎች ፈተና ደርሶበታል:: ያንን ፈተና ሊያደርስ የሚችለው ተራ ግለሰብ ነው ብዬ ግምት አልወስድም:: ረቀቅ ያለ ነገር ነው:: ተቃውሞ የመቀስቀስ ፍላጎት ያለው አካል እንዳለ ነው የሚያሳየው:: ጠ/ሚኒስትሩ በአሁኑ ሰዓት ከተለያዩ ክልሎች የተፈናቀሉ ሰዎችን ጉዳይ ቅድሚያ ይሰጡታል የሚል ተስፋ ነበረን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዛት ከየቦታው ተፈናቅሎ በየመጠለያውና በየሜዳው ፈሶ ያለበት ሁኔታ ስለሚታይ፣ በእኛ በኩል ይሄ ድክመት ይመስለናል:: በፍጥነት መታረም አለበት::

**ግዮን፡- በየቦታው ግጭቶች መከሰታቸው ለጠ/ሚኒስትሩ ቀጣይ እንቅስቃሴዎች እንቅፋት አይሆኑም?**

**ፕ/ር በየነ**፡- እሳቸው ወደ ሥልጣን ከመምጣታቸው ቀደም ብለው ህዝብ ላይ ይደርሱ የነበሩት መፈናቀሎችና ጭቆናዎች አልተቋረጡም:: እንደታየው መጨፍጨፍ፣ መከፋፈል አለ:: እነዚህ ነገሮች ባለፉት ሦስት ወራት ተቋርጠው አላየንም:: የእሳት አደጋ ዓይነት ግጭት የተነሣበት ቦታ፤ አንዱ ጋር ሄደው አግባብተው ተስተካከለ ሲባል ሌላ ጋር ደግሞ ግጭቱ ይፈነዳል:: ይሄ እንግዲህ የሚያሣየው እሳቸው በሚያረጋጉት ጥረት ብቻ እኒዚህ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ተፈትተዋል ተብለው የሚቀመጡ አይደሉም፤ ከመተማ አንሥቶ ምዕራብ ወለጋ፣ ታች ደቡብ ሄዶ ጌዲኦ፣ ጉጂ፤ ቀጥሎም ሶማሌ አካባቢ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል:: እነዚህ ሁሉ እሳቸው እንደሚሉት ሁኔታዎች መረጋጋታቸውን አያሳይም:: ወደ ፊትም ዕንቅፋት የሚሆኑባቸው ችግሮች ናቸው::

**ግዮን፡- ከእነዚህ ግጭቶች ጀርባ የእሳቸውን እንቅስቃሴ የማይደግፉ ኃይሎች እጅ ሊኖርበት አይችልም?**

**ፕ/ር በየነ**፡- ከግጭቶች በስተጀርባ ሁልጊዜ ኃይሎች አሉ:: ይሄ ከዚህ በፊትም ተብሎ ያለቀለት ነው:: ህዝብ፣ ህዝብ ላይ ተነሥቶ አይደለም የሚጋጨው፤ የሚቀሰቅስና የሚያስተባብር የፖለቲካ ፍላጎት፣ የግል ጥቅም፣ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች ካልሆኑ በስተቀር፤ ህዝቡ ከመቶ ዓመት በላይ ረዥም ጊዜ አብሮ የኖረ ነው:: ዛሬ ብድግ ብሎ አንዱ የሌላውን ሰው ቤት ማቃጠል፣ መጨፍጨፍ፣ መግደል በሰዎች ዘንድ የለም:: ይህን የሚያደርጉትና የሚያስተባብሩት የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ናቸው::

ስለዚህ በተለምዶ እንደሚባለው፤ ማየት፣ መዳሰስ፣ ስሙን መጥራት እንደማይቻለው ዓይነት ኃይሎች አሉ፤ 'የቀን ጅቦች አሉ' እየተባለ ▶

# “የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ካልተመሠረተ ኢህአዴግ ብቻውን ችግሩን አይፈታውም”

## ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

◀ ብቻ ችግሩ መፍትሔ የሚገኝለት አይደለም:: ችግሩን በደንብ ተመርምሮና ተደርሶበት፤ የኃይል እርምጃ ሳይሆን ሁሉም ተነጋግሮ መፍትሔ የሚፈጠርበት ሁኔታ መገኘት አለበት የሚል አቋም ነው ያለኝ::

**ግዮን፡- እስከዛሬ ድረስ ባልታየ መልኩ፤ በሰሞኑ ህዝባዊ የድጋፍ ሰልፎች ላይ፤ ኢህአዴግ በሕግ ከደነገገው ባንዲራ ውጭ፤ ንፁህ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለም ያለበት ባንዲራ እየተውለበለበ ነው:: ይሄ ህዝቡ ኮከቡን እንደማይፈልገው አያሣይም?**

**ፕ/ር በየነ፡-** ለእኔ ከባንዲራው ላይ ጭነት መኖር አለበት፤ የለበትም የሚለው ይሄን ያህል ህዝብን የሚያበጣብጥ ጉዳይ አይመስለኝም:: ከዚህ በፊት ብዙ ነገር ታይቷል፤ በባንዲራ ዙሪያ:: ዋናው ቁም ነገር መሠረታዊ የፖለቲካ መፍትሔ መፈለግ ነው እንጂ፤ ያኛው ባንዲራ ከተፈለገ ሕዝባዊና የሚመለከታቸው ወገኖች ክርክር አካሂደው መግባባትና ማስወገድ ይቻላል:: ይሄ አይደለም የሀገራችን ትልቁ ችግር::

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰልፍ ይወጣል፤ አያስደንቅም:: የአሁኑን የህዝቡን ስሜት ማጣጣሌና ውድቅ ማድረጌ አይደለም:: እኔ ህዝብ ያልወጣበትን ጊዜ አላስታውስም:: ሰልፉን ዝም ብለን በየዋህነት ማየት የለብንም:: ድርጅታዊ ሥራ አለው:: ሁሉንም ነገር በጥልቀት ማወቅ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ፡- አዋሳ በተደረገውና እሳቸው ንግግር ባደረጉበት ጊዜ በአውቶቡስ ከተለያየ ቦታ ተጭነው ሰዎች ወደ ስታድዮም እንዲመጡ ሲደረግ ነበር::

ሰልፉን ዝም ብሎ አጉልቶ ማስጮሁ ፋይዳ የለውም:: ካድሬዎች እንዴት አድርገው ሰውን እንደሚያስወጡ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ዘመንም ዐይተናል:: ሌላው ሌላውም አለ፤ እሱ አይደለም ቁም ነገሩ:: ሕዝቡ በጣም የተከፋ ነው:: 27 ዓመት ሙሉ፤ አዲሱ ጠ/ሚኒስትር የሚያወሩትን ቋንቋ ሰምቶም አያውቅም:: እንደዚያ ዓይነት ንግግር መናገር እንደ ወንጀል በሚያስቆጠርበት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ህዝብ፤ አሁን እየታየ ያለውን ስሜት ይዞ ቢወጣ አያስገርምም::

እኛ ኹነቶችን በንቃት እንጂ፣ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ዝም ብለን አናይም:: ፖለቲካዊ ፋይዳው ምንድን ነው? ምን ተከናውኖ ነው ይህ ሁሉ ግርግር የሚታየው? ሊሆን ይችላል ወይ? አይችልም ወይ? የሚለው ነጥብ ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት::

**ግዮን፡- በአሁኑ ሰዓት የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት ብለው ያምናሉ?**

**ፕ/ር በየነ፡-** ከፖለቲካው ሂደት ተነሥቶ ነው መናገር የሚያስፈልገው:: በነገራችን ላይ የሽግግር መንግሥት ይቋቋምና የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ይቋቋም በሚለው መካከል ልዩነት አለ:: በእኛ በመድረክ ፓርቲ እንደአቋም በአሁኑ ጊዜ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ይቋቋም የሚል ጥሪ አስተላልፈናል::

**ግዮን፡- በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ቢያብራሩልን...**

**ፕ/ር በየነ፡-** ልዩነቱ ግልፅ ነው:: የብሔራዊ አንድነት መንፈስ በግልፅ እንደሚያሣየው ሁሉንም የሚያግባባ አንድነት ነው:: ለዚህም ጥሪ አቅርበናል:: ከኢህአዴግ ጋር በአንድ መድረክ ተቀምጠን እንድራደር ብለንም በጽሑፍ አስገብተናል:: በ17 ነጥቦች ዙሪያ ይሄንን ካስገባን ሳምንት አልፎታል:: እንገናኝ የሚለውን መልስ እየጠበቅን ነው ያለነው::

የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚለውን ሀሳብ እኛ የማንጋራው፤ ‘በሥልጣን ላይ ያለው ኢህአዴግ ተሸንፎ ወድቆ፤ እሱንና እሱ የፈጠራቸውን ወገኖች የሚተካ፤ ከዜሮ ጀምሮ በመንቀሳቀስ አዲስ ሥርዓተ መንግሥት ይመሥርት’ ስለሚል እኛ ይህን ሂደት አንቀበልም:: በ1983 ዓ.ም ደርግ ሲወድቅ የተቋቋመው የሽግግር መንግሥት ነው:: እንደሱ ዓይነቱን ሁኔታ በዚህ ውጥረት ወቅት አስፈላጊም አይደለም ነው የምንለው:: በእኛ እምነት ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት ቢመሰረት ከኢህአዴግ ጋር ድርድር ተደርጎ ስለሆነ፤ ህዝባዊ መሠረታቸው ሰፊ የሆነ የሚታወቁ ፓርቲዎች በሙሉ፣ ጥሪ ተደርጎላቸው፤ ታዛቢ ባለበት፣ ሲቪክ ማህበረሰብ፣ የሃይማኖት ተወካዮች ባሉበት ውይይት ተደርጎ፤ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት በሚቋቋምበት ዙሪያ ተደራድሮ ወደዚያ መሸጋገር ያስፈልጋል::

አሁን ሀገራችን የገባችበትን የፖለቲካ ቀውስ፤ ኢህአዴግ ለብቻው ከዚያ ማጥ ውስጥ ሊያወጣት ስለማይችል ነው:: እኛ እንደአማራጭ ያቀረብነው የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ሐሳብ ችግሩን ለመቅረፍ በጠ/ሚኒስተር ዐቢይ እየተሞከረ ነው፤ ግን የችግሮች ጥልቀት በዚህም በዚያም ሁኔታዎች እንዲፈነዱ እያደረጉ ነው:: እሳቸውም ጥቃት ውስጥ እንደገቡ እያየን ነው:: በአንዳንድ ታዳጊ ክልሎች ፀጉረ ልውጦችን ተጠንቀቁ የሚባለው የአንድ ትልቅ ነገር ጫፍ መኖሩን ያሳያል::

ዴሞክራሲያዊና ሁሉንም ወደሚያግባባ የሽግግር መንግሥት ለማምጣት፤ አህአዴግ ለብቻው አይችልምና ይህን ዓይነት የተንኮል ተግባር የሚቀሰቅሱት ወገኖችም ሆኑ ሌሎች አካላት፤ እስኪ በዚህ ዓይነት መድረክ ላይ ተገናኝተን የወደፊቱን የኢትዮጵያ ሁኔታ አብረን እናቅድ የሚል ጥሪ በእኛ በኩል አቅርበናል::

**ግዮን፡- ወንድምዎ ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ፣ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የጦር አውሮፕላናቸው ተመትቶ፤ በኢሳይያስ መንግሥት እጅ ከወደቁ 20 ዓመት ሊሆናቸው ነው:: ሰሞኑን የኤርትራ ልዑካን ቡድን አባላት አዲስ አበባ መጥተው ነበርና በእሳቸው ዙሪያ የሰማችሁት አዲስ ነገር አለ?**

**ፕ/ር በየነ፡-** እኔ እስከማውቀው ድረስ የኮሎኔል በዛብህ ጉዳይ፤ አሁን ለመጣው ልዑካን ቡድን ስለመቅረቡ መረጃው የለኝም:: ይሄ ደግሞ፣ አህአዴግ በሌላ አገር ያሉ ምርኮኛ እስረኞችን ለማስለቀቅ ላለፉት 27 ዓመታት ከታየው ያለመፈለግ ስሜት ለይቼ አላየውም:: ‘ኢህአዴግ እስረኞችን ልቀቁ፤ በዚህ ዙሪያ እንደራደር’ ብሎ አያውቅም::

እንዲያውም አንድ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሶማልያ ውስጥ ኢህአዴግ አዝምቶ ነበር:: ከአንድ ከሁለት ዓመት በኋላ፤ ‘ሸብር ብላችሁ አዘመታችሁ፤ በነገሩ ምን ያህል ጉዳት ደርሷል? ምን ያህል የመከላከያ ሠራዊት አባላት ቆሰሉ? ሞቱ? ምን ያህል ወጪስ ወጣ?’ የሚሉ ጥያቄዎችን በሰዓቱ የፓርላማ አባል ስለነበርሁ አንሥቼ ነበር፤ የተሰጠኝ መልስ ግን ‘ለሽርሽር አልሄዱም’ የሚል ነው፤ ‘ዝርዝሩን የማቅረብ ግዴታ የለብንም’ ነው የተባልነው::

ከዚህ የተነሣ የወንድሜን ጉዳይ የመከታተሉ ሓላፊነት ስላለብኝ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በምናደርጋቸው ግንኙነቶች አማካይነት ባደረግነው ጥረት፤ የኮ/ል በዛብህን ጉዳይ ስናነሣ፤ ‘የኢትዮጵያ መንግሥት ጠይቆም አያውቅ’ ነው የተባልነው:: በሕይወት አለ ወይ? ከሌለም አስፈላጊው መረጃ እንዲቀርብ ዓለም አቀፍ ሕግ ነው የሚደነግገው:: አንድ ሰው ምርኮኛ ወይም የሌላ ሀገር እስረኛ ሲሆን፣ በሕይወት ካለ ይታወቃል፤ ከሌለም አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይቀርባል፤ በሦስተኛ ወገን አማካይነት::

‘ይሄን ሁሉ ጥያቄ በኢትዮጵያ መንግሥት አልተጠየቅንም፤ ላልተጠየቅነው ጥያቄ እንዴት መልስ እንሰጣለን?’ የሚል ነው የኤርትራው መሪ የተናገሩት:: እኔ በራሴ መስመር ተጉዤ ባለኝ ጥረት ያገኘሁት ምላሽ ይህ ነው:: ስለዚህ አሁን የኤርትራ ልዑካን ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ የመንግሥት አካላት የእሱን ጉዳይ ይጠይቁ፣ አይጠይቁ የምናውቀው ነገር የለም::

ከቤተሰብ ጋርም ስለእሱ መረጃ ለማግኘት፤ ወይም ያለንበትን ሁኔታ ለማወቅ፤ ኢህአዴግ ከማናችንም ጋር እስከአሁን ድረስ ግኑኝነት አድርጎ አያውቅም:: ስለዚህ በመንግሥት በኩል ያየነው ጅምር እንቅስቃሴ የለም፤ ለእኛም የደረሰን መረጃ የለም፤ ያለው እውነታ ይሄ ብቻ ነው::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



# “ደርግን የጣለው ኢህአዴግ አይደለም”

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

*ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከሰሞኑ በተለያየ ጊዜና ቦታ ሳቢ ንግግሮችን እያስደመጡን ይገኛሉ፡፡ ከኤርትራ ጋር ከመታረቅ ጀምሮ ድፍድፍ ነዳጅ እስከማውጣት የደረሰ ብስራት ነግረውናል፡፡ እኛም ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተላለፏቸውን ልዩ ልዩ ንግግሮችና መግለጫዎች አሰባስበን ለአንባብያን በሚመች መልኩ የተወሰኑትን ሀሳቦች አጠናቅረናቸዋል፡፡*

### ለኤርትራ ልዑካን በተደረገው የራት ግብዣ ላይ

አርቲስቶች መጪውን መስከረም የምናከብረው አዲስ አበባ እና አስመራ ስለሆነ ከወዲሁ ዝግጅት እንድታደርጉ:: ምፅዋ ላይ ወክ ማድረግ የናፈቃችሁ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥራ ስለሚጀምር እንድትዘጋጁ::

ኤርትራውያን ወንድምና እህቶቻችን ሀገራችሁን እንድትጎበኙ፤ ክረምቱ ሳያልፍ ዝናቡን እንድታዩ፤ ቅዱስ ዮሐንስን፣ እንቁጣጣሽን አብረን በአማርኛና በትግርኛ እንድንዘፍን በጉጉት ስለምንጠብቃችሁ ቶሎቶሎ እንድትመጡ እንፈልጋለን:: ሠላም ለኢትዮጵያ፤ ሠላም ለኤርትራ፤ ሠላም ለሱማሌ፣ ሠላም ለሱዳን፤ ክልላችን (የአፍሪካ ቀንድ) ከጦርነት ቋንቋ ወደ ፍቅር፣ ወደ ሰላም ቋንቋ እንዲሸጋገር፤ ቀጣዩ ዘመን ለክልላችን ብልፅግናና እድገት እንዲሆን፤ መግደል፣ ማቁሰል፣ ክፉ መናገር፤ መሰልጠን የሚመስለን ሰዎች የማያስፈልግ ጊዜ እያባከንን መሆኑ ገብቶን በይቅርታ ልብ ተፀፅተን አሁንም በፍቅር ለመጣ ኢትዮጵያውያን በፍቅር ለማቀፍና ይቅር ለማለት ዝግጁ መሆናችንን እየገለፅን ገዳይነት ኪሳራ ነው፤ ፍቅር ግን ያሻግራል::

### አቶ የማነ ገብረ አብ (የኤርትራ ፕ/ት ልዩ አማካሪ)

ስለተደረገልን ደማቅ አቀባበል ለማመስገን እፈልጋለሁ:: ዛሬ ከ20 ዓመት በኋላ ነው የተገናኘነው፤ ስንገናኝ ግን 20 ዓመት ያህል እንዳልተገናኘን የሚመስል ነገር አልነበረም:: ያለምንም ማቋረጥ አብረን እንደነበርን ሆነን ነው የተገናኘነው:: ዛሬ በመካከላችን ምንም የአስተሳሰብ ልዩነት የለም:: አንድ የሚያሳዝን የታሪክ ምዕራፍ ዘግተን ወደአዲስ ምዕራፍ ገብተናል የሚል እምነት አለን:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፣ አንዳንድ ትንንሽ ችግሮች ለዛሬም ለሚቀጥለውም ሊኖሩ ቢችሉም ይህን ዓይነት ነገር ደግሞ፣ በሁለቱ ህዝቦች መካከል ብቻ ሳይሆን በአንድ ቤተሰብም የሚገኝ ስለሆነ፤ እነዚህን ትንንሽ ጥያቄዎች በመረዳዳት፣ በመግባባት እንደምናሸንፋቸው እናምናለን::

### በአፋር

ደርግን የጣለው ኢህአዴግ አይደለም፤ ደርግን መጀመሪያ የጣለው ደርግ ነው:: ደርግ ገዳይ ባይሆን፤ ጨፍጫፊ ባይሆን ማንም ሊጥለው አይችልም ነበር::

እኔ ራሴ የገባሁትን ቃል ለመፈፀም እንጂ፣ በየዘመናቱ መንግሥታት የገቡትን ቃል ለመፈፀም አልመጣሁም:: ለአፋር የሀገር ሽማግሌዎች የገባሁት ቃል፣ ኢንዱስትሪያል ፓርክ እናመጣላችኋለን፤ በጀት እናሻሽላለን፤ በመስኖ እርሻ የሚስፋፋበትን መንገድ እንፈልጋለን:: በሚቀጥለው ስመጣ ይህን ካልፈፀምኩ ትጠይቁኛላችሁ ማለት ነው:: በተረፈ በየቦታው ድንጋይ ማስቀመጥ፣ በየቦታው ቃል መግባት ላለፉት ዓመታት የኛ ባህል ነበር:: እነዚያን ድንጋዮች መልቀም አልችልም እኔ:: የእኔ እቅድ፣ የኔ አካልም አልነበረም:: ያንን ለመሙላት ጊዜም አላባክንም:: ስለዚህ ባልገባሁት ቃል አልጠየቅም ማለት ነው::

ልክ ወንፊት እንደሚያጠራው በምክክር እያጠራን እንሄዳለን:: ይህ ለኢህአዴጎችም ጭምር የሚሠራ ይሆናል:: የጀመርነውን ለውጥ የሚቀለብስ ማንኛውንም ነገር ለመሸከም ዝግጁ አይደለንም:: የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ውስጥ የሚያስገባ፣ ሰላም የሚያሳጣ፣ መልሶ ጭንቀት የሚያስገባ፣ እናቶች ልጆቻቸው ወጥተው እስኪገቡ ድረስ የሚጨነቁባት ኢትዮጵያ ድጋሚ እንዳትመለስ መከፈል የሚገባው ዋጋ ይከፈላል:: ጠርተን፣ ጠንክረን እንወጣለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

### ለጥበብ ሰዎች

ጥበብ ሥራዋን ብትሠራ ኖሮ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥላቻ ነግሦ፤ ሰው የራሱን ወገን ለመግደል አይደለም ለመብላት ባልተዘጋጀ ነበር:: ጥበብ ሚናዋን ብትጫወት፣ ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ ሀብት ይዛ ባልተቸገረች ነበር:: ጥበብ ግን በባህርይዋ የሚፈጥራትን ብቻ ሳይሆን አውቆ የሚጠቀምባትን ህዝብ ትፈልጋለች::

### ለህገራዊ ሰልፉ ካቀረቡት ምስጋና

ምስጋና ከሚቀበል ሰው ይልቅ ምስጋና የሚሰጥ ታላቅ ነው:: ያለጥርጥር ይህንን እንረዳለን:: ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ በሀገራችን እየታየ ያለው የለውጥ ጭላንጭል፤ አሁን የሀገራችን ህዝብ እየሰጠን ካለው ወሰን አልባ ድጋፍ እና ፍቅር ጋር የሚወዳደር እንዳልሆነ ብንገነዘብም መንግሥት ይህንን ድጋፍ፣ ፍቅር፣ ክብር እና አለኝታነት ለተሠሩ ሥራዎች እንደተሰጠ ምስጋና ብቻ ሳይሆን በቀጣይ እንሠራቸው ዘንድ ለሚገቡን በርካታ ሥራዎች ተግባራዊነት የተላለፈ የአደራ መልእክት፤ እንዲሁም የአጋርነት ማሳያ አድርጎ በመቁጠር፤ ከምንጊዜውም በላይ በፍጹም ቁርጠኝነት እና ትጋት ለማገልገል በጽናት ይሰራል::

ከምሥራቅ እስከምእራብ፤ ከሰሜን እስከደቡብ ያላችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ ከሠራነው ሥራ እጅግ ለሚልቀው እና ትርጉም - አንድምታውም ፍጹም ለሚረቀው ወሰን አልባ ድጋፋችሁ እና ፍቅራችሁ በያላችሁበት ሆናችሁ እነሆ ምስጋናችን ይድረሳችሁ:: የቸራችሁን ምስጋና የኛ ብቻ ሳይሆን የናንተም ድምር ውጤት ነውና እናንተ አመስጋኞቹ ዋናዎቹ ተመስጋኞች መሆናችሁን ለአፍታም ቢሆን አንዘነጋም፤ መዘንጋትም አይቻለንም:: እናም ተመስጋኞቹ አመስጋኞች የለገሳችሁንን አብሮነት በፍቅር - አደራ ያላችሁንን የነገ ትግል በክብር ተቀብለን ታላቂቱን ሀገር ወደቀድሞ እና ከዚያም ወደላቀ ታላቅነት ከፍታዋ ለመመለስ ቃል ስንገባላችሁ በታላቅ አክብሮት እና በፍጹም የእንሻገራለን ቁርጥ ስሜት ነው::

### ድፍድፍ ነዳጅ የማውጣት ሙከራ ስለመጀመሩ

ፖሊ ጂ ሲ ኤል የተሰኘው የቻይና ኩባንያ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ድፍድፍ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝን በሚመለከት፤ በተለይም የተፈጥሮ ጋዝን በሚመለከት አመርቂ ውጤት በመገኘቱ እና ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚወጣው ነዳጅ በቀጥታ በሚዘረጋው የነዳጅ መስመር ወደ ጅቡቲ ሄዶ ለኤክስፖርት እንዲቀርብ፤ በኛ በኩል ዝግጅት ጨርሰን፤ ጅቡቲ በነበረን ቆይታ ያደረግነው ድርድርና የተግባባንበት አንዱ የነዳጅ ማስተላለፊያ ዝርጋታ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅና የተፈጥሮ ጋዝ ለኤክስፖርት ማቅረብ እንድንችል ነው::

በመጀመሪያው ዓመት ብቻ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ እንደሚችል ይገመታል:: እኛ ኢትዮጵያውያን የሀብት ሁሉ መሠረት የሆነው የተፈጥሮ ሀብት ተገኝቶ እሱን በመቀራመትና በመከፋፈል የተመሠረተ የእድገት አቅጣጫ የምንከተል ሀገር አይደለንም::

ለእኛ ዋነኛ ሀብታችን ሴትና ወንድ ዜጎቻችን ናቸው:: እነዚህ ዜጎቻችን እንዴት ሥራ ያገኛሉ? እንዴት ሕይወታቸው ይሻሻላል? አጠቃላይ ሀብታችንስ እንዴት ማደግ ይችላል? ስንል እንደ አንድ የማደጊያ ግብዐት የምንወስደው የተፈጥሮ ሀብታችን ይሆናል::


### ስለሮቦቷ ሶፍያ

የሶፍያ ወደ ኢትዮጵያ መምጣትና አማርኛ መሞከር የሚቀጥለውን የቴክኖሎጂ ዘርፍ ለመረማመድ፣ ለመተዋወቅና ለመገልገል ያለንን ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ የሚያፋጥን ጉልበት ነው::

እንደተነገረኝ የሶፍያ ከ60 ፐርሰንት በላይ የሶፍትዌር ሥራው የተከናወነው በኢትዮጵያውያን ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ ጭንቅላት ያላቸው ወጣቶች፤ አሁን ዓለም ላይ ያለውን የመጨረሻውን ቴክኖሎጂ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መለማመድ መሞከር የጀመሩና ከሌሎች ዓለም ጋር ተገናኝተው ሶፍያን መፍጠር የቻሉ ብሪሊያንት ልጆች አሉ::

# ያልተበረዘውና ያልተከለሰው የኢትዮጵያውያን ማንነት ለልኬት መሠረት ሆኗል።

## ድምጻዊ ሊዛ ብዙ



ብሩክ መኮንን



*ድምጻዊ ሊዛ ብዙ*

የ23 ዓመቷን ኢትዮ-እንግሊዛዊት የግጥምና የዜማ ደራሲ አቀንቃኝ የቅርብ ሰዎቿ ሲጠሯት ሊዛ ብዙ ይሏታል::

ገና በ15 ዓመቷ በሕልሟም ሆነ በውኗ አስባ የማታወቀው የሙዚቃ ባለሞያ ለመሆን የቻለችበት አጋጣሚ ተፈጠረ:: በምትማርበት የአዳሪ ትምህርት ቤት ዕድሜያቸው በአሥራዎች ውስጥ የሆኑ ልጃገረዶች የሙዚቃ ባንድ አባል በመሆን የክርስቲያን አጉሌራን “ኤ ቢዩቲፉል” የተባለ ዜማ ተጫወተች:: ከአንድ ሳምንት በኋላ ችሎታዋን የተረዱት የሙዚቃ ባለሞያዎች የመጀመሪያዋ ነጠላ ዜማዋን እንድትጫወትና እንድትቀረጽ አደረጓት::

ሊዛ ብዙ፣ ከሕፃንነቷ ጀምሮ የቤት እንስሳትን መንከባከብና ብዙውን ጊዜዋን ከእነርሱ ጋር ማሳለፍ ስለምትወድ፤ ስታድግ የእንስሳት ሐኪም ለመሆን ነበር የምትመኘው:: “ምኞትና የሕይወት አቅጣጫ የተለያዩ ናቸው” እንዲሉ በያዝነው የአውሮፓውያን ዓመት የለቀቀችው “ዳይመንድ” የተባለው ዘፈኗ 225 ሚሊዮን የሚጠጋ አድማጭ ጋራ ለመድረስና ተወዳጅ ለመሆን በቅቷል:: እናም ሊዛ ብዙ ከአሁን ወዲያ “ሙዚቃ ሕይወቴ ሆኗል” ብላ በእርግጠኝነት ትናገራለች::

ከኢትዮጵያዊት እናቷ ጋር በተደጋጋሚ ለእረፍት ወደ ኢትዮጵያ እንደምትጓዝ የምታገረው ሊ ብዙ በእርግጠኝነት በሙዚቃው ዘርፍ ለአንጋፋነቷና ለስኬቷ ዋና መሠረት የሆናት “ያልተበረዘውና ያልተበላሸው የኢትዮጵያውያን ማንነት” ነው ትላለች::

“ኢትዮጵያ ውብ ሀገር፣ ውብ ሕዝብ ያላት ሀገር ናት:: ከዚያ በመወለዴ እኮራሁ፤ በኢትዮጵያ በሚኖረኝ ቆይታዬ ገና ወዳልተደረሰበት ወደሌላ ዓለም የሄድኩ ያህል፤ ምናቤ ሁሉ አዳዲስ ነገሮችን ማሰላሰል ይጀምራል::

“ግጥም መጻፍንና ማንጎራጎርን የበለጠ የወደድሁትና የጀመርሁት፣ በኢትዮጵያ ከእናቴ ቤተሰቦች ጋር በማሳልፈው የእረፍት ጊዜ ነው፤ ዓለምን የማይበት መነጽር እዚያ ስሆን ይቀየራል::

“ኢትዮጵያውያን መዝፈን፣ መደነስ ይወዳሉ፤ የትም ቦታ ሙዚቃ ሲጫወቱ ታያለህ፤ ለዚህም ነው መሰለኝ ወደ ሙዚቃ እንድሳብ የሆንሁት::

“በሙዚቃ ሕይወቴ ልዩ ቦታ ያላቸውና ተጽዕኖ አድርገውብኛል የምላቸው የነማርቪንጌ ኤም ዋይን ሐውስ እና የብላክ ኪስ ሥራዎች ናቸው::

“ማርቪንጌይ ሁልጊዜ የሕይወትን ጨለማውን ጎን ነው የሚያሳይህ፤ በሕይወትህ፣ በኑሮህ የሚያጋጥምህን ፈተናና ውጣ ውረድ ሲነግርህ፤ ሁልጊዜ በውስጥህ የተስፋ ብርሃን ይዘህ እንድትንቀሳቀስ ያሳስብሃል::

“ኤም ዋይን ሐውስ ልክ እንደ ማርቪንጌ እውነቱን ስትነግርህ የምትጠቀምበት የተለየ ቅላጼና የዜማ አወጣጧ ቡቡ እና ሁልጊዜ ስሜታዊ ያደርገኛል::

ስለማንነቷ፣ ስለፍቅር ሕይወቷ እና ወደ ዝናው መሰላል እንዴት ለመውጣት እንደቻለች ስትጠየቅ ሊዛ

“በምማርበት አዳሪ ትምህርት ቤት ባለ የልጃገረዶች ሙዚቃ ባንድ ውስጥ ስሞካክር የተመለከቱና ችሎታዬን እንዳወጣው ያበረታቱኝ የነበሩ የሙዚቃ መምህሮች የመጀመሪያ ነጠላ ዜማዬን አስቀርጸውልኝ ለአድማጭ አደረስሁ፤ ይህንን የመጀመሪያ ሥራዬን የሰማው አያን ባርተን የተባለ ፕሮዲዩሰር አፈላልጎ አገኘኝ::

“ከዚያም በመኖሪያ ቤቱ በሚገኝ የአትክልት ስፍራ ጥግ ላይ ያለን ታዛ ወደስቱዲዮነት ቀይሮ ከሚሠራው አያን ባርተን ጋር ተግባባን፤ ወዲያው አብረን መሥራት ጀመርን::

““ዳይመንድ” ለተባለው አልበምም አንድ ዘፈን እንዳቀነቅን አዘጋጀኝ፤ በደስታ አጠናሁት፤ ከቀናት በኋላ በሁለት ሰዓት ውስጥ ተቀርጾ ተጠናቀቀ::

“በዚህ አጋጣሚ ነው ስለእኔ ማወቅ፣ ማሰብ የጀመርሁት:: ያደግሁት በኢትዮጵያዊት እናቴ እና ወግ አጥባቂ በሆነው አባቴ የቅርብ ክትትልና ጥበቃ ስለሆነ፤ በውስጤ እንዳሻኝ ባለመሆኔ የሚሰማኝ የተዘበራረቀ ስሜት ነበር፤ ከቤቴ ወጥቼ ብቻዬን ስንቀሳቀስ ልክ ከወጥመድ ያመለጠች ወፍ ያህል ከመሆን ስሜት ጋራ ለግጥም የሚሆኑ ሐሳቦች በውስጤ ሲተራመሱ ይታወቀኛል:: ያኔ ወረቀት ይገኔ እጽፋለሁ፤ ያም ሆኖ በውስጤ ያለውን አቅምና ችሎታ አላውቅም ነበር:: አየን ….ምስጋና ይድረሰው::

“ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ ባሳልፍም፣ ለገና በዓል ሰሞን ከእናቴና ከወንድሜ ጋራ ስሔድ በነበረኝ ቆይታ በኢትዮጵያ እድሜያቸው በዐሥራዎቹ የሆኑ በርካታ ልጃገረዶች በአጠቃላይ ሕይወትንና ዓለምን እንዴት እንደሚመለከቷት በሙዚቃ ለመግለጽ ከሚያለማምደው ስቱዲዮ ሳሙኤል ከተባለ በጎ አድራጊ ድርጅት ጋር የተወሰኑ ቀናትን አሳልፌ ነበር::

“እነዚህ ሕፃናት ስሜታቸውንና ችሎታቸውን ከመጠቀም በቀር ስለዘመናዊ ሙዚቃ ምንም ሳያውቁ ተሰጥኦዋቸውን ለመጠቀም ሲሞክሩ ማየት በአዲሱ ትውልድ ውስጥ ያለውን ትልቅ ተስፋና ራዕይ እንድረዳ አድርጎኛል::

“የእኔን የሙዚቃ ሥራዎች በአሜሪካ ያስቀረጹት የሶኒ ሪድ ሚዩዚክ ፕሮዲውሰሮች፤ ታምራ ሆርቶን የተባለች ከኢትዮጵያ አንድ ልጅ በማደጎ ወስዳ የምታሳድግ አሜሪካዊ በምታደርግላቸው የገንዘብ ድጋፍ ባለፈው ዓመት ለሠሩት ፊልም ማጀቢያ ሙዚቃ ሠርቼላቸዋለሁ፤ እናም ከዚህ የበለጠ ኢትዮጵያውያን ታዳጊ ሴቶች በተሰጥኦዋቸው ተጠቃሚ ሆነው የተሻለ ሕይወትና ስኬት ላይ እንዲገኙ ተሳትፎዬን ከዚህ የበለጠ ለማሳደግ እሠራለሁ::

“‘ዘፋኝ ባትሆኚ ምን ትሆኛለሽ?’ ብለው ብዙ ሰዎች ይጠይቁኛል፤ አስቤው አላውቅም ስላቸው የሚገረሙ አሉ:: እኔ ግን አዳዲስ ሐሳቦችን በማፍለቅ፣ ሰዎች የተሻለ ነገ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት አልማለሁ፤ ለሀገሬ ለኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶቼ እንዲሁም ለመላው የዓለም ማኅብረሰብ የተሻለ ዓለምን ለመፍጠር እንሥራ እላለሁ::

ካለፉት ሁለት ሦስት ዓመታት ወዲህ በሙዚቃ ሥራዎቿ በአውሮፓና በአሜሪካ የሙዚቃ አፍቃሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትን እያገኘች የመጣችው ኢትዮ-ብሪታንያዊቷ ሊዛ ብዙ፤ ቢቢሲ፣ ወጣት ድምጻውያን የሙዚቃ ባለሞያዎችን ለማበረታታት በሚያደርጋቸው ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በመገኘት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ አንጸባራቂ ኮከብ ስምና ዝናዋ በመግነን ላይ ነው::

በዓለም አቀፍ የሙዚቃ አፍቃርያን ዘንድ ተደማጭ የሆነችው ሊዛ ብዙ፤ በቀጣይ የራሷን አሻራ ለማሳረፍ ሌት ተቀን ከመሥራት መቼም ወደኋላ እንደማትልና ለአድማጮቿም በቀጣይ ምርጥ ሥራዎችን ይዛ እንደምትመጣ በደስታ ትገልፃለች::

# ሰኔ ወር በታሪክ ውስጥ

## ሰኔ 1 ቀን 1932

የፋሺስት ኢጣልያ ጦር ከደብረ ወርቅ ብዙ ጓዝና መሣሪያ ጭኖ ወደከቸር ሲጓዝ፣ በበላይ ዘለቀ በሚመራው የአርበኞች ጦር የደፈጣ ውጊያ ገጥሞት፣ በርካታ የኢጣልያ ጦር አባላት ሙትና ቁስለኛ ሆነው፣ አርበኞችም ድል አድርገው ብዙ የጦር መሣሪያ ማረኩ፡፡

## ሰኔ1 ቀን 1956

በኢትዮጵያ የመኪና መንዳት መስመር ከግራ ወደ ቀኝ እንዲቀየር ተደረገ፡፡

## ሰኔ 2 ቀን 1961

የኢትዮጵያ መሪ የነበረው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ የሀገሪቱን ሰላም በማናጋት መንግሥትን በኃይል ለመገልበጥ ከውጪ መንግሥት የተገኘ የገንዘብ እርዳታ በመጠቀም ተንቀሳቅሳችኋል ባላቸው ተማሪዎች ከበደ፣ ሄኖክ ክፍሌና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የሠባት ዓመት ፅኑ እስራት ፈረደባቸው፡፡

## ሰኔ 11 ቀን 1966

በኢትዮጵያ አብዮትን ለመቀልበስ አምፀዋል የተባሉ የአየር ኃይል አባላት የመሸጉበትን የደብረ ዘይት አየር ኃይል ጦር ሰፈር ከተቆጣጠረው የአየር ወለድ ጦር ጋር በተፈጠረ ግጭት በሁለቱም ወገን ጉዳት ደረሰ፡፡

## ሰኔ 11 ቀን 1966

የኤርትራ ነፃነት ግንባር መጋቢት 19 ቀን 1966 ኤርትራ ውስጥ ከጠለፋቸው አምስት የቴናኮ የነዳጅ ኩባንያ የነዳጅ ፍለጋ ባለሙያዎች መካከል ካናዳዊ ዜግነት ያለውን የሄሊኮፍተር አብራሪ በዚህ ዕለት ከእገታ ለቀቀ፡፡

## ሰኔ 11 ቀን 1936

በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን መልዕክተኛ ብላታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን በሳንፍራንሲስኮ ከተማ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ምሥረታ ሥነ ሥርዓት ላይ ሀገራቸውን በመወከል የቃል ኪዳን ሰነድ ፈረሙ፡፡

## ሰኔ 20 ቀን 1928

በኢትዮጵያውያን ወጣቶች የተመሠረተው የጥቁር አንበሳ ጦር አባላት በነቀምት ወለጋ አካባቢ አርፈው የነበሩ የኢጣልያን የጦር አውሮፕላኖችን አወደሙ፡፡

## ሰኔ 20 ቀን 1951

የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ፣ ካይሮ ላይ በተካሄደ በዓለ ሢመት በግብፁ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ ተቀብተው የፓትርያርክነቱን ዘውድ ደፉ፡፡

## ሰኔ 21 ቀን 1966

የየካቲትን አብዮት ተከትሎ የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴን አዲስ አበባ ውስጥ ማቋቋማቸውን ይፋ አደረጉ፡፡

ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ በሚል ስያሜ ከወራት በኋላ ወደሥልጣን ይወጣል፤ ይህም አስተባባሪ ኮሚቴ በዚያው ዕለት በአዲስ አበባ የሚኙትን ሁለቱን የሬዲዮ ጣቢያዎችና ሌሎችንም ቁልፍ ቁልፍ ሥፍራዎች በወታደራዊ ቁጥጥር ሥር አዋለ፡፡

ከዚያ ቀን ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ተፈፃሚ የሚሆን ከምሽቱ አምስት ሰአት ጀምሮ መንቀሳቀስ እንደማይቻል የሚደነግግ የሰአት እላፊ ገደብ ደነገገ፡፡

## ሰኔ 23 ቀን 1928

የኢጣልያ ጦር በኃይል ኢትዮጵያን ከያዘና ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተሰደዱ በኋላ፣ በጄኔቭ በሚገኘው የሊግ ኦፍ ኔሽን ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት፣ የኢጣልያ ፋሺስት ጦር በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየፈፀመ ያለውን ግፍና በደል በዝርዝር በማቅረብ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አቤቱታ አቀረቡ፡፡

## ሰኔ 29 ቀን 1955

የፖርቹጋል መንግሥት በአፍሪካ ባሉት የተለያዩ ቅኝ ግዛቶቹ የሚያደርሰውን ጭቆናና የመብት ረገጣ በማውገዝ በጊዜው ነፃ የወጡ የአፍሪካ ሀገራት ከፖርቹጋል ጋራ ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አቋርጠው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም ከአፍሪካውያን ጎን በመቆም የትግል አጋርነቱን ለማሳየት ከፖርቹጋል ጋር የነበረውን ዘመን ያስቆጠረ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት አቋረጠ፡፡

## ሰኔ 11 ቀን 1965

በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል የተፈጠረውን ግጭትና ወታደራዊ ፍጥጫ በተመለከተ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ለሁለት ቀናት ለመወያየት የወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበርና የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት ጃፋር አል አሜሪ አዲስ አበባ ገቡ፡፡

## ሰኔ 11 ቀን 1616


አባ ዝሮም ሎቦና ሌሎችም የፖርቹጋል ሚሲዮናዊያን ከቀንቀዝ ተነስተው በስድስተኛው ቀን በቀድሞ ስሟ "ማይጓን" ትባል ወደነበረችውና በኋላ ላይ ፖርቹጋላውያንን ለማስታወስ ለአቡነ ፍሬምናጦስ ማስታወሻ ከአድዋ አጠገብ "ፍሪምና" ብለው ከሰየሚት ሥፍራ ደረሱ፡፡

## ሰኔ 6 ቀን 1974

በአርሲ ክፍለ ሀገር፣ በበቆጂ ከተማ፣ እውቁ ኢትዮጵያዊ ሯጭ ቀነኒሳ በቀለ ተወለደ፡፡

## ሰኔ 1 ቀን 1815

የሸዋው መርዕድ አዝማች ወሰን ሰገድ አርፈው በቀንዱ ጊዮርጊስ ተቀበሩ፤ ልጃቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አልጋውን ወረሱ፡፡



ፍቅሩ ኪዳኔ

# ለ2026ቱ የዓለም ዋንጫ ሦስት ሀገራት ተመረጡ



በመስኮብ ተሰብስቦ የነበረው የፊፋ ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ. በ2026 የሚከናወነውን የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ውድድር እንዲያዘጋጁ ዩናይትድ ስቴት፣ ካናዳና ሜክሲኮን በ134 ድምጽ መርጧል:: ተፎካካሪ የነበረችው ሞሮኮ 65 ድምጽ አግኝታለች:: ከአውሮፓ 11 አገሮች ለሞሮኮ ድምጽ ሰጥተዋል:: እነርሱም ፈረንሳይ፣ ጣልያን፣ ቤልጂየም፣ ሆላንድ፣ ሉክሰምበርግ፣ ሰርቢያ፣ አልባኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ኢስቶኒያ፣ ቱርክና ቤላሩስ ናቸው:: ከአፍሪካ አገሮች በመንግሥቶቻቸው ትዕዛዝ ወይም በራሳቸው ጥቅም የተነሣ ለሞሮኮ ድምጽ ያልሰጡት ቤኒን፣ ቦትስዋና፣ ጊኒ፣ ሞዛምቢክ፣ ናሚቢያ፣ ላይቤሪያ፣ ሌሴቶ፣ ሴራሊዮን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ካፕቬርዴና፣ ዚምባብዌ ናቸው:: የጊኒው ተጠሪ መሣሪያው ተሳስቶ ነው እንጂ፣ እኔ ለሞሮኮ ነው ድምጽ የሰጠሁት በማለት ይከራከራል:: የርሱ መሣሪያ ብቻ ያልሠራበት ምክንያት ግልፅ ባይሆንም:: ካሁን ቀደም ሞሮኮ ኤቦላ የሚባለው በሽታ በምዕራብ አፍሪካ የፈነዳ ጊዜ የአፍሪካን ዋንጫ ውድድር አላዘጋጅም ማለቷ ይታወሳል:: ታዲያ አሁን ድምጽ ያልሰጡትን አገሮች ዝርዝር አንዱ ቀልደኛ ዐይቶ "ሦስቱ የኤቦላ ሀገሮች ጊኒ፣ ላይቤሪያና ሴራሊዮን ሞሮኮን አልደገፉም" በማለት አፊዟል::

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ብዙ ጊዜ ለአፍሪካውያን ዕጩዎች ድጋፍ ቢሰጥም ቅሉ በምርጫው ወቅት ግማሹ የአፍሪካ ወኪሎች በልዩ ልዩ ምክንያት፤ በተለይ በጉቦ በመታለል ድምፃቸውን ለአፍሪካዊዋ ዕጩ እንደማይሰጡ ለመገንዘብ ተችሎ ነበር:: መስኮብ ላይ ግን ከሌላው ጊዜ የተሻለ የአንድነት መልክ ለማየት በቅተናል:: ሆኖም ለወደፊት የሚያዋጣው ልክ እንደ ፊፋ ምርጫ ማን ለማን ድምጽ እንደሰጠ በይፋ የሚገለጽበት ወቅት ሲሆን ነው::

ሞሮኮም እ.ኤ.አ. በ2017 በአዲስ አበባ ላይ በተከናወነው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለተካፈሉት ኢንቨሎፕ አድላ ስለነበረ አንዳንዶቹ ቢከዷትም ሌሎቹ ቃላቸውን በመጠበቅ ድምጽ ሰጥተዋል:: የኢትዮጵያ መልክተኞች አዲስ ስለሆኑ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ጥያቄ መሠረት ሞሮኮን ደግፈዋል:: ስብሰባም እንዴት እንደሚካሄድ ሳይማሩ አልቀሩም:: የነርሱ ምርጫ ስድስት ወር ፈጅቷልና::

ሞሮኮ ወደ አፍሪካ አንድነት ድርጅት አባልነት ከተመለሰች ጀምሮ አልጄሪያንና ሰሃራዊ ሪፐብሊክን ለማሳጣት አፍሪካ ውስጥ ብዙ ዓይነት የኢኮኖሚና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ታካሂዳለች:: ሞሮኮ የአፍሪካን እግር ኳስ ፌዴሬሽንም በአንድ ደካማ የማዳጋስካር ተወላጅ አማካይነት ትቆጣጠራለች:: በመተዳደሪያ ደንቦች ውስጥ ሳይመዘገብ የሦስተኛ ም/ፕሬዝዳንት ስፍራ በመፍጠር ለሞሮኮው ወዳጁ የሰጠው የካፍ ፕሬዝዳንት አህመድ ነው::

በጣም የሚያስገርመው ካታር ሞሮኮን ስለደገፈች ሳውዲ አረቢያ፣ ባህሬን፣ ኩዌትና ዩናትድ አረብ ኤምሬት ድምፃቸውን የሰጡት ለአሜሪካኖቹ ነው:: ኦማን ግን ሞሮኮን ደግፋለች፤ ሶሪያም እንደዚሁ:: ከዶናልድ ትራምፕ ጋር ሲሳሳቁ የከረሙት ሰሜን ኮሪያዎች ልክ እንደ ቻይና ሞሮኮን ደግፈዋል:: በጠቅላላው 12 ሀገሮች ናቸው ከእስያ ድምጽ የሰጡት::

ሌላው አስገራሚ ሁኔታ የሞሮኮን ዴሌጋሲዮን አንቀበልም ያለው የደቡብ አሜሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን፤ ድምጽ አሰጣጡ ላይ ብራዚል ከሁሉም ተለይታ ሞሮኮን መርጣለች:: ሁለቱን ተወዳዳሪዎች አልፈልግም ያለው የኢራን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሲሆን፤ ድምጽ ከመስጠት የተቆጠቡት ስፔን፣ ኩባና ስሎቬኒያ ናቸው::

ይህ ገና ከስምንት ዓመት በኋላ በ48 ቡድኖች ተካፋይነት የሚከናወነውን የዓለም ዋንጫ ውድድር ለማዘጋጀት ዕጩ ሆና የቀረበችው ሞሮኮ አቅሙና ችሎታው ስላላት አይደለም:: በወረቀት ላይ ሁሉም ሊጭር ይችላል:: ለምሳሌ ለውድድሩ 14 ስቴዲየም ያስፈልጋል:: ሞሮኮ ስድስት ቢኖራት ስምንት አዳዲስ መገንባት ይኖርባታል:: በጠቅላላው 15 ቢሊየን ዶላር ያስፈልጋታል:: የዓረብ አገራት ይረዱኛል የሚል ምኞት ሳይኖራት አይቀርም:: ነገር ግን አረቦች እርስ በራሳቸው በመነካከስ ስለተኮራረፉ እንኳን ሞሮኮን ይቅርና ፍልስጥኤምንም አይረዱም:: ሞሮኮ ድጋፏ ዝቅተኛ እንደሚሆን የተገመተው ለዛ ቢሱ ዶናልድ ትራምፕ "አሜሪካንን የማይደግፉ የኛን ዕርዳታ አያገኙም" ብሎ የተናገረ ዕለት ነው:: ደግነቱ ሦስቱ የአሜሪካ አገሮች የዓለም ዋጫን ለማዘጋጀት ምንም የሚቸግራቸው ነገር የለም:: እውነቱን ለመናገር መስከረም ሳይጠባ ለማዘጋጀት ይችላሉ::

ሜክሲኮ እ.ኤ.አ. በ1970 እና በ1986 ያዘጋጀቻቸውን የዓለም ዋንጫዎች ውድድር ከጋሼ ይድነቃቸው ተሰማ ጋር ሆኜ ተመልክቻለሁ:: ዩናይትድ ስቴትስ እ.ኤ.አ በ1994 ያዘጋጀችውንም ሆነ፤ ካናዳ በ1976 ሞንትሪያል ጀምሮ፤ 1988 ካልጋሪ፤ 2010 ቫንኩቨር የተከናወኑትን የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ስለታዘብኩ እነኝህን ሀገሮች አቅሙም ችሎታውም እንዳላቸው ለማረጋገጥ እወዳለሁ:: ከዚህ በላይ የአሜሪካኖቹ አዘጋጅ ኮሚቴ 14 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ለፊፋ አስገባለሁ በማለት ቃል ገብቷል:: ሞሮኮ ግን ሠባት ቢልዮን ነው የተመነችው::

ፊፋ በራሽያ በሚካሄደው ውድድር ስድስት ቢልዮን ዶላር ትርፍ ማግኘቱንም አስታውቋል:: ከፍተኛው ገቢ የሚገኘው ከቴሌቪዥን ጣቢያዎች ኪራይ መሆኑ ግልጽ ነው:: ይኼም ሆኖ የካታር የስፖርት ቴሌቪዥን አሰራጭ ኩባንያ ቢ-ኢን ስፖርት የዓረብ ሀገራትን ኮንትራት የገዛባቸው እነ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ግብፅና ሌሎች ድርሻችንን አንከፍልም በማለት ግብግብ ተያይዘዋል:: አንድ የግብጽ ድርጅት ለፊፋ ማስጠንቀቂያ ከመስጠቱም በላይ ዛምቢያ የሚገኘውን ኮሜሳ የተባለውን ድርጅት እንከስሃለን በማለት ዝተዋል:: ለማንኛውም ውድድሩ እንደቀጠለ ነው:: የካይሮ ፉከራ እኛንም አሰልችቶናል::

# ታሪካዊ ቅርስን ማጥፋት...

**ሠሎሞን ለማ ገመቹ**

በዚህ ጽሑፍ የምናነሣው የማፍረስ ዘመቻ የተቃጣበትን ታሪካዊውን የሼኅ አሕመድ ሳላህ ሕንፃ ጉዳይ ነው:: ይህ ሕንፃ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝና በመልሶ “ማልማት” ስም እንዲጠፋ የተፈለገው፤ በታሪካዊ ቅርስነቱ ግን እውቅና የተሰጠው ነው:: ሕንፃው በተለምዶ ሰንጋ ተራ ተብሎ ይታወቅ በነበረው ሠፈር፤ ከዋቢ ሸበሌ ሆቴል አጠገብ ይገኛል:: ለዚሁ ሕንፃ እውቅና የተሰጠውም፤ በአዲስ አበባ ከተማ የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር፣ የባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት፤ በአዲስ አበባ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ እና በፌደራል መንግሥቱ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን መ/ቤት አማካይነት ነው::

በሼኅ አሕመድ ሳላህ አልዛሕሪ መኖሪያ ቤትነት የሚታወቀውና ሼሁ “ለሆስቴልነት እንዲያገለግል” ብለው እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1921 ዓ.ም. ያስገነቡትና 89 ዓመታትን ያስቆጠረው፤ አሁንም በአስተማማኝ ይዞት ላይ የሚገኘው ይኸው ታሪካዊ ሕንፃ፤ የማይንቀሳቀስ ታሪካዊ ቅርስ ሆኖ፤ በሕጋዊ አካል በኅዳር 27 ቀን 2006 ዓ.ም. ተመዝግቧል:: ከመመዝገቡም በፊት ጉዳዩ ከሚመመለከታቸው ተቋማት ባለሙያዎች ተልከው ሕንፃውን በመመልከት፣ አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ፣ “ሕንፃው ያለውን ታሪካዊ ፋይዳ፣ የተሠራበትን ዘመንና ሁናቴ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ በኪነ-ሕንፃ ይዘቱ በቅርስነት መመዝገብ ያለበት መሆኑን በመግለጽ” ሙያዊ ሐሣባቸውን አቅርበዋል:: በቀረበው ሙያዊ ሐሣብ መነሻም፤ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፣ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት በኩል፤ ታሪካዊ ቅርስ የሆነው የሼኅ አሕመድ ሳላህ ሕንፃ፤ ታሪካዊ ቅርስ መሆኑ በመታወቁ “አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ” ይደረግለትም ተብሏል::

የዚህ ሕንፃ ታሪካዊ ቅርስነት አዲስ አበባ በተቆረቆረች ሰሞን የተገነባ ሕንፃ መሆኑ ብቻ አይደለም:: በትውልድ የመናዊ የሆኑት፤ ሀብት፣ ንብረትና ቤተሰብ አፍርተው፤ በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሁነኛ ባለውለታ ሆነው በኢትዮጵያዊ ዜግነት መንፈስ በመኖራቸው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አድናቆትን ያተረፉት የሼኅ አሕመድ ሳላህ አልዛሕሪ፤ ዘመን የማይሽረው ተግባር የተገለጸበት ወይም የተከወነበት በመሆኑ ነው:: ሼኅ አሕመድ ሳላህ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ፤ ዘመናዊ የሀገርና የውጭ ንግድ መርሆዎችን ለኢትዮጵያውያን አስተዋውቀዋል:: ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በግፍ በወረረችበት ጊዜም፣ ሀገራችን ከየመን እና ከሌሎች የዓረብ ሀገራት ጋር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖራት ብዙ ደክመዋል:: ድካማቸውም ፍሬ በማፍራቱ በዚያን ወቅት ኢትዮጵያ ተጠቃሚ መሆን ችላለች:: ያም ብቻ ሳይሆን ሼኅ አሕመድ፤ በአምስቱ ዓመታት የዓርበኝነት ዘመን ለኢትዮጵያ ነፃነት ተፋላሚዎች ከውጭ የሚላከውን የጦር መሣሪያ አስርገው በማስገባትና ዛሬ በ“ልማት” ስም እንዲፈርስ በሚፈለገው ታሪካዊ ሕንፃ ውስጥ በሠዋራ ሥፍራ በማስቀመጥ፣ ከተቀመጠበትም ሥፍራ በተጠና ቀንና ሰዓት እየወጣ ለኢትዮጵያ ዓርበኞች እንዲደርስ የሚደረግበትን ዕቅድ በመንደፍና ተግባራዊም በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል:: እናም ከዚህን መሰሉ እውነት አንፃር ሲመዘን፣ “በመልሶ ግንባታ” ሰበብ ይፍረስ የተባለው የሼኅ አሕመድ ሳላህ ሕንፃ፤ ታሪካዊ ቅርስ መሆኑ፣ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያስፈልገው ብቻም ሳይሆን ዛሬም ይሁን በመጪዎቹ የኢትዮጵያ ዘመናት፤ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለኢትዮጵያ ቀላል ነው ተብሎ ሊገመት የማይችል ገቢ የሚያስገኝ እንደሆነ ለመገመት የሚከብድ አይሆንም::


ይሁንና በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገበው፣ እውቅና የተቸረውና አስፈላጊው ጥበቃና ክብካቤ ይደረግለት የተባለው ዕድሜ ጠገቡ ሕንፃ፤ “ለልማት ሲባል ይፈርሳል” ከመባሉም ባለፈ “በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገበው በሥህተት ነው” በሚል አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት፤ የአፍራሽ ግብረ-ኃይሎች ዘመቻ ተቃጥቶበታል:: በተቃጣው ዘመቻም የታሪካዊው ሕንፃ የላይኛው ክፍሎች በከፊል ፈርሰዋል:: ጅምር የማፍረስ ዘመቻው የተገታውም፤ የሼኅ አሕመድ ሳላህ አልዛሕሪ ወራሽ ቤተሰቦች ጉዳዩ ይመለከተዋል ላሉት ፍርድ ቤት በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታ በማቅረባቸው፣ ታሪካዊ ቅርሱን የማጥፋት ዘመቻው እንዲቆምላቸው በመጠየቃቸው ነበር:: በወራሾቹ በኩል አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤትም፤ የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ “መንግሥት ቅርሶችን የመጠበቅ ግዴታ ያለበት” መሆኑንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጋዊ ነጥቦች ጠቅሶ፤ በመጋቢት ወር 6ኛ ቀን 2008 ዓ.ም፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 መሠረት ሁከት እንዲወገድ ውሳኔ በመስጠቱ ነው:: እንዲህም ሆኖ ግን “ታሪካዊ ቅርስ የሆነው ሕንፃ መፍረስ የለበትም! መፍረስ አለበት…” የሚለው ክርክር በሕግ ፊት ቀጥሏል:: ጉዳዩን ሲመለከት የቆየው ፍርድ ቤትም ሰኔ 13 ቀን፣ ባስቻለው ችሎት ተለዋጭ ቀጠሮ ለሐምሌ 3 ቀን፣ 2010 ዓ.ም ሰጥቷል::

ለማንኛውም በሕግ ፊት ሊገኝ የሚችለው ምላሽ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የዚህ ታሪካዊ ቅርስ መፍረስ አለመፍረስ ጉዳይ፤ የኢትዮጵያ ባሕል፣ ቅርስና ታሪክ ያገባናል የሚሉ ወገኖች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጉዳይ መሆኑ ቸል ሊባል አይገባውም:: የሼኅ አሕመድ ሳላህ ወራሾች ፍትሕ ፍለጋ ሕግ ፊት የቆሙትም፤ ታሪካዊ ቅርሱ ተጠብቆና ተገቢውን ክብካቤ አግኝቶ ይኑር በሚል ቀና አስተሳሰብ እንጂ፣ “ሕንፃው በመፍረሱ ምክንያት እናገኘው የነበረው ግላዊ ጥቅም ቀረብን” በሚል ቅሬታ እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል:: ስለዚህ አንድ “ባለሥልጣን” ነኝ ባይ ግለሰብ ተነሥቶ ‹‹በሥህተት የተመዘገበ ነው›› የሚል ደብዳቤ ስለፃፈ ብቻ፤ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል የተመዘገበና እውቅና የተቸረው ታሪካዊ ቅርስ “በልማት” ሰብብ መውደም የለበትም:: የነበረው ታሪክ እንደሚያስረዳው፤ የሼኅ አሕመድ ሳላህ ሕንፃ፣ ታሪካዊነቱ ለሼኁና ለወራሽ ቤተሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ነው:: ይሄንን ታሪካዊ ቅርስ ማፍረስ ማለትም ቢያንስ በአምስቱ ዓመታት የዓርበኝነት ዘመን ለኢትዮጵያ ነፃነት ሲባል የተከፈለውን ታላቅ የመሥዋዕትነት ታሪክ ማመሳከሪያ ሠነድ ማቃጠል ማለት መሆኑን ልብ ያለው ልብ ሊለው ይገባል:: የሀገራችንን ተፈጥሯዊና ታሪካዊ እሴቶች ለሀገራችንና ለሕዝቦቿ እድገት እናውል እየተባለ ባለበት ጊዜ፤ የቀደሙ ትውልዶችን ቅርስ ለማውደም መነሣት ከሀገር ጠላት ጋር ተደምሮ ሀገርን ከማውደም አይተናነስም::

በልማት ስም ታሪካዊ ቅርስን ማጥፋት ውጉዝ የመሆኑን ያህል፤ ለሕዝቧ ዕምነት፣ ነፃነትና ለነፃነትም ለተከፈለው ዋጋ፣ ለታሪኳ፣ ለባሕሏ፣ ለቅርሷ ሳይቆረቆሩ፤ “ኢትዮጵያን እንወዳለን! እንደመራለን” ማለትም ትርጉም የለውም::




*ታሪካዊው የሼኅ አሕመድ ሳላህ ሕንፃ፤ የማፍረስ ዘመቻ ሳይቃጣበት በፊት*



አሸናፊ ትርፌ

# የዐቢ.ይ ተቀባይነት እና የማኪ.ያቬሊ.ያኖቹ ጤናማ ያልሆነ አካሄድ

ጀርመናዊው ቀደምት ሶሲዎሎጂስት ማክስ ዌበር እንደሚለው፤ መሪዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኙት በሦስት መንገዶች ነው::

**አንደኛ** (Traditional Authority)፡- መሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ልምዳዊ አካሄዶችን ይጠቀማሉ:: ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆኑት በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነገሡ ነገሥታት የቅቡልነት ምንጫቸው ከዘር እና ከእምነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው::

አፄዎቹ የዘር ግንዳቸውን ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን ጋር ማያያዛቸውና ሥዩመ እግዚአብሔር ነን ማለታቸው ህዝቡ እንዲቀበላቸው አድርጎ ነበር:: ይህም አሠራር እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድረስ አዋጭ ነበር::

**ሁለተኛ** (Charismatic Authority)፡- ተቀባይነት ከመሪዎች ልዩ ብቃትና ሞገስ የሚነሣ ነው:: መሪዎች የተለየ ወይም አርአያ ሊሆን የሚችል ነገር ሲፈፅሙ ህዝቡ በፈቃደኝነት ይታዘዛቸዋል:: በዚህ ዓይነት መንገድ የህዝብን ተቀባይነት ካገኙት መካከል የህንዱ ማህተመ ጋንዲ እና የደቡብ አፍሪካው ኔልሰን ማንዴላ ተጠቃሽ ናቸው::

**ሦስተኛው** (Rational Legal Authority)፡- መሪዎች የሥልጣናቸው ምንጭ ሕግን (ምርጫ) መነሻ ያደረገ ሲሆን ተቀባይነት ያገኛሉ:: በዚህ አካሄድ ህዝቡ ፈቃደኝነቱን የሚያሣየው ለመሪው ሳይሆን ለተቀመጠበት ወንበር ነው::

ከእነዚህ መንገዶች ውጭ የተገኘ ሥልጣን ተቀባይነት እንደሌለው አስረድቷል::

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ተቀባይነት ያገኘ መሪና መንግሥት ላስቀመጣቸው ግቦች መሳካት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኃይልን ቢጠቀም ተቀባይነት አለው:: መንግሥትንም ከሌሎች ተቋማት የሚለየው ዋነኛ መሥፈርት ይህንን ኃይል የመጠቀም መብቱ ነው::

መንግሥት አስፈላጊ ሲሆን ይህን ኃይል በመጠቀም በድንበሩ ወስጥ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤ የዜጎችን ደህንነት ይጠብቃል፤ ሕግ ያስፈጽማል፤ ፍትሕ እንዲኖር ያደርጋል:: በአጠቃላይ መንግሥት የማይገባባቸው መስኮችና የማይሠራቸው ሥራዎች ጥቂት ናቸው:: እነዚህን የተዘረዘሩትን ሥራዎችም ሌሎች አካላት ሊሠሯቸው ወይም ኃላፊነት ሊወስዱባቸው ይችላሉ:: መንግሥት ከእንደዚህ ያሉ ተቋማት የሚለየው ሥራዎቹን ለመሥራትም ሆነ ወዳስቀመጣቸው ግቦች ለመድረስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኃይል መጠቀም የሚችል ብቸኛ ተቋም መሆኑ ነው::

ፖለቲካ ማለትም በፓርቲዎች ወይም በመንግሥታት መካከል ይህንን ፈቃድ ያለውን ኃይል ለመጠቀም የሚደረግ ጥረትና ፉክክር ነው:: ኃይልን ለማግኘትና ይዞ ለመቀጠል ወይም በክፍፍሉ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የሚደረግን ፉክክር እና ጥረት በሙሉ የሚያካትት ነው::

ይህን መነሻ በማድረግ የሀገራችንን ሁኔታ ስናይ፣ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን ጨምሮ የድሮዎቹ አፄዎች ሥዩመ እግዚአብሔር እና የሰሎሞን ዘር ነን በማለታቸው ህዝቡ ተከትሏቸዋል፤ ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ በኋላ የነበሩት መንግሥታት ግን፤ ሀገሪቷን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ያለህዝብ ተቀባይነት በጉልበት ብቻ እንደነበር ይታወቃል::

እንደዚህ ዓይነቱን መንግሥታዊ አካሄድ የበለጠ ለመግለጽ፤ ወደ ተጽዕኖ ወይም ጭቆና የቀረበውን ቃል ይጠቀማል:: ይህም የሚያመለክተው መሪዎች የሚያዙት ነገር ያለውን ተፈጻሚነት እንጂ ተቀባይነታቸውን አይደለም::

የደርግ መንግሥት ያለ ምንም ማስመሰል በጉልበት ሲገዛ፣ ኢህዴግ ደግሞ "በሕጋዊ መንገድ (በምርጫ) ሥልጣን የያዝሁ ስለሆነ፤ ተቀባይነት ያለኝ መንግሥት ነኝ" ቢልም ከማስመሰል የዘለለ የጠራ ምርጫ ያላካሄደ፣ ህዝቡም በፈቃደኝነት ታዝዞት የማያውቅ ነው:: ትእዛዝን ማስፈጸምም ሆነ ሥልጣን መያዝ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት መኖሩን አያረጋግጥም::

ይህን ሐቅ በሚቃረን መልኩ የአሁኑ የኢህአዴግ መሪ ጠ/ሚ ዐቢ.ይ፤ ከድርጅቱ ሕግን መሠረት ባደረገ ምርጫ ተመርጠው በመቀጠልም ያሣዩትን የተለየ ግለሰባዊ አቅምና አስተሳሰብ ምክንያት በማድረግ ህዝቡ ድጋፍ ሰጥቷቸዋል::

ይህ የጠ/ሚ ዐቢ.ይ ሕግንና ግለሰባዊ ብቃትን አዳምሮ የህዝብ ተቀባይነት ማግኘት፤ ጤናማ ያልሆነ ፍርኃት የለቀቀባቸው ማኪ.ያቬሊ.ያውያን አሉ:: ህዝብ ላይ መሣርያ ደግኖ የራስን ፍላጎት ብቻ ሲያስፈጽም የነበረ ቡድን በጠ/ሚ ዐቢ.ይ የፍቅር ስብከት ህዝብ መደመሙ አሳብዷቸዋል:: ከጭካኔ እና ማስፈራራት ውጪ ሥርዓት የማይገኝ የሚመስላቸው የማኪ.ያቬሊ ደቀመዝሙሮች፤ የጠ/ሚ ዐቢ.ይ ይቅር ባይነትና ሕጋዊ አካሄድ የማይቀመስ እሬት ሆነባቸው:: እንዲህ ዓይነቱን የሰላም ሰባኪ፤ ጠላት አድርጎ ማየት እና ዓላማውን ለማደናቀፍ መዶለት የአእምሯቸውን ጤነኝነት እንድንጠራጠር ያደርጋል::

ህዝብ መሪውን በመውደዱ ፍርኃት ውስጥ መግባት፣ የጦር ነጋሪትም መጎሰም ከዛሬ ጋር የማያስታርቅ የአእምሮ በሽታ ምልክት ነው:: "እንዋሐድ" ማለትስ በየት በኩል ነው በትግራይ ላይ የተጋረጠ አደጋ የሚሆነው? የለማ መገርሳ ዐቢ.ይን ማስቀደምስ ተምሳሌትነት ከመሆን ውጭ በምን ዓይነት እይታ ነው የሥልጣን ጥማት ተብሎ የሚተረጎመው? ህብረተሰቡ ጥሩውን ከመጥፎ፣ ክፉውን ከበጎ የሚለይበትን መመዘኛ መስፈርት ገልብጠው ካዩት ችግር ውስጥ እንዳሉ በቂ ማስረጃ ነው::

ሆቭላንድ እና ሲርስ የተባሉ አጥኚዎች መደናገጥ እና ፍርኃት ነገረኛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል:: ሌላው ታዋቂ ደራሲ ኤክሃርት ቶሌ "The power of now" በተሰኘውና ከሁለት ሚሊዮን ቅጂ በላይ በተሸጠው መጽሐፉ፤ "ተከስቶ የማያውቅ ነገር ወደፊት ይከሰታል ብሎ ፍርኃት ውስጥ የገባ ሰው፤ ዛሬን ለመኖር የማይችል ነው" ብሏል::

ስለዚህ ለውጣችን እንዲቀጥል፣ ሰላማችንም እንዲፀና እዚህ ፍርኃት ውስጥ ያሉ ሰዎች መላ ሊባሉ ይገባል:: እውቅና ያለው መንግሥት እያለ፤ ደስታና ኃዘን ለምን ይፈራረቁብናል? ገንዘቡንና ኢኮኖሚውን ይዘው አሻጥር ይሠራሉ:: "ለውጥ ማለት የአሮጌው መጥፋትና የአዲሱ መጀመር ነው" ብለን አሮጌዎቹን በየቀኑ እየተሰናበትናቸው ነው ስንል፤ መኖራቸውን እዚህም እዚያም በሚፈጥሩት ቀውስ ያሳዩናል:: ጭቆና ማለት እኮ ይሄው ነው:: ያለውን ኢኮኖሚያዊም ሆነ ወታደራዊ ኃይል ተጠቅሞ ትዕዛዜን ፈፅሙ ማለት ነው::

ሥልጣን ለመያዝ ከቀድሞው የሶማሊያ መሪ ከዚያድባሬ ጋር ከተወዳጁ፤ ሥልጣናቸውን ለማስመለስ ከሱዳኑ አልበሽር ጋር ተወዳጅተው ሀገር የመውረር አዝማሚያ እያሣዩ ነው ብሎ ህዝቡ መገመቱ አያስገርምም:: በማኪያቬሊ ደቀ መዝሙሮች ዘንድ ሥልጣን ካስገኘ ሀገርም ህዝብም ምንም ናቸው:: እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን እሹሩሩ ማለት እና ጊዜው የሚጠይቀውን ውሳኔ አለማድረግ የከፋ ችግር ያስከትላል::

ጠ/ሚ ዐቢ.ይም ቢሆኑ ህዝቡ ፈቃደኝነቱን ስላሣያቸው ሐሳባቸውን ከማስተዋወቅ ወደተጠናከረ መደበኛ የመንግሥት ሥራ መግባት አለባቸው:: የህዝቡን ደህንነት መጠበቅ እና ከስጋት ማላቀቅ ዋነኛ የመንግሥት ሥራ ነው:: ኃይል የመጠቀም መብቱም ህዝብ እና መሪውን ካልታደገ አይጠቅምም:: በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ራሱን ለመጠበቅ ህዝቡ መንቀሳቀሱ "ከለላ ሊሰጠን የሚችል መንግሥት የለም" ማለታቸው ነው:: እንዲያ ከሆነ "ያለእኛ ሰላም የለም፤ የጠ/ሚ ዐቢ.ይ መንግሥትም ሥርዓት ማምጣት አይችልም" የሚለው ዓላማቸው ይሳካል::



አቡ በከር ዓለሙ

# የድምፃችን ይሰማ ንቅናቄ ከትናንት እስከ ዛሬ

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከወርሃ ጥር፣ 2004 ዓ.ም. ጀምሮ በብቸኛው የሃይማኖት ተቋማቸው በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ውስጥ፤ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት በፈፀመውና እየፈፀመ ባለው ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነትና አሉታዊ ቁጥጥርን በመቃወም "ድምፃችን ይሰማ" የሚል መሪ መፈክር በማንገብ፤ ዓመታትን የወሰደ እልህ አስጨራሽ ሰላማዊ ትግል ያካሄዱ መሆናቸው የታወቀ ነው::

መንግሥት በዚህ በተጠቀሰው ተቋማቸው ውስጥ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ የሆነ ጣልቃ ገብነት መፈፀሙና አሉታዊ ቁጥጥር ማድረጉ ሳይበቃው፤ ጨርሶ ከአንድ መንግሥት በማይጠበቅ መልኩ፤ አንድ በሃይማኖት አንጃ (አል-አህባሽ) የታጠረ አስተምህሮ የተቋሙ እምነት ይሆን ዘንድ ቀጥተኛ የሆነ እርምጃ መውሰዱን ጭምር በመቃወም እረፍት የለሽ የሆነ ሰላማዊ ትግል ሲያካሄዱ ቆይተዋል::

በዚህ መልኩ ለዓመታት ሲያካሄዱ በቆዩት ሰላማዊ ትግል ምክንያትም ከመንግሥት በተሰነዘረ ጥቃትና አፈና ዘርፈ ብዙ መሥዋዕትነቶችን ከፍለዋል:: ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሕገ መንግሥቱ በመንግሥት አማካኝነት መጣሱን በመቃወም እምቢታን በማሳየታቸው ምክንያት ሊቆጠሩ የሚችሉ አያሌ ዋጋዎችን ከፍለዋል::

የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በሰነዘሩት ጥቃት ምክንያት ብዙዎች ተገድለዋል፤ ብዙዋችም የአካል ጉዳተኛ ሆነው እንዲቀሩ ተደርገዋል:: በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ነዋሪ የሆኑ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ለእስር ተዳርገዋል:: ሕዝበ ሙስሊሙ ያነሳቸውን ሕገ መንግሥታዊ የመብት ጥያቄዎችን በተደራጀ መልኩ አሰናድተው ለመንግሥት አቤት ለማለት የተዋቀሩ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት፤ በጉዳዩ ዙሪያ ከመንግሥት ጋር ፊት ለፊት ቀርበው፣ ተነጋግረውና ተወያይተው ሳለ፤ ከባድ በሆነው የፀረ-ሽብርተኝነት ዐዋጅ ተከስሰው፤ እንዲሁም ያለ ምንም ፍትሕና ርትዕ ተወንጅለው የዓመታት እስር በግፍ ተፈርዶባቸዋል:: በእስር ቤት በምርመራ ላይ እያሉም በቶርቸር አማካኝነት ኢሰብዓዊ ድርጊት ተፈፅሞባቸዋል:: በርካታ የሆኑ የሃይማኖት ሰባክያን ጋዜጠኞችና የመብት ተሟጋቾች ሀገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ተደርገዋል:: የኅትመት፣ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ኢስላማዊ የእርዳታ ድርጅቶች እንዲዘጉ ተደርገዋል::

በተከበሩና ፈፅሞ ሰላማዊ በሆኑ የሃይማኖት ሰባክያን ላይ በመንግሥት ቴሌቪዥን ሥማቸው በሐሰት እንዲጠለሽ ተደርጎ ፕሮፓጋንዳ ተሠርቶባቸዋል:: በመስጊዶችና ለዒድ ሶላት በታደሙ ንፁሐን ላይ ዘግናኝ የሆኑ ድብደባዎች በፀጥታ ኃይሎች ተፈፅሞባቸዋል:: ክብርና ፀጥታ የሚገባቸው መስጊዶች የፖሊሶችና የደህንነቶች የወከባና የሁከት መድረኮች እንዲሆኑ ተደርገዋል:: በርካታ በሆኑ ሙስሊም ነጋዴዎች ላይ መንግሥታዊ አሻጥር እንዲፈፀም ተደርጓል ወዘተ ወዘተ...

በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ብቸኛ ተቋም በሆነው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ውስጥ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መልኩ ጣልቃ ስለመግባቱና በምክር ቤቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ቁጥጥር ማድረጉን ሊያሳዩ ከሚችሉ ማስረጃዎችና እማኞች ውስጥ አንዱ፤ በዚሁ በግዮን መጽሔት በቅፅ 1፣ ቁጥር 9፣ ሰኔ 2010 መጣጥፍ ያስነበቡትና ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ በቅፅ 19፣ ቁጥር 962፣ ቅዳሜ ሰኔ፣ 16 ቀን 2010 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው፤ መንግሥት ፈፅሞብኛል ባሉት ግልበጣ ከሐላፊነታቸው የተነሡት፤ የቀድሞው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት የነበሩት ሸይኽ ኺያር መሐመድ አማን ሎዬ አንዱ ናቸው::

ሸይኽ መሐመድ፣ ምንም እንኳን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የመጅሊሱ ፕሬዝዳንት ለመሆን የቻሉ ቢሆኑም እርሳቸው እንደሚሉት መንግሥት ፈፅሞብኛል ባሉት ግልበጣ ከሐላፊነታቸው እስከሚነሡ ድረስ በሥራ ላይ በነበሩባቸው ሁለት ዓመታት መንግሥት በሕዝበ ሙስሊሙና በተቋሙ ላይ ምን ያህል መንግሥታዊ አሻጥር ሲፈፀም እንደነበር በዚሁ በግዮን መጽሔት ባስነበቡት መጣጥፍና በአዲስ አድማስ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ተንትነው አስረድተዋል::

እኚህ የዐይን እማኝ የሆኑት ሸይኽ መንግሥት ከሊባኖስና ከኢራን "አህባሽ" የተሰኘ ▶

**በመንግሥት ቀጥተኛ ተሳታፊነት የሚፈፅማባቸው ለአንድ ሃይማኖታዊ አንጃ ወገንተኛ በመሆን የተቋማቸው እምነት እንዲሆን በመንግሥት የሚፈፀመው ተገቢነት የሌለው ተግባር እንዲቆምና እንዲገታ ማድረግ አልተቻለም**

የእስልምና ሐራጥቃ አስመጥቶ የተቋሙ እምነት እንዲሆን መሥራቱን፤ የመጅሊስ አመራሮች ለእምነትና ለኃላፊነታቸው ሳይሆን የመንግሥት ተላላኪና ጉዳይ ፈፃሚ እንዲሆን መደረጋቸውን፤ መንግሥት በመጅሊሱ ውስጥ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ከፍተኛ መሆኑን፤ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በወቅቱ የዚህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሚኒስትር የነበሩት ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያምና ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ሙሉጌታ ውለታው፤ እንዲሁም በወቅቱ የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሽመልስ ከማል በቀጥታ በመጅሊሱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት አንድ የእስልምና ሐራጥቃ የመጅሊስ አስተምህሮ እንዲሆን ተፅዕኖና ጫና ያደርጉ እንደነበር፤ መጅሊሱ "መንግሥት ባስቀመጠለት አቅጣጫ ብቻ" እንዲጓዝ ከደህንነት ኃይሎች ዛቻና ማስፈራሪያ ይደርስባቸው እንደነበር፤ የተለያዩ የልማት ሥራዎች አቅደው እንደነበርና በመንግሥት ጣልቃ ገብነት እቅዳቸው እንደተደናቀፈባቸው …ወዘተ ዘርዝር አድርገው አስረድተዋል::

ሸይኹ እንዳሉት መንግሥት ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ውስጥ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ በሆነ አግባብ ያደርግ የነበረው ጣልቃ ገብነት በጣም ከፍተኛ ነበር:: አሁንም ጣልቃ ገብነቱ አለ:: መጅሊሱም መንፈሳዊና ልማታዊ ዓላማ ብቻ ሳይሆን ያለው የመንግሥትን ዓላማ የሚያራምድና የመንግሥት ጉዳይ አስፈፃሚ ነው::

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸውን ለማስከበር ቀደም ሲል በግርድፉ በተለፀው መልኩ ላለፉት ስድስት ዓመታት ያክል እልህ አስጨራሽ የሆነ ሰላማዊ ትግል ቢያካሄዱም፤ ባካሄዱት በዚህ ሰላማዊ ትግል ምክንያትም በርካታ ቁሳዊ፣ ሰብዓዊና ሥነ ልቦናዊ መሥዋዕትነትና ዋጋ ቢከፍሉም፤ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያነሷቸው ሕገ መንግስታዊ የመብት ጥያቄዎች ግን በቂና አግባብነት ያለው ምላሽ ሊያገኙ አልቻሉም::

አሁንም ሕገ መንግስቱ ያጎናፀፋቸውን የመደራጀት መብት ተጠቅመው ተቋማቸው የሆነውን ጠቅላይ ምክር ቤት በነፃነት ማደራጀትና ይህን ተቋም ከመንግሥት ተገቢነት የሌለው ጣልቃ ገብነትና አሉታዊ ቁጥጥር ነፃ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉበት መልካም ሁኔታ አልተፈጠረላቸውም:: ወይም አልተመቻቸላቸውም:: በመንግሥት ቀጥተኛ ተሳታፊነት የሚፈፅማባቸው ለአንድ ሃይማኖታዊ አንጃ ወገንተኛ በመሆን የተቋማቸው እምነት እንዲሆን በመንግሥት የሚፈፀመው ተገቢነት የሌለው ተግባር እንዲቆምና እንዲገታ ማድረግ አልተቻለም::

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች "ድምፃችን ይሰማ!" በተሰኘው ዝነኛ ሕዝባዊ ንቅናቄ እየተመሩ ከወርሃ ጥር 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ሲያካሂዱት የቆዩት "ሕገ መንግሥት የማስከበር ሰላማዊ ትግል" ሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን ለደረሰችበት የተሐድሶ (Reform) ጅምርና ጉዞ ፋና ወጊና ፈር ቀዳጅ ንቅናቄ ነበር ለማለት ይቻላል:: ይህንን ሁሉም ሊመሠክረው የሚችለው ሐቅ ነው::

ከድህረ ምርጫ 1997 ዓ.ም. ወዲህ በተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ መነሻነት የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉ በፍርሃት ቆፈን ተቀፍድዶ መንግሥትን በለዘበ ንግግር መተቸት እንኳን እንደ ከባድ ወንጀል የሚቆጠርበት ከባድ የአፈና ወቅት ነበር::

የግል የኅትመት ሚዲያዎች በከፍተኛ ደረጃ

**የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በሰነዘሩት ጥቃት ምክንያት ብዙዎች ተገድለዋል፤ ብዙዎችም የአካል ጉዳተኛ ሆነው እንዲቀሩ ተደርገዋል: : በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ነዋሪ የሆኑ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ለእስር ተዳርገዋል**

እንዲዳከሙ ተደርጓል:: የፀረ-ሽብርተኝነት፣ የመያድ፣ የፕሬስና ሌሎች አጨቃጫቂ አዋጆች ተደነገጉ:: ይህን መንግሥታዊ አፈና የሰላማዊ ትግል በሮችን ዘግቶታል በሚል፤ የትጥቅ ትግልን ጨምሮ ሁለንተናዊ ትግልን የሚያበረታታ "ግንቦት 7" የተባለ ንቅናቄ ተመሰረተ:: በ2002 ዓ.ም. ኢህአዴግ ሁለቱም የምክር ቤት ወንበሮች ጠቅልሎ በመውሰድ የአውራ ፓርቲ ትርክት ተጀመረ:: ሁሉም ነገር ፀጥ፣ ረጭ አለ::

ኢትዮጵያውን ሙስሊሞች ሰፍኖ የቆየውን የፍርሃት ቆፈን በጣጥሰው በመጣል፤ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ተጭኖ የቆየውን የአፈና ቀንበር አሽቀንጥሮ በመወርወር "እምቢ ለመብቴ! እምቢ ለነፃነቴ!" ብለው በዚያ የፍርሃት ደመና ሀገሪቱን በወረሰበት ወቅት አደባባይ ለመውጣት መቻላቸው ሀገራችን አሁን ለደረሰችበት የተሐድሶ ጉዞ ፋና ወጊና ጸያሔ ፍኖት መሆን ችለዋል::

ኢትዮጵውያን ሙስሊሞች ፋና ወጊና ጸያሔ ፍኖት ሆነው የለኮሱት የሰላማዊ ትግል ችቦ ተቀጣጥሎ በተለይ የኢትዮጵያ ግንድና እምብርት በሆነው ኦሮሚያ በምልዐት ተስፋፍቶ፤ በተወሰነ መልኩ ደግም በዐማራ ክልልም ተዛምቶ ከፍተኛና በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሕዝብ እንቅስቃሴና አብዮት እንዲከሰት አደረገ::

ይህንን ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴና አብዮት ተከትሎ በአገሪቱ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሁለት ጊዜያት የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ተጥሎ ወታደራዊ ኮማንድ ፖስት ተቋቋመ:: ይህ ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በገዛ ፈቃዳቸው ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ አስገድዶ አሁን ለደረስንበት የለውጥ ጅምር መነሻ ምክንያት ለመሆን ችሏል::

በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቀውን የሕዝብ እንቅስቃሴና አብዮት ተከትሎ፤ በሀገራችን የመንግሥት መድረክ የተለያዩ ለውጦችና የለውጥ ጅምሮችን እየተመለከትን ነው:: ሚኻኤል ጎርባቾብ ከኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ወጥተው ሶቪየት ኅብረትን "ፔሬስትሮይካ" በሚለው የኢኮኖሚ ቀመራቸው እንደለወጧት ሁሉ፤ ዓይነተኛ አምባገነን ድርጅት ከሆነው ኢህአዴግ ውስጥ የፈለቁት ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድም የኢትዮጵያን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ለመለወጥ ቆርጠው የተነሡ ይመስላሉ::

መደመር፣ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ኢትዮጵያዊነት፣ ዕርቅ የመሳሰሉ ዕሴቶችን ይዘው የተነሱት ክቡር ጠ/ሚኒስትሩ፤ ሰኔ 8 ቀን ምሽት በ3፡50 በጽሕፈት ቤታቸው ተገኝተው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተፈጠረውን ብጥብጥና የዒድ አል-ፈጥር በዓልን አስመልክተው ለ "etv ዜና" መግለጫ በሰጡበት ወቅት በንግግራቸው መካከል ሕዝበ ሙስሊሙን አስመልክተው የሚከተለውን ተናግረው ነበር::

"… እኩይ ዓላማና ተግባር ያላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች (ሰሞኑን የተፈጠረውን ብጥብጥ መነሻ አድርገው)፤ በተጨባጭም አልተሳካላቸውም እንጂ፣ ሕዝበ ሙስሊሙ በሃይማኖት ጉዳይ ግጭት እንዲፈጥርና ኢትዮጵያ ያልተረጋጋች አገር እንድትሆን የሚፈልጉ ኃይሎች እንዳሉ እናውቃለን::

ሕዝበ ሙስሊሙ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ማንኛውንም ጥያቄውን ሰምተን፣ ተነጋግረን ለመፍታት ከምንጊዜውም በላይ ዝግጁ መሆናችንን አውቆ፤ በዚህ ሃይማኖት ተጠቅመው ሊረብሹ፣ ሊያባሉን ለሚፈልጉ ሰዎች ግን ዕድል ፈንታ መስጠት የለበትም የሚል እምነት አለኝ::"

ይህንን የጠቅላይ ሚኒስትሩን "ማንኛውንም ጥያቄውን ሰምተን ተነጋግረን ለመፍታት ከምንጊዜውም በላይ ዝግጁ ነን" የሚለውን ጥሪ ተከትሎ፤ ከስድስት ዓመታት በፊት የተቋቋመው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ በጉዳዩ ዙሪያ እንዲያወያዩት በደብዳቤ የጠየቀ ሲሆን፤ በዚህ አጀንዳ ዙሪያም በዕለተ ሐሙስ፣ ሰኔ 14 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፤ ግሪን አዳራሽ በርካታ የሀገር ውስጥ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች በተገኙበት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል::

ኮሚቴው በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ተገኝቶ የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ "ሪፖርተር" ጋዜጣ በሰኔ 17 ቀን 2010 የእሁድ እትሙ ያስነበበን ሲሆን፤ በዘገባውም "ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በገቡት ቃል መሰረት በቅርቡ እንዲያነጋግሯቸው በደብዳቤ ጠይቀዋል::"

ኢትዮጵውያን ሙስሊሞች ከወርሃ ጥር 2004 ጀምሮ፤ ብቸኛው የሃይማኖት ተቋማቸው በሆነው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ውስጥ፤ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት በፈፀመው ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነትና አሉታዊ ቁጥጥርን በመቃወምና "ድምፃችን ይሰማ!" የሚል መሪ መፈክር በማንገብ ዓመታትን የወሰደ እልህ አስጨራሽ ሰላማዊ ትግል ያካሄዱበት ጉዳይ፤ በዐቢይ ዘመን መልስ ያገኝ ይሆን? ድምፃቸውስ ይሰማ ይሆን? የሁላችንም ጥያቄ ነው::



ኃይሉ አሰለፍገብሬ

# አባይ፡-ኢትዮጵያና ግብፅ

## እንደ መግቢያ

ግብፅና ኢትዮጵያ የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት አላቸው፤ ከሰማኒያ ከመቶ በላይ ከኢትዮጵያ የሚፈልቀው ጥቁር አባይ ከነጭ አባይ ጋር ተጨምሮ ለግብፃውያን የህልውናቸው መሠረት ነው፤ ከጥንት ጀምሮ የግብፅ መሪዎች ይህንን የህልውና መሠረታቸውን መጠቀምና ማስቀጠል የሚፈልጉት በኢትዮጵያውያን ኋላ ቀርነት፣ ደካማነትና ኪሳራ ላይ ብቻ ሆኖ መዝለቁ የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት እስከዛሬ አሉታዊ አድርጎታል:: ይህ በዲፕሎማሲ ቋንቋ፣ በተሸናፊነት መንፈስ በኢትዮጵያ መሪዎችና ፖለቲከኞች የሚሸፋፈን ቢሆንም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ለተያዘ ቅሬታና የቁጭት ስሜት ምክንያት ነው::

ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ይወዳሉ፣ ኳሱ ከሰንደቅ ዓላማቸው ጋር ሲሆን ደግሞ ውጤቱ ሁልጊዜ ህመም ቢሆንባቸውም የሚወዱት ስቃይ ነው:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከየትኛውም ሀገር አቻው ጋር ሲጫወት በሜዳ ተገኝተው የሚደግፉ፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን የሚከታተሉ፣ ዳኛው የተሳሳተ ውሳኔ ከሰጠ፣ ባይሰጥም ከመሰላቸው፣ “ዳኛው ግብፃዊ ነው እንዴ?” ብለው መጠየቃቸው የተለመደ አባባል ነው:: ይህም ከላይ በገለፅነውና እስካሁን በቀጠለው የግብፅ መሪዎች ፍላጎትና ተግባሮቻቸው ምክንያት የተያዘ ተገቢ ስሜት ሲሆን ዛሬ በእግር ኳሱ ብቻ መገለፁን መናቅ ትክክል አይደለም::

ቀደም ብሎ ግብፃውያን መሪዎች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ጥንታዊውን የሁለቱን ሀገሮች የሃይማኖት ግንኙነት ይጠቀሙ ነበር፤ ውጤታማም ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ግን የቀጠሉት የሀገራችንን የውስጥ ጉዳይና ቅራኔ እንዲሁም ኋላ ቀርነታችንን በመጠቀም እሴቶቻችን ላይ ቤንዚን በመጨመር፣ በመቆስቆስና በማንደድ ሲሆን በዚህም ውጤታማ ሆነው ዘልቀዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ግብፃውያን ወቅት ያተረፈላቸውን ተሰሚነት፣ ለፍትሐዊ ተጠቃሚነት ግድ የሌለውን ዓለምና በተለይ የአረብ ሀገሮችን አጋርነት ተጠቅመው የሀገራችንን የመልማትና የተፈጥሮ ሐብቷን የመጠቀም መብቷን ሙሉ ለሙሉ አፍነው ቆይተዋል::

እስካሁን በዚህ አጠቃላይ ዐውድ የቀጠለው የሁለቱ ሀገር ግንኙነት ትላንትም ዛሬም ለወደፊቱም ለሁለቱ ሀገሮችም አይጠቅምም:: ዛሬ ሁኔታዎች እያዘገሙም ቢሆን መቀየራቸውን መታዘብ ይቻላል፤ ወደፊትም መቀየራቸው አይቀሬ ነው:: አዝጋሚው ሂደትና የግብፅ መሪዎች ፍላጎት ግን ሁለቱንም እየጎዳ መቀጠሉን ወደፊትም የበለጠ ጉዳትና ኪሳራ እንደሚሆን መረዳት ተገቢ ነው::

የሁለቱ ሀገሮች አጀንዳ፣ ዛሬ ለኃይል ምንጭ ብቻ ነው ተብሎ እየተገነባ ካለው ከህዳሴው ግድብ የውሃ አሞላልና ከውሃ ክፍፍል በላይ፣ በወቅቱ የውሃ ሐብቱን የመጠቀም፣ በተለይ በኢትዮጵያ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ጥገኝነት በወቅቱ የቀነሰ ህዝብና ኢኮኖሚ ዕውን የማድረግ፣ ተፈጥሮን የመጠበቅ እና ግብፃውያን መሪዎች በኢትዮጵያውያን ስሜት ላይ የፈጠሩትን ቁስል የሚያሽር ግንኙነትና እውነተኛ ትብብርና ዕርቅ መሆን ይኖርባቸው ነበር:: በሁለቱም ሀገሮች መሪዎች እየተደረጉ ያሉ ድርድሮች፣ ውይይቶችና ስምምነቶች የጋራ ሆነው በዚህ መሠረት ላይ ካልተፈፀሙ ለሁለቱም ህዝቦች ችግርን የሚያራዝሙ፣ ከላይ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያውያንን ስሜት የሚያስቀጥሉ ብቻ ይሆናሉ::

## አባይ፤ የህዳሴው ግድብና የኢትዮጵያ መሪዎች፤

የኢትዮጵያ መሪዎች የወቅቱን ትኩሳትና ግርግር ብቻ ከማብረድ በላይ፣ ታሪካዊውንና ወቅታዊውን የግብፅ መሪዎችን ፍላጎቶችና ችግሮቻቸውን፣ ለሁለቱም ሀገራት ህዝቦች ያተረፉትንና ወደፊት የሚያተርፉትን ችግር፣ የቀጠለውን የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ስሜት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፣ ለራሳቸው ለግብፃውያን ሁሉ ለማስገንዘብ መሥራት ይገባቸው ነበር::

የዛሬውን የህዳሴ ግድብ ጨምሮ የአባይን ውሃ በኢትዮጵያ ለልማት ለመጠቀም ዕቅዱ የተዘጋጀው በንጉሡ ዘመን ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት በአሜሪካኖች ድጋፍ ነበር:: የአሜሪካኖች የድጋፍ ጅምር ለግብፅ የርዕዮተ ዓለም አሰላለፍ የተመዘዘ ቢጫ ካርድ ብቻ ስለነበር ግብፅ አሰላለፏን ስታስተካክል ለዓመታት የተደረገው ጥናት በሁለት ቀናት ተቋርጦ ዕቅዱ ከግማሽ ምዕተ ዓመታት በላይ አቧራ ሲጠጣ ቆይቷል::

ከምስራቁ ወደምዕራቡ ዞረው ለጊዜው የተሳካላቸው የግብፅ መሪዎች ኢትዮጵያ በራሷ አቅም ልትሠራ የምትችለውን ልማት ለመከላከል የመረጡት ስልት በሀገሪቱ ችግሮች ስንጥር በማስገባት ማዳከምን ነበር:: ጀብሃን፣ ሻዕብያን፣ ወያኔንና ሌሎችንም መሣርያና ችግሮቻችንን ብቻ ከላይ (መሠረታዊ መንስኤዎቻቸውን ሳይሆን) ማስታጠቃቸውን፣ ዛሬም የአኩራፊዎቻችን አለኝታና መጠጊያ ሆነው መዝለቃቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም:: በተጨማሪም ኢትዮጵያ ዓባይን ለሚመለከቱ ማንኛውም ዕቅዶች ከየትኛውም ሀገርና የገንዘብ ተቋም ብድር፣ እርዳታና የቴክኒክ ድጋፍ እንዳታገኝ ሳታመነታ በመሥራቷና ስለተሳካላትም ጭምር ዛሬ የሀገራችን መሪዎች ግፉን አሜን ብለው ሊቀበሉት ችለዋል::

በዚህ ሂደት ኢትዮጵያ በረጅም የእርስ በርስ ጦርነት፣ በችጋርና በመከራ ውስጥ እየተንፏቀቀች፤ በድርቅና በረሀብ የሰው ሕይወት እየጠፋ ለስድሳ ዓመታት ስትዘልቅ የህዝብ ቁጥሯ ዛሬ ከመቶ ሚሊዮን በላይ ቢሆንም እንደጥንቱ ሙሉ ለሙሉ የተፈጥሮ ጥገኛ እንደሆነ ነው:: ቀደም ብሎ የተሻለ ውጤታማ የሆነውን የአባይ ውሃ በተወሰነ መጠን የማልማት ዕድል ቢኖራት፣ ሀገሪቱ የጦርነት አውድማ ባትሆን፣ ትምህርት ቢስፋፋና እድገት ብታስመዘግብ ኖሮ፣ ዛሬ ሀገሪቱ የተመጠነ የህዝብ ቁጥር፣ በተወሰነ መልኩ ከተፈጥሮ ጥገኝነት የተላቀቀ ኢኮኖሚና ህዝብ እንዲሁም ሌሎች የተፈጥሮና የውሃ ሐብቶቿን ለመጠቀም የሚያስችል አቅም ይኖራት ነበር::

ባለቤቶች ራሳችን ብንሆንም በግብፅ መሪዎች የሚደገፈው ኋላ ቀር ጉዞ ግን ሌሎችን ጨምሮ የተፈጥሮ ሐብት የሆነውን የአባይ ውሃ በመጠኑ ቀንሶታል:: ይህም የተፈጥሮ ሐብቶች ለሀገራችን ያላቸውን አስፈላጊነት ከነበረው በአራት እጥፍ ጨምሮታል ማለት ይቻላል::

የግብፅ መሪዎችን አፍራሽ ፍላጎት ለመቋቋምና መብታችንን መጠቀም ለመጀመር ደግሞ ዘገየን፤ ይህም ዋጋ ቢያስከፍለንም እስከመጨረሻው ሊገታን አልቻለም:: የህዳሴውን ግድብ ጀምረነዋል፤ ወደፊትም እንቀጥላለን::

የኢትዮጵያውያንን በተፈጥሮ ሐብታቸውና በአባይ ውሃ የመጠቀምን መብት የሚወስኑት ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶች፣ ሀገራችን ከዓለም አቀፍ ተቋማት የምታገኘው የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ እና የሀገራችን ውስጣዊ አቅም ናቸው:: ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ያለውና ወደፊት የሚኖረው የተፈጥሮ ሀብት፣ የውሃ ሀብቱ ተጨባጭና ወቅታዊ አስፈላጊነት፣ ከታችኛው ተፋሰስ ሀገሮች በተለይ ከግብፅና ከሱዳን ጋር ያሉን ታሪካዊና ወቅታዊ ግንኙነቶች፣ ታሪካዊ ቁርሾዎች ድርሻ አይኖራቸውም ማለት አይቻልም:: ይህንን ለግብፅ መሪዎች በግልፅ ቋንቋ ከማስረዳት ባሻገር፣ በተለያዩ ሥልቶች ለሀገራችን ጉዞ እንቅፋት መሆናቸውን ማቆም እንደሚገባቸው በፊትም ሊነገራቸው ይገባ ነበር::

“ይቻላል” ተብሎ የተጀመረው የህዳሴው ግድብ መሠረት ሲጣል፣ ሀገራችን ሀብቷን ለምን ሳትጠቀም እንደዘገየች፣ ዛሬም እንዴት እንደምትገነባው ተገልፆ፣ ከታሪካችን የወደፊቱን ማመላከት ለሁሉም ጠቃሚ ነበር:: ኢትዮጵያውያን የመልማትና የመጠቀም መብታቸው በግብፅ ታፍኖ ለዘመናት ከዘለቁ በኋላ፣ ይህንን አፈና ለመቀልበስ በተጀመረው ግንባታ ውስጥ የአፈናውን አንዳንድ ስልቶች ከተቀበለ የተሸናፊነት ስሜት ጋር የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጥና ከዚያ በኋላ ማስቀጠል ስህተት ነው:: ለወደፊቱም አቅም አይሆንም::

በውጭ ሀገር ሥራ ተቋራጭ፣ በከፍተኛ ብድር ላይ የተደገፈና በእርዳታ በሚደጎም አጠቃላይ ኢኮኖሚ የሚገነባን አንድ ፕሮጀክት፣ የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር “መሐንዲሶችም፣ ግንበኞችም፣ የፋይናንስ ምንጮችም እኛው” ብለው በኩራት መናገራቸው ተገቢ ሳይሆን▶

ከፍተኛ ስህተትም ሲሆን፣ የተጫነብንንም ግፍ በፈቃዳችን የመረጥነው መሆኑንና አቅማችንን ያስገነዝባል:: በፍርሃትና በራስ ስሜት ብቻ መሸነፋችንን፣ ግፍንም አሜን ብለን መቀበላችንን ያረጋግጣል:: ከዚህ ስሜት መውጣት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው::

በመንግሥት ብቻ ተገድቦም አልቀረም፤ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ስለግድቡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው ሲናገሩ፣ ታሪክን አንሥተው የገለፁበት መንገድም ተመሳሳይ ነበር፤ "የአክሱምን ሕንፃ ስናቆም፣ ላሊበላን ስናንፅ የዓለም ባንክ፣ አይ.ኤም.ኤፍ ነበሩ?" ሲሉ ራሳቸው ጠይቀው "አልነበሩም፤" ብለው ራሳቸው መልሰዋል:: በአዎንታ ራሱን ለሚነቀንቀው ጋዜጠኛ "የህዳሴውን ግድብ ለመገንባትም ዛሬ እነዚህ ተቋማት ግዴታ አይደሉም፤ አያስፈልጉንም፤ በራሳችን አቅም መገንባት እንችላለን፤" ሲሉ በስሜት ተናግረዋል፤ ከስሜት ጋር ደግሞ ስህተቶች አሉ::

ዓለም ላይ ስመ ገናና የነበረውን አክሱም፣ የመን ድረስ ተሻግሮ አስተዳድሯል፤ ህንድ ድረስ የንግድ ግኙነት ነበረው፤ ለግብፅ ክርስቲያኖች ጭምር አለኝታ ነበር፤ የምንለውን ሀገርና ህዝብ ሐውልት ሲያቆም፣ ግብፃውያን ንቀውታል፤ በዓለም ሀገሮች ዓይን አይሞላም፤ ብቻውን ነበር ማለት ከፍተኛ ስህተት ነው:: መነሻቸው ከመከካለኛው ምሥራቅ የሆኑት፣ በየጊዜው ከምንጫቸውና ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነቶች የነበራቸው ክርስትናችን እና ንጉሡ ላሊበላ ቤተ-መቅደስ ሲገነቡ ብቻቸውን ነበሩ ማለት አለማገናዘብ ብቻ ነው::

ዛሬ እኛ አሽቆልቁለን ዓለምና ተቋማት ተራምደው እነዚህ ሁሉ አያስፈልጉንም ማለት ሞክራ ያልቻለችውን ጦጣ የሚስታውስ ብቻ ይሆናል:: ዛሬ በግብፅ መሪዎች ፍላጎት ጫማ ሥር ወድቀን በሌሎች ሀገሮች፣ በዓለም ባንክ፣ በ አይ.ኤም.ኤፍ ዓይን መሙላት አለመቻላችንን በተለይ ከአክሱም ሥልጣኔ ጋር ማነፃፀር ነው ተገቢ የሚሆነው፤ የሚጠቅመንም::

በዘመናቸው ያላስፈለጋቸውን አባይ አክሱማውያን ለግብፅ ወንድሞቻቸው ብቻ ቢተውት ትክክል ነበሩ፤ ተቀባይነታቸውን፣ ጥቅማቸውንና ፍላጎቶቻቸውን ለማረጋገጥ አባይን የተጠቀሙበት ግን ውሃውን መገደብ ስለሚችሉ ነበር:: ዛሬ የውሃ ሀብቱ እጅግ አስፈላጊ ቢሆንም ለዘመናት ሳንጠቀምበት የሰው ሕይወት እየጠፋ፣ በችጋርና በመከራ ውስጥ ቆይተናል:: ይህንን ታሪክ ለመቀየር እንደምንችል፣ እንደጀመርነው ከዚህ በኋላ መቀጠል ይቻላል:: ለህዝቡ ሞራል ተብሎ ከተገለፀም መቅደም የነበረበት ችግሩ ነው:: ለህዝቡ ሞራል፣ መነሣሣትና ርብርብም ምክንያቱ እነዚህ የውሸትና የማስመሰል ንግግሮች አይደሉም፤- ከላይ የተገለፀው የዘመናት ቁጭቱ እንጂ::

ናይል፣ የህዳሴው ግድብና የግብፅ መሪዎች፤

ከግብፃውያኑ መሪዎች ዛሬ ደግሞ የሚጠበቀው፤ የትናንቱን ስህተት ሁሉ የሚያራግፍ፣ አፍራሽ ተልእኮቻቸውን ሁሉ ማቆም ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ስሜትና ቁርጠኝነት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሀብታችንን የመጠቀምና የማልማት መብቶቻችንን በማክበርና በማረጋገጥ የታሪካዊውን ግንኙነት መስመር በወቅቱ ማስተካከል ነበር:: ግብፃውያን መሪዎች የዛሬውን የኢትዮጵያ መሪዎች ፖለቲካና ዲፕሎማሲ ትተው ዘላቂውንና ከላይ የተገለጠውን የዜጎችን ስሜት መረዳት አለባቸው::

ግብፅና መሪዎቿ በቅርቡም በሀገራችን የተከሰተውን ችግር ለማራገብ ሞክረዋል፤ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ በቅኝ ግዛት ውል ለመሞገትና ንቀታቸውን ለመቀጠል ሞክረዋል:: ኢትዮጵያ በአዝጋሚ ሂደትም ቢሆን መቆም ጀምራለች:: ግብፅና መሪዎቿ ያራገቡት ችግር ዛሬ ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድን የመሰለ ተስፋ



የተጣለበት መሪ አምጥቷል:: ምንም ቢሆን የነገዋን ኢትዮጵያ በተሻለ ተስፋ መጠበቅ ግዴታ ስለሆነ አቋምን በወቅቱ ማስተካከል የግብፅና መሪዎቿ ወቅታዊ ግዴታ ነበር::

ከኢትዮጵያ መሪዎች የተሸናፊነት ስሜትና ፈራ ተባ ብለው በያዙት የዲፕሎማሲ አቋም ምክንያት የህዳሴው ግድብ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለና በኢትዮጵያ ህዝብ ርብርብ ግንባታው ከቀጠለ በኋላም የግብፅ መሪዎች አቋም የተለያየ መልክ ነበረው::

የመሠረት ድንጋዩ በተጣለ ማግስት የግብፅ መሪ የነበሩት ሆስኒ ሙባረክ ያቀኑት በንቀታቸው ምክንያት ወደኢትዮጵያ ሳይሆን ወደጣልያን ነበር:: ይህም ግድቡን የሚገነባው ሳሊኒ የጣልያን ሥራ ተቋራጭ ስለሆነ በጣልያን መንግሥት በኩል እንቅፋት ለመሆን የተደረገ ሙከራ ነው:: የጣልያን መንግሥት "ሳሊኒ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነ ተቋም ስለሆነ ጣልቃ መግባት አንችልም፤" በማለት ሙከራውን አልተቀበለውም:: ሙከራው ወደሳሊኒ አልቀጠለም ወይም ቀድሞ አልተሞከረም ብሎ አለማሰብ አይቻልም፤ ሳሊኒ ከሀገራችን ጎን ቆሞ መቀጠሉን ከማድነቅ ጋር::

ሆስኒ ሙባረክን የተኩት የሙስሊም ወንድማማቾቹ ሙርሲ ከዚህም በላይ የግብፃውያንን ህልውና ለማስጠበቅ እንደሚዘምቱና የጦር መሪዎቻቸውን ሰብስበው ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ ታዝበን ነበር:: በተለያዩ የውስጥ ቀውሶች በቀጠለችው ግብፅ ከሙርሲ በኋላ ወደሥልጣን ከመጡት አል.ሲ.ሲ መጀመርያ ላይ የለውጥ አዝማሚያ ታይቶ ነበር::

አል.ሲ.ሲ የኢትዮጵያውያንን የመልማት ፍላጎት እንረዳለን፣ እንደግፋለን ብለው፤ ከመሪዎች አልፎ የሁለቱ ሀገሮች የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትም ተጀምሮ ነበር:: በሊቢያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በግብፅ በኩል ወደሀገራቸው እንዲገቡ ከመተባበርም አልፈው በአውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው አቀባበል አድርገውላቸው ነበር:: ለሁለቱ ሀገሮች የሚበጀው ተመሳሳይ ግንኙነት፣ መተባበርና መከባበር ስለሆነ ተስፋን ያጫረ ጅምር ቢሆንም የቀጠለና የጎለበተ ግን አልነበረም::

ከዚህ በኋላ በሁለቱ ሀገሮች የቀጠለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፤ ውይይቱና ድርድሩ ሁሉ በትክክለኛው መሠረት ላይ ያልቆመ፣ በጥርጣሬና ባለመተማመን ላይ የተመሠረተ ነበር:: በአጠቃላይ ሱዳን የነበራትን አቋም ያስተካከለችበት ሲሆን፣ የግብፅ መሪዎች ግን የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ አመንጭተን የምንለቅበት ነው የምንለውን ግድብ እንኳን በሙሉ ልባቸው ለመቀበል ተቸግረዋል:: እስከዛሬ በባከነው ጊዜ፣ ኢትዮጵያውያን ጥቂት መብቶቻችንን ለመጠቀም ሳንችል የቆየንበትን ታሪክ አልተረዱትም:: አንድ ጊዜ ዝቅ ስላደረጉን የወደፊቱን ተገቢ ፍላጎቶቻችንን ከወዲሁ አልገመቱትም:: ስለዚህ በዚህ የምንቀጥል ከሆነ መጨረሻው ለማንም የማይጠቅም በተለይ ግብፃውያንን ዋጋ የሚያስከፍል ብቻ ይሆናል:: በዚህ ሁኔታ ትናንትን ወደኋላ በማስታወስና ዛሬን በመመልከት የወደፊቱን መዘዝ ለመተንበይ ይቻላል::

## እንደ መደምደሚያ

የኢትዮጵያውያንን በተፈጥሮ ሀብታቸውና በአባይ ውሃ የመጠቀም መብት በሚወስኑት ሁኔታዎች መሠረት ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት የሚተርፈውን የውሃ ሀብት ግብፃውያን የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል::

የግብፅ መሪዎች ኢትዮጵያን እንደጥንቱ አፍነው መቀጠል አይችሉም፤ ቢችሉም አይጠቅማቸውም:: ከዚህ ባሻገር ግን የግብፅ መሪዎች በዚሁ ቀጥለው ሀገራችን የጀመረችውን በተለያዩ መንገዶች የተፈጥሮ ሀብቷን የመጠቀም መብቷን እያረጋገጠች ስትቀጥል አቅማችን ያድጋል:: ያልነበረን ወንድማማችነትና ትብብር ድንገት ማምጣት ስለማይቻል ግብፃውያን እንደአክሱም ዘመን በወንድማማች ህዝቦች መካከል በሚኖር የትብብር መንፈስ ከኢትዮጵያ ጋር የመሥራት ዕድላቸው እየጠበበ ይሄዳል:: በዚህ ወቅት በመካከላችን የሚኖረው ዓለም አቀፉ ሕግና ስምምነት ብቻ ይሆናል:: በዚህ ሁኔታም ግብፃውያን አያተርፉም::

የሩቅ ታሪክም ቢሆን ሀገራችን በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ ነበር:: አፄ ቴዎድሮስ ሀገሪቱን በቀላሉ አንድ አድርገው ቢነሡም ፍጻሜያቸው እንደዘመነ መሳፍንት ወቅት ነበር:: ንጉሡ በመቅደላ ተወስነው፤ በትግራይ በዝብዝ ካሳ፣ በሸዋ አፄ ምኒልክ፣ በላስታ ዋግሹም ጎበዜ ነግሠው ነበር:: እንግሊዝ በአፄ ቴዎድሮስ የተያዙ ዜጎቿን ለማስፈታት ዕቅድ ስትነድፍ የተያዘ አንድ ግንዛቤ ነበር:: እንግሊዞች ለኢትዮጵያ ቅርብ ከሆኑት ቅኝ ግዛቶቻቸው ግብፅና ሱዳን ጦር ለማዝመት ሀሳብ ነበራቸው:: ኢትዮጵያውያንን ምን ቢከፋፈሉ ከእነዚህ ሀገሮች የሚሰነዘር ጥቃት አንድ ላይ እንደሚያቆማቸው ስለተረዱ ከህንድ ነበር ጦር ያዘመቱት:: ሶማሊያና ዚያድባሬ እስከአፍንጫቸው ታጥቀው፣ ኤርትራና ሻዕቢያም በራሷ በግብፅ ስፖንሰርነት የደረሰባቸውን አይተውታል::

ዛሬ በኢትዮጵያ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፤ የተፈጠረ አቅም፣ የተያዘ ግንዛቤና ስምምነት አለ፤ ይህም ይቀጥላል:: ከዚህ ጋር ዋናው የነበረውና ያልተቀየረው ወደኳስ ሜዳ እንደሚሄድ እየጨፈረ ለሀገሩ ወደጦር ሜዳ የሚተም ኢትዮጵያዊ እንዳለ መረዳት ጠቃሚ ነው:: ከላይ ስለግብፅና አባይ ከያዘው ስሜት ጋር ይህንን ማሰብ በዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ በኢኮኖሚና በዲፕሎማሲ የበላይነት የተመሠረተን እብሪት ከወዲሁ ማስተካከል እንደሚገባ ያስገነዝባል:: ይህም ዕብሪተኛ መሪዎቿን ጨምሮ ለግብፃውያን በሙሉ፣ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብና ተቋማት ግንዛቤ ወሳኝ ነው::


# የሁለቱ ሲኖዶሶች መጨረሻ ምን ይሆን?



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

ላለፉት 25 ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ለሁለት ተከፍለው የኖሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች፤ በመጪው ሐምሌ በዋሽንግተን ዲሲ የዕርቀ ሰላም ውይይት እንደሚያካሂዱ ይጠበቃል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ “ግንቡን እናፍርስ ድልድዩንም እንገንባ = Break the wall, Build the Bridge” በሚል መሪ ቃል በመጪው ሐምሌ 20 እና 21 በአሜሪካ፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና ሎሳንጀለስ ከተሞች ከሚያደርጉት የሥራ ጉብኝት ቀደም ብሎ፤ በዋሽንግተን ዲሲ ማርዮት ማርከስ ዓለም አቀፍ ሆቴል፣ የሲኖዶሳዊው ዕርቀ ሰላም ንግግር የሚካሔድ ሲሆን፤ ውይይቱም ከሐምሌ 11 እስከ 20 ቀን 2010 ዓ.ም. እንደሚዘልቅ ተገልጿል፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያና የሚመራውና ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በጸሐፊነት የሚገኙበት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአሜሪካ ጉብኝት አመቻች ኮሚቴ፣ ባለፈው ረቡዕ፣ ከቀትር በኋላ በማሪዮት ሆቴል በሰጠው መግለጫም፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በዋሽንግተን ዲሲ በሚኖራቸው ቆይታ፣ በስደት የተቋቋመው ሲኖዶስ ርእሰ መንበር የሆኑትን፣ አራተኛውን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን አግኝተው እንደሚያነጋግሩ ጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሲኖዶሳዊ አንድነት ለማምጣት ጥረት የሚያደርገው፣ የአባቶች ዕርቀ ሰላም ዓለም አቀፍ ኮሚቴ፣ 30 ያህል ሽማግሌዎች የሚገኙበት ሲሆን፤ የአዲስ አበባው ቅርንጫፍ ተሳታፊ አባላት ከሦስቱ ልኡካን ብፁዓን አባቶች ጋራ፣ ሐምሌ 11 ቀን 2010 ዓ.ም. ወደ ሥፍራው እንደሚያመሩ ተገልጿል፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ሚያዝያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም. “ከውጭ አባቶች ጋራ ስላለው ዕርቀ ሰላም” በሚል አጀንዳ ከዕርቀ ሰላሙ ጋራ በተያያዘ ስለሚቀበላቸው መርሖዎችና ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ተወያይቶ፣ ባለፈው የካቲት ወር፣ ቅዱስ ሲኖዶሱን በመወከል የሚደራደሩትን ልኡካን ምርጫ በማጽደቅ ለተልእኮ የሠየማቸውና ሐምሌ 11 ወደአሜሪካ የሚጓዙት ልኡካን፡- የሰሜን ምዕራብ ሸዋ - ሰላሌ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ፣ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እና የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሲሆኑ፣ በብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ እንደሚመራም ተገልጿል፡፡

ከቀድሞው በተሻለ አያያዝ ተነሣሽነቱን በመውሰድ ከሚያደራድሩትና ከሚያነጋግሩት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ ዙር የሰላም እና አንድነት የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ኮሚቴ አባላትም፡- ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም፣ ዶ/ር ንጉሡ መለሰ፣ አቶ ግርማ ዋቄ፣ ዶ/ር አብርሃም፣ ቀሲስ ዶ/ር መዝገቡ ካሳ እና አቶ ብርሃን ተድላ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስም፣ ከጥቅምት 22 እስከ 24 ቀን 2010 ዓ.ም. በኮለምበስ ኦሃዮ ባደረገው ጉባኤ፣ በሁለት የሰላም እና አንድነት ኮሚቴው አባላት የደረሰውን የዕርቀ ሰላም መልእክት በስፋት ከተወያየበት በኋላ፣ በብፁዕ አቡነ ኤልያስ የሚመራ ሦስት አባላት ያሉት ተደራዳሪ ልኡክ በመሠየም፤ ለስኬቱም ከኮሚቴው ጎን እንደሚቆም ገልጾ፣ “እግዚአብሔር ይጨመርበት፤ አምላከ አበው ሥራችሁን የተቃና ያድርግላችሁ” በማለት ቡራኬውን ሰጥቶ መስጠቱን በጻፈው ደብዳቤ አስፍሮ ነበር፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ግንቦት 4 ቀን 2010 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት፤ ቅዱስነታቸውና የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዊ አንድነት ለማስጠበቅ በጀመሩት የዕርቀ ሰላም ጥረት እንዲገፉበት ከማሳሳብ ባሻገር፤ ጥረቱ እንዲሳካ፣ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንደሚሰጥ አስታውቀዋቸው ነበር፡፡

ለሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላት ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በሲኖዶሳዊ አስተዳደሯ መከፋፈሏ በግላቸውም ቢኾን እንደሚያሳዝናቸው የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ አንዲትና ታላቅነቷ የተጠበቀ የተጠናከረች ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ማየት ፍላጎታቸው እንደሆነ ለቅዱስነታቸው በወቅቱ ገልጸውላቸዋል፡፡

“ልዩነቶቹ በተለያየ ምክንያት ተከሥተው ሊኾን ይችላል፤ ነገር ግን ለመፍታት የማይቻሉ አይመስለኝም፤ ይቻላል፤ ሃይማኖታዊ ሰው ደግሞ አይደለም የውስጡንና የራሱን፣ የሌሎችንም ችግር መፍታት አይሳነውም ተብሎ ነው የሚታመነው፤” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አያይዘውም፣ “የሌሎችን ችግር ይፈታሉ የተባሉት ችግር ፈቺዎቹ ራሳቸው ከተቸገሩና ሌላ ችግር ፈቺ ካስፈለጋቸው ትልቁ ችግር የሚኾነው እርሱ ነው፤” በማለት ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ልዩነቷን ለማስወገድ በያዘችው ጥረት እንድትቀጥልበት አበረታተዋል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ በበኩላቸው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ስለ ማበረታቻ ሐሳባቸውና አቋማቸው በማድነቅና በማመስገን፣ በውጭ ከሚኖሩት አባቶች ጋራ የተጀመረው ዕርቀ ሰላም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው ስላደረጋቸው ጥረቶች አብራርተው፤ ቅዱስ ሲኖዶስም ባካሄደው ዓመታዊ ጉባኤው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቋቋመው የሰላምና አንድነት ኮሚቴ፣ ከቀድሞው በተሻለ አያያዝ ሒደቱን ለማስቀጠል ላቀረበው ጥያቄ ይሁንታውን በመስጠት የሚነጋገሩ ልኡካን አባቶች መሠየሙንም ነግረዋቸው ነበር፡፡

ይህ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳሳቢነት፤ ለ25 ዓመታት ያህል ተለያይተው የኖሩትን ሲኖዶሶች ወደዕርቀ ሰላም ውይይት ያደረሰው መልካም መንገድ፣ በመንግሥት እያመካኙ ወይም መንግሥት እንዲህ ሊያስብ ይችላል፤ እያሉ ወደ ኋላ የሚሉትንና በዕርቀ ሰላሙ ሒደት ላይ ሻጥር የሚፈጥሩትን የሀገር ቤት አካላት አስታግሦ፤ በውጭ ባሉትም ዘንድ፣ “ዕርቀ ሰላሙን መንግሥት አይፈልገውም፤” የሚለውን ስጋት አስወግዶ የሚፈለገውን አንድነት ያመጣ ይሆንን?




## የባሕር ዳር የድጋፍ ሰልፍ እሁድ ሰኔ 24 2010 ዓ.ም




## በቦንጋ ከተማ ማክሰኞ ሰኔ 26 2010ዓ.ም



